የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የኢትዮጵያ የ2017 የዘላቂ ልማት ግቦች የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ

## የመንግስት ቁርጠኝነት፣ ሀገራዊ ባለቤትነት እና የአፈፃፀም አዝማሚያዎች





# የኢትዮጵያ የ2017 የዘላቂ ልማት ግቦች የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ

የመንግስት ቁርጠኝነት፣ ሀገራዊ ባለቤትነት
እና የአፈፃፀም አዝማሚያዎች

# ማውጫ


| | | |
|---|---|---|
| | **መቅድም** | i |
| 1. | መግቢያ | 1 |
| 2. | የግምገማ ዘዴዎች እና ሂደቶች | 3 |
| 2.1. | **የግምገማ ዘዴዎች** | 3 |
| 2.2. | **የግምገማ ሂደቶች** | 3 |
| 3. | ፖሊሲዎችና አስቻይ ሁኔታዎች | 7 |
| 4. | የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሀገራዊ ልማት ማዕቀፍ ጋር ማስተሳሰር | 9 |
| 5. | ሶስቱን የዘላቂ ልማት ገፅታዎች ማስተሳሰር | 13 |
| 6. | ግቦችና ኢላማዎች | 14 |
| 7. | የዘላቂ ልማት ግቦች ትግበራ | 17 |
| 7.1. | **የዘላቂ ልማት ግቦች አጠቃላይ አፈፃፀም** | 17 |
| 7.2. | **ዘላቂ ልማት ለሁሉም** (Leaving No One Behind) | 19 |
| 7.3. | **የዋና ርዕስ ትንተና፡- ድህነትን ማጥፋትና ብልጽግናን ማስፋፋት** | 24 |
| 7.4. | **የስድስቱ ዘላቂ የልማት ግቦች ዝርዝር ግምገማ** | 28 |
| 8. | የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈፀሚያ ተቋማዊ አደረጃጀቶች | 52 |
| 9. | የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈፀሚያ ዘዴዎች | 54 |
| 10. | የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማስፈፀም ቀጣይ እርምጃዎች | 56 |
| 11. | ክትትል፣ ሪፖርትና ግምገማ | 58 |
| 11.1. | **መረጃ፣ ስታቲስቲክስ እና አመልካቾች** | 59 |
| 11.2. | **የክትትል፣ ሪፖርትና ግምገማ ዘዴዎች** | 60 |
| 11.3. | **ተሞክሮዎች፣ ፈተናዎች እና መልካም አጋጣሚዎች** | 60 |
| 12. | ማጠቃለያ | 63 |
| 13. | የስታቲስቲክ አባሪዎች | 69 |
| 13.1. | **የተመረጡ የዘላቂ ልማት ግቦች አፈፃፀም ማሳያዎች** | 70 |
| 13.2. | **የተመረጡ የዘላቂ ልማት ግቦች አፈፃፀም ማሳያዎች…የቀጠለ** | 71 |
| 13.3. | **ዝርዝር ግምገማ የተካሄደባቸው የዘላቂ ልማት ግቦች አፈፃፀም** | 71 |
| 13.4. | **ዝርዝር ግምገማ የተካሄደባቸው የዘላቂ ልማት ግቦች አፈፃፀም…የቀጠለ** | 74 |
| 13.5. | **ዝርዝር ግምገማ የተካሄደባቸው የዘላቂ ልማት ግቦች አፈፃፀም…የቀጠለ** | 75 |
| 13.6. | **ዝርዝር ግምገማ የተካሄደባቸው የዘላቂ ልማት ግቦች አፈፃፀም…የቀጠለ** | 77 |
| 13.7. | **ዝርዝር ግምገማ የተካሄደባቸው የዘላቂ ልማት ግቦች አፈፃፀም…የቀጠለ** | 79 |

# መቅድም

ኢትዮጵያ በምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች (MDGs) የትግበራ ሂደት ውጤታማ አፈፃፀም ካስመዘገቡ ጥቂት የአፍሪካ አገራት መካከል አንዷ ናት፡፡ ይህንን የዳበረ ልምድና መልካም ተሞክሮ መሠረት በማድረግ ዓለም አቀፍ የዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030ን በባለቤትነት በመውሰድና የብሔራዊ የልማት ዕቅድ አካል በማድረግ ወደ ትግበራ ገብታለች፡፡ እ.ኤ.አ ኦገስት 2016 ዓ.ም ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት በቀረበላት ጥያቄ መሠረት የዘላቂ ልማት ግቦች የ2017 የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ አካሂዳለች፡፡

ይህ የኢትዮጵያ የዘላቂ ልማት ግቦች የ2017 የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ ሪፖርት ለ2017 የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ በተመረጡት ስድስት የዘላቂ ልማት ግቦች (ግብ 1፣2 ፣3፣5፣9 እና 14) ላይ ትኩረት በማድረግ እንዲሁም ስለ ሪፖርቱ ዝግጅት በተሰጠው መመሪያ እና የ2017 የፈቃደኝነት ብሔራዊ የግምገማ ዋና ርዕስ የሆነው ድህነትን ማጥፋትና ብልፅግናን ማስፋፋት ላይ መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሰነድ ነው፡፡ይህም የኢትዮጵያ የ2017 የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ ሪፖርት እ.ኤ.አ ጁላይ 2017 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት ከፍተኛ የፖለቲካ መድረክ ቀርቧል።

የኢትዮጵያ የዘላቂ ልማት ግቦች የ2017 የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ ሪፖርት ሁለት ዓላማዎች አሉት፡፡የመጀመሪያው ዓላማ የዘላቂ የልማት ግቦችን በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ተፈፃሚ ለማድረግ የተደረጉትን ዝግጅቶች በመዳሰስ፣ የተመዘገቡትን አፈፃፀሞች በሀገር አቀፍ፣ በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች ደረጃ በመገምገም የአፈፃፀም ጥንካሬዎችን፣ ፈተናዎችንና መፍትሄዎችን፣ መልካም ተሞክሮዎችን እንዲሁም የወደፊት መልካም አጋጣሚዎችን በግልፅ የሚያመላክት የግምገማ ሪፖርት ማዘጋጀት ሲሆን ሁለተኛው ዓላማ ሀገራችን በዘላቂ ልማት ግቦች የአፈፃፀም ሂደት ያሏትን ተሞክሮዎች ለሌሎች ሀገሮች ማካፈል እና ለመድረኩ ተመሳሳይ የግምገማ ሪፖርት ከሚያቀርቡ ሌሎች አገሮች በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የዘላቂ ልማት ግቦችን አፈፃፀም ስኬታማ ለማድረግ የሚረዱ ልምዶችን መውሰድ ነው፡፡

በተዘጋጀውም ረቂቅ የ2017 የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ ሪፖርት ዙሪያ ለመወያየትና ግብዓት ለማሰባሰብ በፌዴራል፣ በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች ደረጃ የመንግስት አስፈፃሚ ተቋማት፣የፓርላማ አባላት፣ የግል ተቋማት፣የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የትምህርት ተቋማት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት እና የልማት አጋሮች ተወካዮች በተሳተፉባቸው የምክክር መድረኮች ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡ ከምክክር መድረኮቹ የተገኙ ግብዓቶችንም በማካተት ሰነዱን የማዳበር ሥራ ተሠርቷል፡፡

ይህ የዘላቂ ልማት ግቦች የ2017 የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ ሪፖርት በብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን መሪነትና አስተባባሪነት ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በተወካዮቻቸው አማካኝነት በማሳተፍ ተዘጋጅቶ የመንግስትን ይሁንታ ካገኘ በኃላ ሪፖርቱ በተባበሩት መንግስታት ከፍተኛ የፖለቲካ መድረክ ቀርቧል፡፡

በአጠቃላይ ይህ የዘላቂ ልማት ግቦች የ2017 የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ ሪፖርት ኢትዮጵያ የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ለማሳካት ያላትን ቁርጠኝነት እና ባለቤትነት በግልፅ የሚያሳይ ሲሆን ለሌሎች አገሮችም ጠቃሚ ተሞክሮችን እንደሚያስተላልፍ ይታመናል።

**ጌታቸው አደም**



**በሚኒስትር ዴኤታ ማዕረግ**

**የብሔራዊ ፕላን ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር**

# 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ ምድረ ቀደምት (የሰው ዘር መገኛ፣ የአረቢካ ቡና ዘር መገኛ፣ የዓባይ ወንዝ መነሻ፣ የብርቅዬ የዱር እንስሳት መገኛ...ወዘተ) እና ብዝሀነትን እያስተናገደች ያለች ሀገር ናት (Ethiopia is Land of Origins and Diversity)። የረጅም ዘመን ታሪክ ያላትና በቅኝ ግዛት ዘመን የአፍሪካ የነፃነት አርማ ሆና የኖረች ሀገር ናት። ሊግ ኦፍ ኔሽንን ከመሠረቱ ቀደምት ሀገራት መካከል አንዷ ስትሆን ቀደም ሲል የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እና በአሁኑ ጊዜ ደግሞ የአፍሪካ ህብረት ዋና መቀመጫ ናት። ኢትዮጵያ የተለያዩ መንግስታዊ ሥርዓቶች የተፈራረቁባት፤ በቋንቋ፣ በኃይማኖት፣ በባህል እና በመልክዓ ምድር አቀማመጥ የተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ተከባብረው፣ ተፈቃቅደውና ተቻችለው በአንድ ላይ የሚኖሩባት ስትሆን በአሁኑ ጊዜ የፌዴራል አደረጃጀትና ያልተማከለ የአስተዳደር ሥርዓት የምትከተል ሀገር ናት። በፌዴራል አደረጃጀቱ መሠረት የፌዴራል መንግስት፣ 9 የክልል መንግስታት (Regional States) እና 2 የከተማ አስተዳደሮች (City Administrations) ሀገሪቱን እየመሩና እያስተዳደሩ ይገኛሉ። የሀገሪቱ ጠቅላላ ስፋት 1.1 ሚሊዮን ካሬ ኪሎ ሜትር ሲሆን በማዕከላዊ ስታቲስክስ የትንበያ መረጃ መሠረት የህዝብ ብዛቷ በ2009 የበጀት ዓመት 92.30 ሚሊዮን ደርሷል።

የኢትዮጵያ መንግስት እ.ኤ.አ. ከ2000 እስከ 2015 በሥራ ላይ የዋለውን ዓለም አቀፍ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች አጀንዳ ከሀገሪቱ የልማት ማዕቀፎች ጋር በማስተሳሰርና በበጀት በመደገፍ አጠቃላይ ሀገራዊ እና የሴክተር ፖሊሲዎቹንና ስትራቴጂዎችን ለማስፈፀም ከፌዴራል እስከ ክልል በዘረጋቸው አሠራሮች፣ አደረጃጀቶች እና በአሰማራው የሰው ኃይል፣ ሁሉንም የልማት ኃይሎችን አስተባብሮ በመምራት እና አፈፃፀሙን በቅርብ ተከታትሎ በመደገፍ ስኬታማ ውጤቶች አስመዝግቧል።፡ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች አፈፃፀም በሀገር አቀፍ ደረጃ በመገምገም መልካም ተሞክሮዎችን እና ፈተናዎችን ለይቷል። አጠቃላይ የግምገማ ግኝቶችንም ለዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 ዝግጅት ግብዓት እንዲሆኑ በተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም የኢትዮጵያ ጽ/ቤት አማካኝነት ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት አካፍሏል።

የኢትዮጵያ መንግስት በዚህ የዳበረ ልምድና መልካም ተሞክሮ ላይ በመመሥረት የዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030ን የተባበሩት መንግስታት አባል ሀገራት መሪዎች እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 25-27 ቀን 2015 በኒዮርክ ባደረጉት ስብሰባ ተቀብሎ ተፈፃሚ ለማድረግ ቃል ገብቷል። በዚህም መሠረት መንግስት የዘላቂ ልማት ግቦችን በባለቤትነት በመውሰድና የሀገራችን የልማት ማዕቀፍ በማድረግ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፀድቆ ወደ ትግበራ ገብቷል። የኢትዮጵያ መንግስት ከተባበሩት መንግስታት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ካውንስል (ECOSOC) እ.ኤ.አ. ኦገስት 2016 የዘላቂ ልማት ግቦች የ2017 የፈቃደኝነት ግምገማ እንዲያካሄድ በቀረበለት ጥያቄ መሠረት ጥያቄውን ተቀብሎ ወደ ግምገማ ገብቷል።

የኢትዮጵያ የ2017 የዘላቂ ልማት ግቦች የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ ዋና ዋና ዓለማዎች ሁለት ሲሆኑ እነዚህም (1) የዘላቂ ልማት ግቦችን የዝግጅት እና የትግበራ ሂደት በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በመገምገም ጥንካሬዎችን፣ ክፍተቶችን፣ ፈታናዎችን እና መልካም አጋጣሚዎችን በግልፅ ለይቶ ያስቀመጠ የግምገማ ሪፖርት ማዘጋጀት (2) ሀገር-አቀፍ የፈቃደኝነት ግምገማ ሪፖርቱን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ማስፀደቅ፣ የፀደቀውን ሀገር-አቀፍ የፈቃደኝነት የግምገማ ሪፖርት ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት የኢኮኖሚና የማህበራዊ ካውንስል (ECOSOC) ማቅረብ፣ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከፍተኛ የፖለቲካ መድረክ (High Level Political Forum of the United Nations, HLPF) ስብሰባ ላይ በአካል በመገኘት በግምገማ ሪፖርቱ ላይ ገለፃና ማብራሪያ መስጠት እና ከመድረኩ ጠቃሚ ግበረ-መልሶችን መውሰድ ናቸው።

የዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 ህዝቦችን ከድህነትና ከረሀብ ለማላቀቅ፣ መሬትን ከጥፋት ለመታደግ እና የሰው ልጆችን የተሟላ ኑሮና ብልፅግና ለማረጋገጥ በምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች አፈፃፀም እና በሪዮ +20 ስኬቶች ላይ በመመሥረት የተዘጋጀ ነው። የዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 የማይነጣጠሉና ሁሉን አቀፍ (Universal) ባህሪያት ያሏቸው 17 ግቦችን (Goals) እና 169 ኢላማዎችን (Targets) ያካተተ ሲሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ የዘላቂ ልማት ግቦች ኢላማዎችን

አፈፃፀም ለመከታተልና ለመገምገም ጥቅል ስምምነት የተደረሰባቸው 230 አመልካቾችም ይፋ ተደርገዋል፡፡ የዘላቂ ልማት ግቦች አፈፃፀም ግምገማ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ሲሆን በየሀገራቱ መንግስታት የሚመራ፣ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት የሚያሳትፍ እና በሀገር፣ በአህጉር እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄድ ነው።

የኢትዮጵያ መንግስት ከተባበሩት መንግስታት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ካውንስል የቀረበለትን የ2017 የፈቃደኝነት ግምገማ በብቃት ለመወጣት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን አከናውኗል። በዚህም መሠረት የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማውን በሀገር አቀፍና በክልሎች ደረጃ ለመምራትና ለማስተባበር የሚያግዙ ዝርዝር የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ የመነሻ ሀሳብ ሰነድ (Concep Note) እና የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ ማገናዘቢያ (Checklist) በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው መንግስት አስፈፃሚዎች እና ለብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን የህዝብ ክንፍ በወቅቱ ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርጓል።

የ2017 የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማውን በሴክተር እና በማክሮ ደረጃ የሚመሩና የሚያስተባብሩ የመንግስት አስፈፃሚ አካላትን በመለየት በግምገማው የመነሻ ሀሳብ እና በማገናዘቢያ ሰነዶች ላይ በሁለት ደረጃዎች የተከፈሉ (በስትራቴጂክ ደረጃ እና በቴክኒክ ደረጃ) የምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት በፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማው ዓላማና አስፈላጊነት፣ በግምገማው የመረጃ ምንጮች፣ በግምገማው ዘዴዎችና ዋና ዋና ሂደቶች፣ በግምገማው ይዘቶችና የአቀራረብ ፎርማት እና በግምገማ ሪፖርት ማቅረቢያ የጊዜ ሠሌዳ ዙሪያ ውይይቶችን በማካሄድ የጋራ ግንዛቤ እንዲያዝ ተደርጓል። የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴርም በቀረበለት የበጀት ጥያቄ መሠረት የግምገማ ሥራውን ለማስፈፀም በጀት ፈቅዶ ወደ ሥራ ተገብቷል።

የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማውን በተመለከተ ከሚመለከታቸው የመንግስት አስፈፃሚ አካላት ጋር በተያዘው የጋራ ግንዛቤ መሠረት የሚመለከታቸው የመንግስት የሴክተር አስፈፃሚ መ/ቤቶች ባለሙያዎችን መድበው የግምገማ ሥራውን እንዲያከናውኑ ተደርጓል። ይህንኑ የግምገማ ሥራ በየደረጃው የሚያስተባብር እና የግምገማ ሪፖርቶችን የሚያጠናቅር የሥራ ቡድን በብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን ደረጃ በማቋቋም በሚመለከታቸው የመንግስት የሴክተር አስፈፃሚ መ/ቤቶች የተዘጋጁ የግምገማ ሪፖርቶች ለብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን እንዲቀርቡ ተደርጓል። በዚህም መሠረት ረቂቅ ሀገራዊ የግምገማ ሪፖርት በብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን ተዘጋጅቶ በክልሎች፣ በከተማ አስተዳደሮች እና በፌዴራል ደረጃ ባለድርሻ አካላትን ያሳተፉ ምክክሮች ተካሂደዋል። ከምክክሮቹ የተገኙ ጠቃሚ ሀሳቦችና አስተያየቶች በመጨረሻ መልኩ በተዘጋጀው ረቂቅ ሀገራዊ የግምገማ ሪፖርት እንዲካተቱ ተደርጓል።

የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ ሪፖርቱ የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሀገር አቀፍ የልማት ማዕቀፍ ጋር ከማስተሳሰር ጀምሮ በትግበራ ሂደት የታዩ ጥንካሬዎችን፣ ክፍተቶችን፣ ያጋጠሙ ፈተናዎችን፣ ቀጣይ ዕርምጃዎች እና መልካም አጋጣሚዎችን ለይቷል። ረቂቅ ሪፖርቱ መግቢያውን ጨምሮ በ13 ክፍሎች የተደራጀ ሲሆን እነዚህም ክፍል 2 የግምገማ ዘዴዎችና ሂደቶች፣ ክፍል 3 ፖሊሲዎችና አስቻይ ሁኔታዎች፣ ክፍል 4 የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሀገራዊ የልማት ማዕቀፍ ጋር ማስተሳሰር፣ ክፍል 5 ሶስቱን የዘላቂ ልማት ገጽታዎች ማስተሳሰር፣ ክፍል 6 ግቦችና ኢላማዎች፣ ክፍል 7 የዘላቂ ልማት ግቦች ትግበራ፣ ክፍል 8 የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈፀሚያ ተቋማዊ አደረጃጀቶች፣ ክፍል 9 የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈፀሚያ ዘዴዎች፣ ክፍል 10 የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማስፈፀም ቀጣይ እርምጃዎች፣ ክፍል 11 ክትትል፣ ሪፖርትና ግምገማ፣ ክፍል 12 ማጠቃለያ እና ክፍል 13 የስታቲስቲክስ አባሪዎች ናቸው።

ይህ የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ ረቂቅ ሪፖርት በክልል፣ በከተማ አስተዳደር እና በፌዴራል ደረጃ በተዘጋጁ የምክክር መድረኮች ባለድርሻ አካላት (የመንግስት ተቋማት፣ የግሉ ዘርፍ ማህበራት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት፣ የአካል ጉዳተኞች ማህበራት፣ የሙያ ማህበራት፣ የሴቶች ማህበራት፣ የወጣቶች ማህበራት፣ አርሶ-አርብቶ አደሮች፣ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ የልማት አጋሮች) በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲሳተፉ በማድረግ እና የተገኙ ግብዓቶችን በማካተት በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲፀድቅ ቀርቧል።

# 2. የግምገማ ዘዴዎች እና ሂደቶች

## 2.1. የግምገማ ዘዴዎች

የዘላቂ ልማት ግቦችን አፈፃፀም በተመለከተ ኦፊሴላዊ የናሙና ጥናት/የቆጠራ እና የአስተዳደራዊ መዛግብት መረጃዎችን ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ እና አግባብ ካላቸው የመንግስት አስፈፃሚ ተቋማት ማሰባሰብ፣ ማደራጀት፣ መተንተንና ለ2017 የፈቃደኝነት ብሄራዊ ግምገማ ሪፖርት ዝግጅት በግብዓትነት መጠቀም በዚህ የግምገማ ሂደት ሥራ ላይ ከዋሉት ዘዴዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በመረጃዎች የአሰባሰብ ሂደት በሀገር አቀፍና በክልሎች/በከተማ አስተዳደሮች ደረጃ የተሰበሰቡ መረጃዎች ምንጮች የማይጣረዙ እንዲሆኑ በሁሉም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ወጥነት ያላቸው ሥራዎች ተከናውነዋል። ከዚህ በተጨማሪ የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማው በተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ ሪፖርት አቀራረብ የጋራ መመሪያ መሠረት ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በተወካዮቻቸው አማካኝነት በማሳተፍ የተካሄደ ሲሆን የግምገማ ሪፖርቱም የመመሪያውን ዋና ዋና ይዘቶች በተሟላ ሁኔታ እንዲያካትት ተደርጓል።

በዚህም መሠረት ከዘላቂ ልማት አንፃር ለአጠቃላይ የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ ግብዓት የሚሆኑና የሀገራችንን የፖሊሲ አቅጣጫዎችና አስቻይ ሁኔታዎች፣ ተቋማዊ የማስተባበሪያ መንገዶች፣ የማስፈፀሚያ ስልቶች፣ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማን የሚመለከቱ መረጃዎችን የማሰባሰብ፣ የማደራጀት ሥራ ተሠርቷል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ለ2017 ከተመረጠው ዋና የግምገማ ርዕስ እንዲሁም ከዋናው የግምገማ ርዕስ ጋር ተመጋጋቢነት ባላቸው እና ዝርዝር የ2017 የፈቃደኝነት ብሄራዊ ግምገማ በተካሄደባቸው የዘላቂ ልማት ግቦች (ግብ 1፡ ድህነትን ማጥፋት፣ ግብ 2፡ ረሀብን ማጥፋት፣ ግብ 3፡ ጤናማ ህይወትና ደህንነት፣ ግብ 5፡ የሥርዓተ-ፆታ ዕኩልነት፣ ግብ 9፡ የኢንዱስትሪ ፈጠራና መሠረተ-ልማት፣ ግብ 14፡ የውሀ ሥነ-ምህዳርን ለዘላቂ ልማት መጠበቅ እና ግብ 17 ዓለም አቀፍ ትብብር ለዘላቂ ልማት) አፈፃፀም ዙሪያ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ተሰባስበው ለግምገማ ግብዓት እንዲሆኑ ተደርጓል።

በዘላቂ ልማት ግቦች የ2017 የፈቃደኝነት ግምገማ ላይ በዘጠኙ ክልሎች፣ በሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች እና በፌዴራል ደረጃ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተወካዮች ባሳተፈ አግባብ በተካሄዱ ምክክሮች የ2017 የፈቃደኝነት ብሄራዊ ግምገማን በተመለከተ ተመሳሳይ የውይይት መነሻ ሀሳቦች ተዘጋጅተው እንዲቀርቡ ተደርጓል። ከተካሄዱ ምክክሮች የተገኙ ግብረ-መልሶችም በክልሎች፣ በከተማ አስተዳደሮች እና በፌዴራል ደረጃ ወጥ የሆኑ የጋራ የመረጃ ምንጮች ነበሩ። በአጠቃላይ መረጃዎችን በሚመለከት በሀገር አቀፍና በክልሎች፣ በከተማ አስተዳደሮች እና በፌዴራል ደረጃ የተካሄዱ የ2017 የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማዎች ተመሳሳይ የመረጃ ምንጮችን እንዲጠቀሙ በመደረጋቸው በሀገር አቀፍ፣ በፌዴራል፣ በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች ደረጃ ከዘላቂ ልማት ግቦች ጋር የተያያዙ ግንዛቤዎች እንዲሁም የተለያዩ መረጃዎች በወጥነት እንዲያዙ ማድረግ ተችሏል።

## 2.2. የግምገማ ሂደቶች

በሀገራችን የ2017 የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ የዘላቂ ልማት ግቦች የቅድመ-ዝግጅት፣ የዝግጅት እና የትግበራ አፈፃፀም ሂደቶች ተዳስሰዋል። ከቅድመ-ዝግጅት አኳያ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች አፈፃፀም በሀገር አቀፍ ደረጃ በመገምገም ለዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 ዝግጅት ግብዓት አስተዋጽኦ መደረጉና በድህረ 2015 የልማት አጀንዳ የአፍሪካ የጋራ አቋም ሰነድ የዝግጅት ከፍተኛ ኮሚቴ አባልነት ከፍተኛ ተሳትፎና አስተዋጽኦ መደረጉ፣ የ2030 የዘላቂ ልማት አጀንዳን እንደ አባል ሀገር በመቀበል የማፅደቅ፣ የዘላቂ ልማት ግቦችን በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በባለቤትነት መያዝ፣ ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር የማስተሳሰር፣ የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት በሀገር-አቀፍ፣ በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች ደረጃ በተዘጋጁ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ረቂቅ ዕቅዶች ላይ በየደረጃው ሁሉም ባለድርሻ አካላት ግንዛቤ እንዲይዙ መደረጉ፣ ዕቅዶቹን በየደረጃው በመንግስት በማስፀደቅ በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ወደ ትግበራ የማስገባት እና የዕቅዶቹን ትግበራ በየደረጃው በቅርብ የመከታተልና የመደገፍ ሂደቶች በግምገማው ተዳስሰዋል። በዚህም መሠረት ዝርዝር የግምገማ ሂደቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 2.2.1. ለዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 ዝግጅት የኢትዮጵያ አስተዋፅኦ

ኢትዮጵያ በምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች የትግበራ ሂደት ውጤታማ አፈፃፀም ካስመዘገቡ ጥቂት የአፍሪካ ሀገራት መካከል አንዷ ናት። ከስምንቱ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ውስጥ ስድስቱን መቶ በመቶ አሳክታለች። በቀሪዎቹ ሁለት ግቦችም አመርቂ ውጤቶች አስመዝግባለች። ከተቀመጡላቸው ዒላማዎች አኳያ ያልተደረሰባቸው ሁለት ግቦች (1) የሥርዓተ-ፆታ ዕኩልነትና ሴቶችን ማብቃት እና (2) የእናቶችን ጤና ማሻሻል ሲሆኑ የእነዚህ ሁለት ግቦች የአፈፃፀም መነሻዎች በጣም ዝቅተኛ በሚባል ደረጃ የነበሩ ናቸው። እነዚህን ሁለት ግቦች ወደሚፈለገው ውጤትና ስኬት ለማሸጋገር የሚመለከታቸውን አካላት አስተባብሮ በመምራት መንግስት በርካታ ጥረቶች ያደረገ ቢሆንም ከግቦቹ ጋር በተያያዙ ልማዳዊ ጎጂ አስተሳሰቦች፣ የተዛቡ አመለካከቶች እና የመሠረተ-ልማት ችግሮች ምክንያት ግቦቹን በሚጠበቀው ደረጃ ለማሳካት አልተቻለም።

በአጠቃላይ በምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ዙሪያ ሀገራችን ያስመዘገበቻቸውን መልካም ውጤቶች መሠረት በማድረግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለተዘጋጀው የዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 ዝግጅት የመረጃ ግብዓት አስተዋፅኦ እንድታደርግ በተባበሩት መንግሥታት ከተመረጡ 50 ሀገሮች መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ናት። በዚህም መሠረት የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች አፈፃፀም በተመለከተ በፌዴራል፣ በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች ደረጃ ከተዘጋጁና ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ካሳተፉ የግምገማ መድረኮች እንዲሁም ከናሙና ጥናት/ከቆጠራ እና ከአስተዳደራዊ መዛግብት መረጃዎችን በማሰባሰብ ለዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 ዝግጅት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ያካተተና ደረጃውን የጠበቀ ሀገር-አቀፍ የግምገማ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለተባበሩት መንግስታት እንዲቀርብ ተደርጓል።

ከዚህ በተጨማሪ ሀገራችን የአፍሪካ የድህረ 2015 የልማት አጀንዳ የጋራ አቋም "Common African Position on Post 2015 Development Agenda" በሚል መጠሪያ የሚታወቀውን ሰነድ ለማዘጋጀት 10 የአፍሪካ ህብረት ሀገራትን በአባልነት ይዞ በተደራጀው ከፍተኛ የዝግጅት ኮሚቴ አባል በመሆን ለሰነዱ ዝግጅት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጋለች። የኢትዮጵያ መንግስት በዝግጅቱ ወቅት ስኬታማ በሆነ የአመራር ጥበብና ድርድር ሰዎችን ማዕከል ያደረገ ሁሉን አቀፍ ተቋማዊ ለውጥ ለልማት (Structural Transformation for Inclusive and People Centered Development) የሚል ሀሳብ በማቅረብና በአዘጋጅ ኮሚቴው ተቀባይነት እንዲያገኝ በማድረግ ሀሳቡ በድህረ 2015 የልማት አጀንዳ የአፍሪካ የጋራ አቋም ከተቀመጡ መሠረታዊ አቅጣጫዎች (Strategic Pillars) መካከል አንዱ እንዲሆንና በአፍሪካ ህብረት ሀገራት መሪዎች እንዲፀድቅ ተደርጓል። የድህረ 2015 የአፍሪካ የልማት አጀንዳ የጋራ አቋም ሰነድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለተዘጋጀውና አሁን በትግበራ ላይ ለሚገኘው የዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 ዝግጅት ትርጉም ያለው አስተዋፅኦ እንደነበረው ይታመናል።

### 2.2.2. የ2030 የዘላቂ ልማት አጀንዳን በባለቤትነት መያዝ

የኢትዮጵያ መንግስት የዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030ን እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 25-27 ቀን 2015 ዓ.ም. የተባበሩት መንግስታት አባል ሀገራት መሪዎች በኒዮርክ ባደረጉት ስብሰባ ተቀብሎ አፅድቋል። በዚህም መሠረት የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር በማስተሳሰር፣ በመንግስት መሪነትና አስተባባሪነት በዕቅዱ የዝግጅት ሂደት ላይ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በቀጥታና በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲሳተፉ፣ ረቂቅ ዕቅዱን በሀሳቦቻቸውና በአስተያየቶቻቸው እንዲያዳብሩ፣ በዕቅዱ ዓላማ እና ዋና ዋና ግቦች ላይ የጋራ ግንዛቤ እንዲጨብጡ እና ዕቅዱን በባለቤትነት ይዘው በትግበራ ሂደቱ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ በፌዴራል እና በክልሎች/በከተማ አስተዳደሮች ደረጃ ሰፊ ምክክሮች ተደርገዋል። በተደረጉ ሰፊ ምክክሮችም የጋራ ግንዛቤዎችና እና የጋራ የባለቤትነት ስሜት ተፈጥሯል። የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት በተዘጋጀው የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ረቂቅ ዕቅድ ላይ በተዘጋጁ የውይይት መድረኮች በቂ ጊዜ ወስደው ተሳትፎ ያደረጉ የባለድርሻ አካላት ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች የተወከሉ ናቸው።

የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ስብጥር ሲታይም በክልል ደረጃ የአርሶ-አርብቶ አደሮች ተወካዮች፣ የወጣቶች አደረጃጀት ተወካዮች፣ የሴቶች አደረጃጀት ተወካዮች፣ የንግዱ

ማህበረሰብ ተወካዮች እና የምሁራን ተወካዮች የተሳተፉ ሲሆን በፌዴራል ደረጃ የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ተወካዮች፣ የኃይማኖት ተቋማት ተወካዮች፣ የሲቪል ማህበረሰብና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የምርምር ተቋማትና የሙያ ማህበራት ተወካዮች፣ የወጣቶች አደራጃጀት ተወካዮች፣ የሴቶች አደረጃጀት ተወካዮች፣ የግሉ ዘርፍ ማህበራት ተወካዮች፣ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ተወካዮች፣ የልማት አጋሮች ተወካዮች ተሳትፈዋል። ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ እና የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት የተዘጋጀው የሁለተኛው ሀገራዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በመጀመሪያ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀጥሎም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀድቆ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወደ ትግበራ ገብቷል።

በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች ደረጃም የየአካባቢዎችን ተጨባጭ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ያስገቡና ከሁለተኛው ሀገራዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ተመጋጋቢ የሆኑ እንዲሁም የዘላቂ ልማት ግቦችን ያካተቱ ዕቅዶች ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ባሳተፈ አግባብ ተዘጋጅተው በመጀመሪያ በክልሎች ካቢኔዎች ቀጥለውም በክልሎች ምክር ቤቶች ፀድቀው ወደ ትግበራ ተገብቷል። በመሆኑም የዘላቂ ልማት ግቦችን በተመለከተ በሀገር አቀፍ፣ በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች ደረጃ ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር በተሳሰረ ሁኔታ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የጋራ ግንዛቤ እና የጋራ ባለቤትነት ይዘው ወደ ትግበራ የገቡበት ሁኔታ እንዳለ እ.ኤ.አ. ኖቬምበር 2016 ዓ.ም. ከተባበሩት መንግስታት የኢትዮጵያ ቡድን ጋር በመተባበር በሶስት የውይይት ማዕከላት ከሁሉም ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች የቢሮ ኃላፊዎች እና የሲቪል ማህበረሰብ ተወካዮች ጋር በተደረጉ ምክክሮች ለማረጋገጥ ተችሏል። ይህ መልካም ጅምር በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።

በአጠቃላይ የዘላቂ ልማት ግቦችን በባለቤትነት ይዞ ተፈፃሚ ከማድረግ አንፃር የኢትዮጵያ መንግስት ከፍተኛ ቁርጠኝነትና ዝግጁነት አለው። ይህንንም ቁርጠኝነትና ዝግጁነት ሁሉም የልማት ኃይሎች (ፓርቲ፣ መንግስትና ህዝብ) በተለያዩ የመንግስት አስተዳደር ዕርከኖች በግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ዕምነትና ባለቤትነት ይዘው በተቀናጀና በተደራጀ አግባብ መፈፀም ጀምረዋል። የዘላቂ ልማት ግቦችን ተፈጻሚ ከማድረግ አኳያ አስገዳጅ ህግ ባይኖርም የኢትዮጵያ መንግስት በዓለም አቀፍ ደረጃ የገባውን ቃል በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ወደ ተጨባጭ ተግባር ለማሸጋገር የዘላቂ ልማት ግቦችን የሁለተኛው ሀገራዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አካል በማድረግ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (በፓርላማ) አስፀድቆ የዕቅዱ ተፈፃሚነት በሀገር-አቀፍ ደረጃ የህግ አስገዳጅነት እንዲኖረው አድርጓል። ይህ እርምጃ የኢትዮጵያ መንግስት የልማት ኃይሎችን አስተባብሮ በመምራት በትግበራ ሂደት ውስጥ ያስገባቸውን የዘላቂ ልማት ግቦች በከፍተኛ ቁርጠኝነት እና ሀገራዊ ባለቤትነት መያዙን በግልፅ ያሳያል።

### 2.2.3. የ2030 የዘላቂ ልማት አጀንዳን በሁሉም ባለድርሻ አካላት ተፈፃሚ ማድረግ

ከፍ ብሎ ለመግለፅ እንደተሞከረው የኢትዮጵያ መንግስት የዘላቂ ልማት ግቦችን በከፍተኛ ቁርጠኝነት እና ሀገራዊ ባለቤትነት ይዞ ሁሉንም የልማት ኃይሎች አስተባብሮ በመምራት የዘላቂ ልማት ግቦችን ያካተተ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አዘጋጅቶና በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፀድቆ ከ2008-2012 ባሉት የበጀት ዓመታት ሥራ ላይ ለማዋል ወደ ትግበራ ገብቷል። በየዓመቱ በመንግስት የሚመደበው የካፒታልና የመደበኛ በጀት ይህንኑ ዕቅድ የሚያስፈፅም ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ የዘላቂ ልማት ግቦችን የትግበራ ሂደት ለማፋጠን በየዓመቱ ብር 12 ቢሊዮን ወጪ እያደረገ ይገኛል። የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት ተዘጋጅቶና በመንግስት ፀድቆ በትግበራ ላይ ካለው የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውጭ በትይዩ (In Parallel) የሚዘጋጅና ሥራ ላይ የሚውል ዕቅድም ሆነ በጀት የለም። በሀራችን ልማትን ለማፋጠን የሚታሰቡ ሁሉም ዕቅዶች ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተመነዘሩ መሆን ይጠበቅባቸዋል። በመሆኑም ሁሉም ባለድርሻ አካላት በየተሠማሩበት የልማት መስክ የሚያከናውኗቸው የልማት ሥራዎች የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት ከተዘጋጀውና በመንግስት ፀድቆ በትግበራ ላይ ከሚገኘው የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተመነዘሩ ናቸው። በዚህም መሠረት ባለድርሻ

አካላት ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ተሳስረው የተዘጋጁትን የዘላቂ ልማት ግቦች በየተሰማሩበት የልማት መስክ በመንግስት መሪነትና አስተባበሪነት ተፈፃሚ በማድረግ ላይ ናቸው።

አጠቃላይ ሀገራዊና የሴክተር እንዲሁም የክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ተፈፃሚ ለማድረግ መንግስት በተለያዩ የአስተዳደር ዕርከኖች የዘረጋቸው ተቋማዊ አሠራሮች፣ አደረጃጀቶች እና የዘላቂ የልማት ግቦችን በማካተት አዘጋጅቶ ወደ ትግበራ ያስገባው ሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ለመሥራት ዋና የማስተባበሪያ መንገዶች ናቸው። በመሆኑም እያንዳንዱ የመንግስት አስፈፃሚ አካል የሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እና የዘላቂ ልማት ግቦችን ከማስፈፀምና ከመፈፀም አንፃር ባለድርሻ አካላትን አስተባብሮ በመምራት በዕቅዱ የትግበራ ሂደት ውስጥ በሰፊው እንዲሳተፉ ከሚያደርጋቸው የልማት ኃይሎች መካከል አንዱና ዋናው የህዝብ ክንፍ ነው።

የህዝብ ክንፍ የእያንዳንዱን የመንግስት አስፈፃሚ አካል ኃላፊነት መሠረት በማድረግ የሥራ አግባብነት ያላቸው የተለያዩ ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት ልማታዊ የጋራ የውይይት መድረክ ሲሆን የግሉን ዘርፍ፣ የሲቪል ማህበረሰቡን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ የሙያ ማህበራትን፣ የሴቶችና የወጣቶች አደረጃጀቶችን፣ አርሶ-አርብቶ አደሮችን...ወዘተ ያካትታል። በህዝብ ክንፍ ልማታዊ የጋራ የምክክር መድረክ እንደየአግባቡ ከዕቅድ ዝግጅት እስከ አፈፃፀም በመንግስትና በህዝብ ክንፉ የተከናወኑ የልማት ሥራዎች በየሩብ ዓመቱ ይገመገማሉ፣ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ይለያሉ፣ በቀጣይ መከናወን ያለባቸው የልማት ሥራዎች ተለይተው የጋራ ውሳኔ ይሰጥባቸዋል። ይህም የዘላቂ ልማት ግቦችን በባለድርሻ አካላት እንዲፈፀሙ ከማድረግ አኳያ ከፍተኛ አስተዋኦ አለው።

የልማት አጋሮችም በዕቅድ የዝግጅት ሂደት ተሳትፎ በማድረግ፣ የዕቅዱን አፈፃፀም በእያንዳንዱ ሴክተር በቴክኒካል የሥራ ቡድን (Technical Working Group) ተደራጅተው በየጊዜው በመከታተልና አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት እንዲሁም በየዓመቱ በመንግስት በሚዘጋጅ የግምገማ መድረክ የዕቅዱን አፈፃፀም በመገምገም ጠቃሚ ግብረ-መልሶች በመስጠትና እና ቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን በሚመለከት የዘላቂ ልማት ግቦች ስኬታማ ሆነው እንዲፈፀሙ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ያደርጋሉ።

የዘላቂ ግቦችን በተመለከተ ለባለድርሻ አካላት በየደረጃው ግንዛቤ የማስጨበጥና ባለቤትነት የመፍጠር ሥራ የአንድ ወቅት እንቅስቃሴ ብቻ ሳይሆን በቀጣዮቹ የትግበራ ዘመናትም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። በዚህም መሠረት ቀደም ሲል ከተባበሩት መንግስታት የኢትዮጵያ ቡድን ጋር በመተባበር ከሁሉም የሀገሪቱ ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የተለያዩ የቢሮ ኃላፊዎችን እና የሲቪል ማህበረሰብ ተወካዮችን በተመረጡ ማዕከላት መድረኮችን በማዘጋጀት በዘላቂ ልማት ግቦች ላይ የተጀመሩ ግንዛቤ የማስጨበጥና ባለቤትነት የመፍጠር ዓውደ ጥናቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ይደረጋል።

በአጠቃላይ የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት እና ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ የኢትዮጵያ መንግስት ያዘጋጀውና በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፀድቆ በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በሥራ ላይ ያዋለው የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሀገራዊ በመሆኑ በትግበራ ሂደቱ ሁሉም ባለድርሻ አካላት እየተሳተፉበት ነው። መንግስት በዘረጋቸው ተቋማዊ አሠራሮች እና አደረጃጀቶች መሠረት የባለድርሻ አካላትን አስተባብሮ በመምራት በዕቅዱ የትግበራ እና የክትትልና ግምገማ ሂደት የተደራጀና የተቀናጀ ተሳትፎ እንዲያደርጉ በየደረጃው ጥረቱን አጠናክሮ ይቀጥላል። ከዚህ አንፃር በተለያዩ የአስተዳደር ዕርከኖች የመንግስት አስፈፃሚ አካላት በህግ የተሰጣቸውን ሥልጣን እና ተግባራት መሠረት በማድረግ በሚያከናውኗቸው የልማት ሥራዎች አግባብነት ያላቸው ባለድርሻ አካላትን በመለየት፣ በህዝብ ክንፍ በማደራጀት እና በዘላቂ ልማት ግቦች የትግበራ፣ የክትትልና ግምገማ ሂደት በላቀ ደረጃ በማሳተፍ የአመራርና የማስተባበር ሚናቸውን ለመወጣት ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

# 3. ፖሊሲዎችና አስቻይ ሁኔታዎች

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ቃል-ኪዳን መገለጫ ነው። ህገ መንግስቱ አንድ የጋራ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ እና አንድ የጋራ ሀገር የመገንባት ዓላማ አለው። ከዚህ በተጨማሪ በኢኮኖሚ ልማት፣ በማህበራዊ ልማት፣ በአካባቢ ልማት እና በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ለህዝቦች ቀጥተኛ ተሳትፎ የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር (ለታችኛዎቹ የአስተዳደር ዕርከኖች በቂ ሥልጣን ለመስጠት) ያልተማከለ አስተዳደር መከተል ህገ-መንግስታዊ ግዴታ ነው።

የኢትዮጵያ መንግስት አጠቃላይ ሀገራዊ የፖሊሲ አቅጣጫዎች በህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ላይ የተመሠረቱ ሲሆኑ ህዝቡ በየደረጃው ዕኩል ተሳታፊና ፍትሀዊ ተጠቃሚ የሚሆንባቸውን የኢኮኖሚና የማህበራዊ ልማቶች የሚያረጋግጡ፣ ድህነትን በማጥፋት እና በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ላይ ያተኮሩ ናቸው። የክልል መንግስታትና የከተማ አስተዳደሮች በአጠቃላይ ሀገራዊ የፖሊሲ ማዕቀፎች ውስጥ ሆነው ከየአካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር የሚጣጣሙ ዝርዝር ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ዕቅዶችን እና ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ተፈፃሚ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው። ይህንን ኃላፊነትም በተጨባጭ እየተወጡ ይገኛሉ።

ከፍ ብሎ ለመግለፅ እንደተሞከረው የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ በገበያ መርህ ላይ በተመሠረተና ባልተማከለ የኢኮኖሚ አስተዳደር ሥርዓት በተለያዩ ደረጃዎች ህዝቦችን በማሳተፍ በመንግስት ተዘጋጅተው በሥራ ላይ የዋሉ አጠቃላይ ሀገራዊ የልማት ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች አንድ የጋራ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ እና አንድ የጋራ ሀገር የመገንባት ዓላማ ያላቸው ናቸው። ፖሊሲዎቹ በዋነኛነት ጠንካራ ሀገራዊ ኢኮኖሚ በመገንባት የዜጎችን የልማት ተጠቃሚነት የማረጋገጥ እና ድህነትን ከነሁሉም መገለጫዎቹ የማጥፋት አቅጣጫዎች የሚከተሉ ናቸው።

ኢትዮጵያ በምትከተለው ያልተማከለ የአስተዳደር ሥርዓት አጠቃላይ ሀገራዊ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በተለያዩ የመንግስት አስተዳደር ዕርከኖች ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም አሟልቶ መፈፀም አንድ የጋራ ኢኮኖሚ ማህበረሰብ እና አንድ የጋራ ሀገር በመገንባት ሂደት ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ በአጠቃላይ ሀገራዊ ፖሊሲዎች እና ከየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተጣጥመው በክልል መንግስታትና በከተማ አስተዳደሮች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ በዋሉ ፖሊሲዎች መካከል የጠበቀ ትስስርና ተመጋጋቢነት አለ። በተመሳሳይ በሁሉም የመንግስት አስተዳደር ዕርከኖች በሥራ ላይ ያሉ የሴክተር ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ከአጠቃላይ ሀገራዊ ፖሊሲዎች እና በጐንዮሽ እርስ-በዕርስ ያላቸው ትስስር ጠንካራ ነው። በመሆኑም የዘላቂ ልማት ግቦችን በተለያዩ ደረጃዎች ተፈፃሚ ከማድረግ አኳያ በሥራ ላይ ያሉ ፖሊሲዎች ምቹ ናቸው።

የኢትዮጵያ መንግስት አጠቃላይ ሀገራዊና የሴክተር ፖሊሲዎችን እና ስትራቴጂዎችን እንዲሁም በአጠቃላይ ሀገራዊ እና የሴክተር ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ማዕቀፍ ውስጥ ከየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተጣጥመው የተዘጋጁ የክልል/የከተማ አስተዳደር ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ለማስፈፀም በየደረጃው ተቋማዊ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በመዘርጋት እና አስፈላጊውን የሰው ኃይል በመመደብ ሀገራችንን እ.ኤ.አ. በ2025 ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍ ሀገራዊ ራዕይ በማስቀመጥ ፈጣንና ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ የመሠረተ ልማት ግንባታ፣ የማህበራዊ ልማት እና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል። እነዚህ ተቋማዊ አሠራሮችና አደረጃጀቶች የዘላቂ ልማት ግቦችን ተፈፃሚ ለማድረግ የተሟሉና ምቹ ከመሆናቸውም በላይ አዳዲስ/ተጨማሪ ተቋማዊ አሠራሮችና አደረጃጀቶች እንደማያስፈልጉ የሚያመለክቱ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱ የመንግስት አስፈፃሚ አካል በህግ በተሠጠው ሥልጣንና ተግባራት ዙሪያ አግባብ ካላቸው የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ የሚሠራበት እና በዜጎች ቻርተር የሚመራ የህዝብ ክንፍ መድረክ በእያንዳንዱ የመንግስት መ/ቤት ተቋቁሟል። የህዝብ ክንፍ

መድረኩ በየሩብ ዓመቱ የጋራ ስብሰባዎችን በማካሄድ እና በጋራ የልማት ጉዳዮች ዙሪያ በመወያየት የጋራ ውሳኔ ያሳልፋል። ይህ አደረጃጀት የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት በተዘጋጀው የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ላይ ባለድርሻ አካላት በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው እና ዕቅዱን በባለቤትነት ይዘው እንዲፈፅሙት፣ አፈፃፀሙን በቅርብ በመከታተል እና በጋራ የህዝብ ክንፍ መድረክ በመገምገም ዕቅዱ ስኬታማ ሆኖ እንዲፈፀም የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ያርጋሉ።

ከፍ ብሎ በዝርዝር የተመለከቱና የኢትዮጵያን ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት መሠረት በማድረግ ተዘጋጅተው በሥራ ላይ ያሉ የኢትዮጵያ መንግስት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች፣ እንዲሁም እነዚህን ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ተፈፃሚ ለማድረግ የተዘረጉ ተቋማዊ አሠራሮችና አደረጃጀቶች የዘላቂ ልማት ግቦችን በተቀናጀና በተደራጀ አግባብ ተፈፃሚ ለማድረግ በኢትዮጵያ ውስጥ ምቹ ሁኔታዎች መኖራቸውን በግልፅ ያሳያሉ። መንግስት ሁሉንም የልማት ኃይሎች አስተባብሮ በመምራት እና ከፍ ብሎ በዝርዝር የተመለከቱትን አስቻይ ሁኔታዎች በተቀናጀና በተደራጀ አግባብ በመጠቀም የዘላቂ ልማት ግቦችን በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ተፈፃሚ ለማድረግ እየሠራ ይገኛል።

# 4. የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሀገራዊ ልማት ማዕቀፍ ጋር ማስተሳሰር

የዘላቂ ልማት ግቦችን ከኢትዮጵያ ሀገራዊ የልማት ማዕቀፎች ጋር ከማስተሳሰር አንፃር አመቺ የፖሊሲ ሁኔታዎች እንዳሉ ቀደም ብሎ ተገልጿል። የኢትዮጵያ መንግስት አጠቃላይ ሀገራዊና የሴክተር ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች እንዲሁም በአጠቃላይ ሀገራዊ እና የሴክተር ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎች ማዕቀፍ ውስጥ በሀገር አቀፍ እና ከየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተጣጥመው የተዘጋጁ የክልል እና የከተማ አስተዳደር ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና ዕቅዶችን ለማስፈፀም በየደረጃው የተዘረጉ ተቋማዊ አሠራሮችና አደረጃጀቶችም የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሀገራዊ እና ክልላዊ የልማት ማዕቀፎች ጋር ለማስተሳሰር ዋና የማስተባበሪያ መንገዶች ናቸው።

የዘላቂ ልማት ግቦች በዝግጅት ሂደት ላይ ያለው የረጅም ዘመን (የ15 ዓመት) ሀገራዊ የልማት ዕቅድ የመጀመሪያ ምዕራፍ በሆነው በሁለተኛው የአምስት ዓመት (2008-2012) የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እንደ አንድ መነሻ ተወስደው በልዩ የትኩረት መስኮች፣ በመሠረታዊ አቅጣጫዎች፣ በማክሮ-ኢኮኖሚ ዕቅድ፣ በማስፈፀሚያ ፋይናንስ ዕቅድ፣ በኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ ዕቅድ፣ በመሠረተ-ልማት ዘርፍ ዕቅድ፣ በሰው ኃብት ልማትና በቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ዕቅድ፣ በልማታዊ መልካም አስተዳደርና በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዕቅድ እና በባለ ብዙ ዘርፎች ዕቅድ እንደየአግባቡ ለማስተሳሰር ጥረቶች ተደርገዋል።

የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እንደ አንድ መነሻና የዝርዝር ዝግጅቱ አካል ተደርገው የታቀዱት የዘላቂ ልማት ግቦች በተለያዩ ደረጃዎች በተደረጉ ውይይቶች በሁሉም የልማት ኃይሎች የጋራ ግንዛቤ እንዲያዝባቸው አስፈላጊ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል። በሀገር አቀፍና በክልሎች ደረጃ ተመጋግበው ከተዘጋጁ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዶች ጋር ተሳስረው መታቀዳቸው እና በፌዴራል ደረጃ በሚኒስትሮች ምክር ቤትና በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሁም በክልሎች ደረጃ በየክልሎቹ ካቢኔዎች እና ምክር ቤቶች ፀድቀው እና በበጀት ተደግፈው በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ወደ ትግበራ መግባታቸው እና የዘላቂ ልማት ግቦችን ተፈፃሚ ለማድረግ ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውጪ በፌዴራልም ሆነ በክልሎች ደረጃ ሌላ ዕቅድና ሌላ በጀት አለመኖሩ የትስስሩ ሌላው መገለጫ ነው።

የ2030 የዘላቂ ልማት አጀንዳን እና የዘላቂ ልማት ግቦችን ከመፈፀም አኳያ ዓለም አቀፍ አስገዳጅ ህግ ባይቀመጥም የዘላቂ ልማት ግቦች ኢትዮጵያ ድህነትን ለማጥፋትና የዜጎችን ብልፅግና ለማረጋገጥ ሀገራችን የጀመረችውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት፣ መሠረተ-ልማት ማህበራዊ ልማት፣ የአካባቢ ልማት፣ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እና በአጠቃላይም የህዳሴ ጉዞ ለማፋጠን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው በመሆኑ የዘላቂ ልማት ግቦች የሀገራዊ የልማት ማዕቀፍ አካል ተደርገዋል። የዘላቂ ልማት ግቦችን በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ለመፈፀም በተለያዩ የመንግስት አስተዳደር ዕርከኖች የባለቤትነት መንፈስ መፍጠር የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችም ተከናውነዋል።

ከፍ ብሎ በተገለፀው መሠረት አዳዲስ ፖሊሲዎች፣ ተቋማዊ አሠራሮች እና አደረጃጀቶች ሳያስፈልግ ቀደም ብሎ በነበሩና አሁንም በሥራ ላይ ባሉ ፖሊሲዎች፣ አሠራሮችና አደረጃጀቶች የዘላቂ ልማት ግቦችና በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ተፈፃሚ ሊደረጉ የሚችሉ የዘላቂ ልማት ኢላማዎች ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር የጠበቀ ትስስር እንዲፈጥሩ እና ወደ ትግበራ እንዲሸጋገሩ ተደርጓል። ከዚህ አንፃር የዘላቂ ልማት ግቦች በዝግጅት ሂደት ላይ ያለው የረጅም ዘመን (የ15 ዓመት፡- 2008-2022) ሀገራዊ ዕቅድ የመጀመሪያ ምዕራፍ ከሆነው የሁለተኛው አምስት ዓመት (2008-2012) የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዋና የትኩረት መስኮች (Priority Areas) ጋር ያላቸው ትስስር በሚከተለው ሥዕል ቀርቧል።

## ሥዕል 1: የኢትዮጵያ ልማት የትኩረት መስኮች እና የዘላቂ ልማት ግቦች ትስስር

| ተ.ቁ. | የኢትዮጵያ ልማት የትኩረት መስኮች | የዘላቂ ልማት ግቦች |
|---|---|---|
| 1 | የግብርና ዘርፉ የሀገሪቱ ፈጣን ኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ | 1, 2, 6, 8, 9, 10, 12, 13, 14, 15, 17 |
| 2 | በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዕመርታ ማምጣትና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ማፋጠን | 1, 2, 4, 6, 8, 9, 10, 12, 17 |
| 3 | የኢኮኖሚው የማምረት አቅም ላይ ለመድረስ ቅልጥፍናን በመጨመር ለምርታማነት፣ ጥራትና ተወዳዳሪነት ልዩ ትኩረት መስጠት | 1, 2, 4, 7, 8, 9, 12, 15, 17 |
| 4 | በጠቅላላ ፍላጎትና በጠቅላላ አቅርቦት መካከል የሚታየውን የተዛባ ክፍተት ማስተካከል | 8, 10, 12, 17 |
| 5 | የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና የፕሮጀክቶች ማኔጅመንት አቅምን ማጎልበት | 8, 9, 11, 12, 17 |

| ተ.ቁ. | የኢትዮጵያ ልማት የትኩረት መስኮች | የዘላቂ ልማት ግቦች |
|---|---|---|
| 6 | ከከተማነት መስፋፋት ፈጣን ዕድገት፣ ኢንዱስትሪያላይዜሽንና መዋቅራዊ ለውጥ ጋር የተጣጣመ የከተማ አስተዳደርና አመራር መከተል |   |
| 7 | ለሀገር ውስጥ የግል ባለሀብቶች ትራንስፎርሜሽን ልዩ ትኩረት መስጠት |   |
| 8 | የሰው ኃብት ልማትን በቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ መደገፍ |   |
| 9 | ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት |   |
| 10 | የኪራይ ሰብሳቢነት ችግሮችን በመቅረፍ ልማታዊ የበላይነትን ማረጋገጥ |   |

የዘላቂ ልማት ግቦች ከፍ ብሎ በተገለፀው ሁኔታ ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር እንዲተሳሰሩ ተደርገው ዕቅዱ በመንግስት ከፀደቀ በኋላ በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በትግበራ ሂደት ላይ ይገኛሉ። የዘላቂ ልማት ግቦች እና የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ አፈፃፀምም በየደረጃው የቅርብ ክትትልና ድጋፍ እየተደረገለት ይገኛል። እያንዳንዱ የፌዴራልና የክልል የመንግስት አስፈፃሚ አካል የሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሠረት በማድረግ በየበጀት ዓመቱ ከዘላቂ ልማት ግቦች ጋር ትስስር ያለው ዝርዝር ዕቅድ በማዘጋጀት እና የማስፈፀሚያ በጀት በመመደብና በማስፀደቅ የትግበራ ሥራውን በየደረጃው በማከናወን ላይ ይገኛል። እንዲሁም የመንግስት አስፈፃሚ አካላት እንደ አግባቡ በአደራጇቸው የህዝብ ክንፎች (የግሉ ዘርፍ፣ የሲቪል ማህበረሰብ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አርሶ-አርብቶ አደሮች...ወዘተ) መድረኮች የዕቅዱን ትግበራ የሚያፋጥኑ የልማት ሥራዎች በጋራ በማከናወን ላይ ይገኛሉ።

ከፍ ብሎ ለመገለፅ እንደተሞከረው እስካሁን በተደረጉ የልማት እንቅስቃሴዎች የዘላቂ ልማት ግቦች በዝግጅት ሂደት ላይ ያለው የረጅም ዘመን (የ15 ዓመት) ሀገራዊ የልማት ዕቅድ የመጀመሪያ ምዕራፍ ከሆነው ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሠረታዊ አቅጣጫዎች እና የትኩረት መስኮች ጋር ተሳስረዋል። እነዚህ መሠረታዊ አቅጣጫዎችና የትኩረት መስኮች በረጅም ዘመኑ ሀገራዊ የልማት ዕቅድ የትግበራ ዘመን (እ.ኤ.አ. ከ2016-2030) ተጠናክረው የሚቀጥሉ ናቸው። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ተፈፃሚ ሊደረጉ የሚችሉ የዘላቂ ልማት ግቦች ኢላማዎችም (Targets) በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከማክሮ-ኢኮኖሚ፣ ከፋይናንሲንግ፣ ከኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ፣ ከመሠረተ ልማት ዘርፍ፣ ከሰው ሀብት ልማትና የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ፣ ከልማታዊ መልካም አስተዳደርና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እና ከባለብዙ ዘርፎች ልማት ኢላማዎች ጋር እንዲተሳሰሩ ተደርጓል።

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ተፈፃሚ የሚደረጉና ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር የተሳሰሩ ኢላማዎችን የአፈፃፀም ሂደት ለመከታተል የሚያስችሉ በሀገር አቀፍ ደረጃ የመረጃ ግኝቶችንና ፍሰቶችን መሠረት በማድረግ የተደራጁ ቀጥተኛና ወካይ (Proxy) አመልካቾች በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የፖሊሲ ማትሪክስ በግልፅ እንዲቀመጡ ተደርጓል። ለሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እና የዘላቂ የልማት ግቦች አፈፃፀም ክትትልና ሪፖርት ግብዓት የሚሆኑ አፊሴላዊ መረጃዎች የሚመነጩት ከመንግስት አስፈፃሚ አካላት አስተዳደራዊ መዛግብት (70 በመቶ) ሲሆን ቀሪዎቹ አፊሴላዊ መረጃዎች ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የናሙና ጥናት/ቆጠራ (30 በመቶ) ነው። ከዚህ በተጨማሪ ተዓማኒነት ካላቸው ምንጮች መረጃዎች በግብዓትነት ይወሰዳሉ። ከዚህ አንፃር ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተጣጥመው የማይሄዱትን ዓለማቀፍ አመልካቾች ከሀገራዊ አመልካቾች ለመለየት ዝርዝር ጥናቶች በሂደት ላይ ናቸው።

በአጠቃላይ የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሀገር አቀፍ እና ከክልሎች/ከከተማ አስተዳደሮች የልማት ማዕቀፎች ጋር በማስተሳሰር በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ ተፈፃሚ የማድረግ መልካም እንቅስቃሴዎች በጅምር ላይ ባሉ የረጅም ዘመን (2008-2022) ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ዝግጅት እና የዘላቂ ልማት ግቦች የማስፈፀሚያ ፋይናንስ ፍላጎት ጥናት ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ይደረጋል። የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሁለተኛው ሀገራዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር በማስተሳሰር ወደ ትግበራ ማሸጋገር መንግስት ኢትዮጵያን እ.ኤ.አ. በ2025 ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍ ያስቀመጠውን ሀገራዊ ራዕይ ለማሳካት፣ ድህነትን ለማጥፋትና በሀገራችን የተጀመረውን የትራንስፎርሜሽን እና የህዳሴ ጉዞ ለማፋጠን አስተዋፅኦው የጎላ ነው።

# 5. ሶስቱን የዘላቂ ልማት ገፅታዎች ማስተሳሰር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት በምዕራፍ 10 የብሔራዊ ፖሊሲ መርሆዎችንና ዓላማዎችን ይደነግጋል። በዚህም የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች፣ የማህበራዊ ነክ ዓላማዎች እና የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ ዓላማዎች በቅደም ተከተል በአንቀፅ 89፣ በአንቀፅ 90 እና በአንቀፅ 92 በግልፅ ተቀምጠዋል። አጠቃላይ ሀገራዊ ፖሊሲዎች እና በእነዚህ የፖሊሲ ማዕቀፎች ሥር ሆነው በየደረጃው ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥመው የተዘጋጁ የክልልና የሴክተር ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች እርስ-በዕርሳቸው ተመጋገቢነት ያላቸው ናቸው። በመሆኑም በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ከፖሊሲ አኳያ የኢኮኖሚ ልማት፣ የማህበራዊ ልማት እና የአካባቢ ልማት የተሳሰሩ ናቸው። የሀገሪቱ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂም ሶስቱን የዘላቂ ልማት ገፅታዎች በማስተሳሰር ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውል እየተደረገ ነው።

የሀገሪቱን ራዕይ፣ ሀገራዊና የሴክተር ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን፣ ኢትዮጵያ የተሰማማችባቸው ዓለም አቀፍ እና ክፍለ-አህጉራዊ የድህረ-2015 የልማት ግቦችን፣ ዓለም አቀፍ እና ከባቢያዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን እንደመነሻ በመውሰድ የተዘጋጀውና በመንግስት ፀድቆ በትግበራ ላይ የሚገኘው የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድም ሶስቱን የዘላቂ ልማት ገፅታዎች ያስተሳሰረ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያ መንግስት የፓሪሱን የአየር ንብረት ለውጥ ዓለም አቀፍ ስምምነት ከሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (በፓርላማ) አስፀድቆ የሀገሪቱ አስገዳጅ የህግ አካል አድርጓል። ይህም የሶስቱ የዘላቂ ልማት ገጽታዎች ትስስር ሌላው ማሳያ ነው።

በመሆኑም በኢትዮጵያ እየተካሄዱ ያሉ የልማት ሥራዎች ከፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች አንፃር ሶስቱን የልማት ገጽታዎች በማስተሳሰር እንዲፈፀሙ አቅጣጫዎች የተቀመጡላቸው ናቸው። ሆኖም እነዚህን የፖሊሲ አቅጣጫዎች ከመፈፀምና ከማስፈፀም አኳያ የአቅም ውስንነቶች ይታያሉ።

አጠቃላይ ሀገራዊ ፖሊሲዎችን እና በእነዚህ የፖሊሲ ማዕቀፎች ሥር ሆነው የተዘጋጁ የክልልና የሴክተር ፖሊሲዎችን በሚጠበቀው ደረጃ ከማስፈፀምና ከመፈፀም እንዲሁም ዘላቂ ልማትን ከማረጋገጥ አንፃር ግን በየደረጃው እና በየዘርፉ ሰፊ የልማታዊ አቅም ክፍተቶች ይስተዋላሉ። ከእነዚህ የልማታዊ አቅም ክፍተቶች መካከል በአስፈፃሚውና በፈፃሚው አካል የሚታዩ የአመለካከት ችግሮች፣ የልማታዊ ተነሳሽነትና ባለቤትነት ውስንነቶች እና ቀልጣፋ አገልግሎት አሰጣጥና የህዝብ አገልጋይነት ችግሮች ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ የቴክኒክ ዕውቀት ውስንነቶችም ይስተዋላሉ።

ከዚህ አንፃር ፖሊሲዎቹን በዝርዝር አውቆና ተረድቶ በየደረጃው ተፈፃሚ በማድረግ የሚፈለገውን ውጤት ለማረጋገጥ እና በአፈፃፀም ሂደት የፖሊሲ ክፍተቶች ካሉ እየተለዩ በበቂ መረጃዎች ላይ በመመሥረት በሚመለከተው አካል እንዲሞሉ የሚያስችሉ የሪፎርም ሥራዎች በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች እየተከናወኑ ናቸው። በመሆኑም ከሶስቱ የዘላቂ ልማት ገፅታዎች ጋር ተሳስረውና ተመጋግበው የተዘጋጁ አጠቃላይ ሀገራዊና ክልላዊ እንዲሁም የሴክተር ፖሊሲዎች የዘላቂ ልማት ግቦችን በአካተቱ የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዶች አማካኝነት በተደራጀ፣ በተቀናጀና ውጤታማ በሆነ አግባብ እንደሚፈፀሙ ።

# 6. ግቦችና ኢላማዎች

የዘላቂ ልማት ግቦችን በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ተፈፃሚ ለማድረግ የመንግስት ቁርጠኝነት ከፍተኛ ነው፡ ቁርጠኝነቱንም በተግባር እያረጋገጠ ይገኛል። የዘላቂ ልማት ግቦችን በባለቤትነት በመያዝ እና ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ግቦችንና ኢላማዎችን ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር እንዲተሳሰሩ አድርጓል። የዘላቂ ልማት ግቦችን በማስተሳሰር የተዘጋጀው የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀድቆ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች በትግበራ ላይ እንዲውል ተደርጓል። በዚህም መሠረት የዘላቂ ልማት ግቦችና የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ሂደት በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች የቅርብ ክትትልና ድጋፍ እየተደረገለት በሚጠበቀው ደረጃ እየተፈፀመ ነው።

የዘላቂ ልማት እና የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ግቦች ውህደት፣ አግባብነት ያላቸው ኢላማዎች ትስስር እና በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ የመረጃ ግኝቶችንና ፍሰቶችን መሠረት በማድረግ የተደራጁ ቀጥተኛና ወካይ (Proxy) አመልካቾች በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የፖሊሲ ማትሪክስ በግልፅ እንዲቀመጡ ተደርጓል። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ መደበኛ የመረጃ ፍሰት ያላቸውና በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጡ ኢላማዎችን አፈፃፀም ይለካሉ ተብለው የተመረጡ ቀጥተኛ እና ወካይ አመልካቾችና የአፈፃፀም መነሻዎች በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የፖሊሲ ማትሪክስ በዝርዝር ተቀምጠዋል።

በ2008 የበጀት ዓመት የዘላቂ ልማት ግቦች ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የዘርፎች የአፈፃፀም መርሀ-ግብሮች ጋር ተሳስረውና በመንግስት በጀት ተደግፈው በሁሉም የሀገሪችን አካባቢዎች ተፈፃሚ ተደርገዋል። በዚህም መሠረት በየዘርፉ መልካም የሚባሉ አፈፃፀሞች ተመዝግበዋል። ለምሳሌ ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ተሳስረው በበጀት ዓመቱ ተፈፃሚ በተደረጉ የዘላቂ ልማት ግቦች ዙሪያ ከተመዘገቡ የአፈፃፀም ውጤቶች መካከል የዘላቂ ልማት ግብ 4፣ ግብ 6 እና ግብ 7 አፈፃፀሞችን በማሳያነት መመልከት ይቻላል (አባሪ 13.1)።

ግብ 4፡ ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም ተደራሽነትን ማረጋገጥ፡- የትምህርት ተደራሽነትን በሚመለከት የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቅበላ በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 39 በመቶ (ወንድ 40 በመቶ፣ ሴት 38 በመቶ) በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 49.9 በመቶ (ወንድ 51.1 በመቶ፣ ሴት 48.6 በመቶ) አድጓል። ይህ አፈፃፀም መልካም የሚባል ሲሆን የሴቶችን ቅበላ ከወንዶች ጋር ለማመጣጠን ትኩረት ተሰጥቶ መሥራት እንዳለበት የሚያመላክት ነው። የመጀመሪያ ደረጃ (ከ1ኛ-8ኛ ክፍል) ትምህርት ቤቶች ቁጥር በ2007 የበጀት ዓመት 33,373 የደረሰ ሲሆን ንጥር ተሳትፎ በ2007 የበጀት ዓመት 96.9 በመቶ (ወንድ 100 በመቶ፤ ሴት 93.2 በመቶ) የነበረ ሲሆን በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 97.6 በመቶ (ወንድ 100 በመቶ፤ ሴት 93.74 በመቶ) ከፍ ብሏል። በበጀት ዓመቱ የተመዘገበው አፈፃፀም መጠነኛ ጭማሪ የታየበት ቢሆንም የሴቶችን ተሳትፎ ከወንዶች እኩል ከማድረግ አንፃር ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ አፈፃፀሙ ያሳያል። እንዲሁም የመጀመሪያ ደረጃ (1ኛ-8ኛ) ትምህርት የሥርዓተ-ፆታ ተሳትፎ አመልካች (Gender parity Index) በ2007 የበጀት ዓመት 0.93 የነበረ ሲሆን በ2008 የበጀት ዓመት 0.91 ዝቅ ብሏል። በአጠቃላይ ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ አንፃር እስካሁን የተመዘገቡ የአፈፃፀም ውጤቶች መልካም ሲሆኑ የሴቶችን ተሳትፎ ከማሳደግ አንፃር ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ መሥራት እንዳለበት የሚያመላክቱ ናቸው።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን በተመለከተ የመጀመሪያ ዕርከን (9-10 ክፍል) ትምህርት ጥቅል ተሣትፎን በ2007 የበጀት ዓመት ከነበረበት 39.8 በመቶ (ወንድ 41.3 በመቶ፤ ሴት 38.4 በመቶ) በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 44.8 በመቶ (ወንድ 46.2 በመቶ፤ ሴት 43.4 በመቶ)፣ የ2ኛ ደረጃ የመሰናዶ ትምህርት (11-12 ክፍል) ጥቅል ተሣትፎ በ2007 የበጀት ዓመት ከነበረበት 10.6 በመቶ (ወንድ 11.3 በመቶ፤ ሴት 9.9 በመቶ) በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 12.6 በመቶ (ወንድ 13.4 በመቶ፤ ሴት 11.7 በመቶ) ማድረስ ተችሏል። በሁለቱም ዕርከኖች የሴቶች ተሳትፎ ከወንዶች ዝቅ ያለ

እንደሆነ የአፈፃፀም ውጤቶች ያሳያሉ። ከእነዚህ የአፈፃፀም ውጤቶች በመነሳት በቀጣይ የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ ትርጉም ባለው ሁኔታ ለማሳደግ የተደራጀና የተቀናጀ ጥረት ይጠይቃል።

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን በተመለከተ እስከ 2008 በጀት ዓመት መጨረሻ በጠቅላላ 304,139 ዜጎች ሠልጥነው ወጥተዋል። እንዲሁም በበጀት ዓመቱ 131,097 ተማሪዎች በሥልጠና ላይ እንደነበሩ የአፈፃፀም መረጃዎች ያሳያሉ። የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ለውጥ ለማፋጠን እየተሠሩ ካሉ የልማት ሥራዎች አኳያ በጥሩ የአፈፃፀም ላይ የሚገኝ ሲሆን ተጠናክሮ እንዲቀጥል በመደረግ ላይ ነው። ከዚህ አኳያ የትምህርት ጥራቱንና የሠልጣኞችን ቁጥር ለማሳደግ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ይገኛል። በሌላ በኩል የከፍተኛ ትምህርት የቅድመ ምረቃ ጥቅል ተሳትፎ በ2007 የበጀት ዓመት ከነበረበት 729,028 (ሴቶች 35 በመቶ) በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 778,766 (ሴቶች 34 በመቶ) አድጓል።

ግብ 6፡ የንፁህ ውሀና የንጽህና አገልግሎትን ለሁሉም ተደራሽነት ማረጋገጥ፡- የውሀና ሳኒቴሽን ዘርፍ የልማት ዓላማ አስተማማኝ፣ ቀጣይነት ያለውና የንጹህ መጠጥ ውሀ አቅርቦትና የፍሳሽ አወጋገድ ሥርዓት ማቅረብ፣ ለኢንዱስትሪዎች ማስፋፊያ እና ለሰፋፊ የመስኖ እርሻዎች ልማት የግብዓት አገልግሎት መስጠት እና ህብረተሰቡን ያሳተፈ የተፋሰስ ልማትና እንክብከቤ በማካሄድ የውኃ ሀብት አካላትን ዘላቂ ጠቀሜታ እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። በ2008 የበጀት ዓመት የንፁህ መጠጥ ውሀና የንፅህና አገልግሎት በገጠርና በከተማ ለሚኖረው ህብረተሰብ ለማዳረስ የልማት ሥራዎች ተከናውነዋል። ከዚህ አንፃር በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ስታንዳርድ መሠረት የገጠር የንፁህ መጠጥ ውሀ አቅርቦት ሽፋን (በተሻሻሉ የውሀ ተቋማት) በ2007 ከነበረበት 59 በመቶ በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 61.1 በመቶ ከፍ ብሏል። በተመሳሳይ የከተማ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን (በቧንባ) በ2007 ከነበረበት 51 በመቶ በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 52.5 በመቶ ከፍ ያለ ሲሆን አጠቃላይ ሀገራዊ የንፁህ መጠጥ ውሀ አቅርቦት ሽፋን (በገጠርና በተማ) በ2007 ከነበረበት 58 በመቶ በ2008 በጀት ዓመት ወደ 61 በመቶ ከፍ ብሏል።

የማይሰሩ የገጠር መጠጥ ውሀ ተቋማት መጣኔ በ2007 የበጀት ዓመት 11.2 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2008 የበጀት ዓመት ብዙም ለውጥ ሳያሳይ 11 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል። በአጠቃላይ የንፁህ መጠጥ ውሀና የንፅህና አገልግሎት በኢትዮጵያ ገጠር እና ከተማ አካባቢዎች በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን በቀጣይ ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ እንደሆነ ከተደረሰበት የአፈፃፀም ደረጃ መመልከት ይቻላል።

ግብ 7፡ አቅምን ያገናዘበ ታዳሽ ኢነርጂ ለሁሉም ተደራሽነትን ማረጋገጥ፡- የኢትዮጵያ ኢነርጂ

መሠረተ-ልማት ዓላማ የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮችን ባገናዘበ ሁኔታ የኃይል ማስተላለፊያ ኔትዎርክን ማስፋፋት፣ አገልግሎት አሰጣጡን አስተማማኝና የተቀላጠፈ ማድረግና ተቋማዊ ትራንስፎርሜሽን ማረጋገጥ ናቸው። ከዚህ አንፃር የኢነርጂ ልማትን በመላ ሀገሪቱ በማስፋፋትና በማሳደግ ለሁሉም አካባቢዎች እንዲዳረስ ለማድረግ እየተሠራ ይገኛል። ከኃይል ማመንጫዎች ልማት አኳያ የውሀ ኃይል ማመንጫ፣ የጂኦተርማል ሀይል ማመንጫ፣ የንፋስ ሀይል ማመንጫ እና የፀሐይ ኃይል አቅርቦት በቅደም ተከተል ትኩረት የተሰጣቸው ናቸው። በዚህም መሠረት ሀገራዊ የኢነርጂ ፍላጐትን ለማሟላት ታዳሽ የሀይል ምንጮችን በማስፋፋት ንፁህና አየርን የማይበክል ከውኃ ኃይል፣ ከንፋስ ኃይል፣ ከእንፋሎት ኃይል፣ ከፀሐይ ኃይል ኢነርጂ ለማመንጨት የተቀናጁና የተደራጁ ጥረቶች በመካሄድ ላይ ናቸው።

በዚህም መሠረት የኤሌክትሪክ ኃሐሓይልየይል ማመንጨት ሀገራዊ አቅም በ2008 በጀት ዓመት 4,269.5 ሜ.ዋ. ደርሷል። በመገንባት ያሉ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም በተቀመጠላቸው ዕቅድ መሠረት እየተከናወኑ ነው፡ ከዚህ አንፃር በዓባይ ወንዝ ላይ እየተገነባ ያለው የታላቁ ህዳሴ የኃይል ማመንጫ ግድብ ፕሮጀክት አፈፃፀምም በ2009 ወደ 57 በመቶ ደርሷል። በሌላ በኩል የመነጨውን ኃይል ወደ ተጠቃሚዎች ለማድረስ የኃይል ማስተላለፊያ መሥመሮች የዝርጋታ ሥራ እየተከናወነ ሲሆን የተዘረጋውን መስመር በ2007 የበጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 14,065 ኪ.ሜ. በ2008 ወደ 15,137 ኪ.ሜ. ማሳደግ ተችሏል። ሀገራዊ የኤሌክትሪክ ሽፋንም በ2007 ከነበረበት 54.25 በመቶ በ2008 ወደ 56 በመቶ አድጓል።

በአጠቃላይ የዘላቂ ልማት ግቦችና ኢላማዎች ከሁለተኛው የዕደገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ተሳስረው እየተፈፀሙ ሲሆን አፈፃፀማቸውም በየደረጃው በዘርፍ አስፈፃሚ አካላት በየጊዜው ክትትል እየተደረገበት ይገኛል። ከዚህ አንፃር በክትትል ሪፖርቶች ላይ በመመሥረት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቋሚ ኮሚቴ አባላት የአፈፃፀሙን ሂደት በየጊዜው እየገመገሙ የማሻሻያና የማስተካከያ ግብረ መልሶችን ለፈፀሚው አካል እየሰጡ ይገኛሉ። በየበጀት ዓመቱ መጨረሻም ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ተሳስረው እየተተገበሩ ያሉ የዘላቂ ልማት ግቦችና ኢላማዎች አፈፃፀም ሪፖርቶች በፌዴራል የዘርፍ አስፈፃሚ ተቋማት አማካኝነት ለብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን እንዲቀርቡና እንዲገመገሙ ይደረጋል። በዚህም መሠረት የዘላቂ ልማት ግቦች እና ኢላማዎች አፈፃፀም በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ከተቀመጡ አመልካቾች አንፃር እንዲገመገሙና ሪፖርት እንዲዘጋጅ ይደረጋል።

የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሀገራዊ የልማት ማዕቀፍ ጋር ለማስተሳሰር እስካሁን በተደረጉ ጥረቶች የዘላቂ ልማት ግቦች ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ሙሉ በሙሉ ተሳስረዋል። የዘላቂ ልማት ግቦች ኢላማዎችንም ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ በዝርዝር ለማየትና ከዕቅዱ ጋር ለማስተሳሰር ተሞክሯል። ይህንን ጥረት አጠናክሮ በመቀጠል ትስስሩን ለማጠናከር በጅምር ላይ ያሉ የረጅም ዘመን ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ዝግጅት እና የዘላቂ ልማት ግቦች የማስፈፀሚያ ፋይናንስ ፍላጎት ጥናት ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል ተብሎ ይታመናል። እነዚህ ጅምር ሥራዎች የዘላቂ ልማት ግቦች ኢላማዎችን ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እና በዚሁ ዕቅድ አፈፃፀም ቋት ላይ ከሚተኩ የሶስተኛው እና አራተኛው ትራንስፎርሜሽን ዕቅዶች ጋር ይበልጥ በማስተሳሰር በበጀት ተደግፈው ወደ አፈፃፀም እንዲገቡ ለማድረግ ሰፊ ዕድሎች ይኖራሉ። የኢላማዎቹን የአፈፃፀም ሂደት ለመከታተልና ለመገምገም መረጃዎች እንዴት እንደሚሰበሰቡ አማራጮች የሚታዩ ይሆናል። ይሁን እንጂ ከአቅም ውስንነት ጋር ተያይዞ የአፈፃፀም መረጃዎችን በወቅቱ፣ በጥራት እና በሚጠበቀው ዝርዝር ማግኘት ትልቅ ፈተና እንደሚሆን ከወዲሁ ለማየት ተችሏል።

# 7. የዘላቂ ልማት ግቦች ትግበራ

## 7.1. የዘላቂ ልማት ግቦች አጠቃላይ አፈፃፀም

የኢትዮጵያ መንግስት ተተኪው ትውልድ የራሱን ፍላጎት ለማሟላት በሚያስችለው አቅም ላይ ተፅዕኖ የማያሳድሩ የልማት ሥራዎችን በማከናወን አሁን ያለውን ትውልድ ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችሉ ድህነት ተኮር አጠቃላይ ሀጋራዊ እና የሴክተር ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ቀርፆ በሥራ ላይ አውሏል። በተመሳሳይ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ አዘጋጅቶ ወደ ሥራ ገብቷል። የፓሪሱን የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (በፓርላማ) አስፀድቆ የሀገሪቱ የህግ አካል አድርጓል። እንዲሁም ብሔራዊ የአደጋ ክስተት ስጋት ሥራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ዘርግቶ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ተፈፃሚ በማድረግ ላይ ይገኛል።

የኢትዮጵያ መንግስት የልማት ፖሊሲዎች የሀገሪቱን አጠቃላይ ተጨባጭ ሁኔታዎች እና የህዝቦችን የልማት ፍላጎቶች መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ እና ህዝቦችን በየደረጃው ተጠቃሚ ለማድረግ ዓላማ ያላቸው ናቸው። በመንግስት የገጠር ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በግልፅ እንደተመለከተው ኢትዮጵያ ያላት ሰፊ ሀብት የሰው ጉልበትና መሬት ነው። ከዚህ አንፃር የመሬትና የብዝሀ ህይወት ደህንነትን በመጠበቅ፣ ፈጣንና ሁሉን-አቀፍ የኢኮኖሚ ዕድገት በማረጋገጥ፣ የኢኮኖሚ መሠረተ-ልማት፣ የማህበራዊ ልማት እና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን በማፋጠን የኢትዮጵያ ልማት መነሻና መድረሻ ህዝቦች እንደሆኑ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ያመለክታሉ። በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግስት በተለያዩ ደረጃዎች ተፈፃሚ እያደረጋቸው ያሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች የዘላቂ ልማት ግቦችን በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ እና የኢትዮጵያን ህዝቦች የልማቱ መነሻ እና መድረሻ ያደረጉ ናቸው። የኢትዮጵያ መንግስት እነዚህን ፖሊሲዎች በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ተፈፃሚ በማድረግ የምግብ ዋስትናን በሀገር፣ በአካባቢ እና በቤተሰብ ደረጃ ለማረጋገጥ፣ ድህነትን ከነሁሉም መገለጫዎቹ ለማጥፋት፣ የሥርዓተ-ፆታ ዕኩልነትን ለማረጋገጥ እና የአየር ንብረት ለውጥን በመቋቋም የኢትዮጵያ ዜጎችን ብልፅግና ለማረጋገጥ እየሠራ ይገኛል።

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የዘላቂ ልማት ግቦችን ተፈፃሚ ከማድረግ አኳያ የረጅም ዘመን ሀገራዊ የልማት ዕቅድ (2008-2022) የመጀመሪያ ምዕራፍ በሆነው በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012) ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው የልማት መስኮች (Development Priorities) ተለይተው ተቀምጠዋል። እነዚህም (1) የግብርና ዘርፉ የሀገሪቱ ፈጣን ኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ (2) በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዕመርታ ማምጣትና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ማፋጠን (3) የኢኮኖሚው የማምረት አቅም ላይ ለመድረስ ቅልጥፍናን በመጨመር ለምርታማነት፣ ጥራትና ተወዳዳሪነት ልዩ ትኩረት መስጠት (4) በጠቅላላ ፍላጎትና በጠቅላላ አቅርቦት መካከል የሚታየውን የተዛባ ክፍተት ማስተካከል (5) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና የፕሮጀክቶች ማኔጅመንት አቅምን ማጎልበት (6) ከከተማነት መስፋፋት ፈጣን ዕድገት፣ ኢንዱስትሪያላይዜሽንና መዋቅራዊ ለውጥ ጋር የተጣጣመ የከተማ አስተዳደርና አመራር መከተል (7) ለሀገር ውስጥ የግል ባለሀብቶች ትራንስፎርሜሽን ልዩ ትኩረት መስጠት (8) የሰው ኃብት ልማትን በቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ መደገፍ (9) ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት (10) የኪራይ ሰብሳቢነት ችግሮችን በመቅረፍ ልማታዊ የበላይነትን ማረጋገጥ ናቸው።

ከፍ ብሎ የተዘረዘሩ የልማት ትኩረቶች በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በዝርዝር በተቀመጡ የማክሮ-ኢኮኖሚ፣ የኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ፣ የመሠረተ ልማት ዘርፍ፣ የሰው ሀብት ልማትና የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ፣ የልማታዊ መልካም አስተዳደርና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እና የባለብዙ ዘርፎች ልማት ኢላማዎች አማካኝነት ውጤታማ እና ስኬታማ ሆነው እንዲፈፀሙ የሚመሩና መሠረታዊ አቅጣጫዎችን የሚያመላክቱ እንዲሁም ከዘላቂ ልማት ግቦች ጋር የተሳሰሩ ስትራቴጂክ አቅጣጫዎች በግልፅ ተቀምጠው የዕቅዱ የትግበራ ሂደት በተደረጀና

በተቀናጀ ሁኔታ እየተመራ ይገኛል። የዕቅዱ ስትራቴጂክ አቅጣጫዎችም (1) የተጀመረውን ፈጣን፣ ቀጣይና ፍትሐዊ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት ማስቀጠል፣ (2) የኢኮኖሚው የማምረት አቅም ላይ ለመድረስ ቅልጥፍና መጨመርና አምራች ዘርፎችን በማጐልበት በጥራት፣ በምርታማነትና በተወዳዳሪነት የላቀ ዕድገት ማምጣት (3) የተፋጠነ የሀገራዊ ባለሃብት ትራንስፎርሜሽን ማምጣትና ብቁ የልማት ኃይል ማድረግ (4) የኮንስትራክሽን ዘርፍ አቅም በማጐልበት የመሠረተ ልማት ተደራሽነትን መጨመርና የአገልግሎቱን ጥራት ማረጋገጥ (5) የከተሞችን ፈጣን ዕድገት በአግባቡ በመምራትና በማስተዳደር ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው ፈጣን ዕድገት አስተዋፅዖ እንዲጐለብት ማድረግ (6) የሰው ሃብት ልማትንና የቴክኖሎጅ አቅም ግንባታን ማፋጠንና ዘላቂነቱን ማረጋገጥ (7) የመንግሥትን የማስፈፀም አቅም በመገንባትና የህዝቡን ተሳትፎ በማጐልበት ዲሞክራሲያዊና ልማታዊ መልካም አስተዳደርን ማስፈን (8) የሴቶችንና የወጣቶችን ብቃት፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ እና (9) ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት ናቸው።

ከፍ ብሎ ከተመለከቱ የሁለተኛው አምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የልማት የትኩረት መስኮች (Development Prioties) እና መሠረታዊ አቅጣጫዎች (Strategic Pillars) መገንዘብ የሚቻለው የአፍሪካ ህብረት አጀንዳ 2063ን እና የዘላቂ የልማት አጀንዳ 2030ን ከኢትዮጵያ ብሔራዊ የልማት ማዕቀፍ ጋር አስተሳስሮ ተፈፃሚ ለማድረግ ምቹ ሁኔታዎች መኖራቸውን ነው። በዚህም መሠረት የድህረ 2015 የአፍሪካ የጋራ አቋም ግቦችን እና ዓለም አቀፍ የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሀገራዊ የልማት ማዕቀፍ ጋር በማስተሳሰር እና በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ ተፈፃሚ በማድረግ እ.ኤ.አ. በ2030 ግቦችን ለማሳካት መንግስት በቁርጠኝነት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር አስተሳስሮ ተፈፃሚ ከማድረግ አንፃር ኢትዮጵያ በአዲስ አበባ አክሽን አጀንዳ መሠረት የሀገር ውስጥ ሀብት የማሰባሰብ አቅሟን በማጠናከር የሚሰበሰበውን ሀብት ቀልጣፋና እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም እየሠራች ትገኛለች። የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈፀሚያዎችን በፋይናንስ፣ በቴክኖሎጂ እና በአቅም ግንባታ ለማጠናከር በዓለም አቀፍ አጋርነት ዙሪያ የተደራጁና የተቀናጁ ሥራዎች በመሠራት ላይ ናቸው።

ባለፉት ዓመታት መንግስት የታክስ ፖሊሲውን በተሻለ ሁኔታ በማስተዳደር የታክስ ገቢ ዕድገት እንዲያሳይ አድርጓል። ሆኖም የታክስ ገቢው እያደገ ከመጣው የመንግስት የወጪ ፍላጎት እና ኢኮኖሚው ሊያመነጭ ከሚችለው ገቢ ጋር ሲነፃፀር ብዙ እንደሚቀረው ታይቷል። በመሆኑም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የታክስ ፖሊሲውን እና የታክስ ህጉን ይበልጥ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ አግባብ በመፈፀም የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ በ2007 መጨረሻ ከነበረበት 13.3 በመቶ (ብር 165.3 ቢሊዮን) በ2012 ወደ 17.2 በመቶ (ብር 542.8 ቢሊዮን) ለማሳደግ ግብ ተቀምጦ እየተሠራ ይገኛል። ሆኖም የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ አፈፃፀም በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 12.7 በመቶ መጠነኛ ቅናሽ በማሳየት በ2008 የበጀት ዓመት 12.5 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል። በበጀት ዓመቱ የተመዘገበው አፈፃፀም በቀጣይ የታክስ ፖሊሲውን ይበልጥ በተሻለ ሁኔታ በማስተዳደር የታክስ አስተዳደር መረጃ ሥርዓቱን ለማጠናከርና የታክስ ከፋዮችንና የህብረተሰቡን የታክስ ትምህርትና ግንዥነት ለማሳደግ፣ የታክስ ህግን ለማስከበር እና የታክስና ገቢዎች መዋቅር ተቋማዊ አቅም ለመገንባት ትኩረት ተሰጥቶ መሠራት እንዳለበት የሚያመላክት ነው።

ሠላምና ደህንነት ልማትን ለማፋጠን፣ ድህነትን ለማጥፋት እና የህዝቦችን ብልፅግና ለማረጋገጥ ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው። በመሆኑም ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታት ከተመሠረተበት እ.ኤ.አ. ከ1945 ጀምሮ የድርጅቱን የሠላምና የደህንነት መርሆዎች የመጠበቅና የማስከበር ድርሻዋን በስኬታማነት እየተወጣች ትገኛለች። በተባበሩት መንግስታት የሰላም ማስከበር ሂደት ያላት ተሳትፎም እ.ኤ.አ. ከ1950ዎቹ ጀምሮ ረጅም ታሪክ ያለው ነው። በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ከፍተኛ ቁጥር ያለው የተባበሩት መንግስታት የሰላም አስከባሪ ኃይል ያሰማራች እና ለአፍሪካ ህብረት የሰላም አስከባሪ ኃይል በማሰማራትም ቀዳሚ ሀገር

ናት። በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግስት የሀገሪቱን ሰላምና ደህንነት በመጠበቅ በአህጉራዊ እና ዓለም አቀፍ የሰላም እና የደህንነት ማስጠበቅ አጀንዳ ወሳኝ ሚና እየተጫወተ ነው። ይህም ሁሉን-አቀፍ የሆነውን የ2030 የዘላቂ ልማት አጀንዳ በሀገር፣ በአህጉር እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማሳካት የጎላ አስተዋፅኦ አለው።

ከፍ ብሎ በዝርዝር የተገለፁ ሀገራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የልማት፣ የሠላም እና የደህንነት ጉዳዮች በኢትዮጵያ መንግስት የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አካል ተደርገው በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች በትግበራ ሂደት ላይ ናቸው። የዘላቂ ልማት ግቦችን በማስተሳሰር በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በ2008 የበጀት ዓመት ወደ ትግበራ የገባው የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በመጀመሪያ የትግበራ ዘመኑ (በ2008 የበጀት ዓመት) በሀገሪቱ በተከሰተውና ሁሉንም የሀገራችን አካባቢዎች በስፋት ባዳረሰው ከፍተኛ ድርቅ ፈተናዎች ያጋጠሙት ቢሆንም መንግስት የድርቁን የጉዳት መጠን፣ ጥልቀትና ስፋት በዝርዝር በማጥናት ተፅዕኖዎችን በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ በመቋቋም የአንድም ሰው ህይወት ሳይጠፋ የኢኮኖሚውን ፈጣን ዕድገት፣ ማህበራዊ ልማትና የአካባቢ ልማት ማስቀጠል ችሏል። በዕቅዱ ሁለተኛ የትግበራ ዘመንም (በ2009 የበጀት ዓመት) በሀገራችን ውሀ አጠር እና አርብቶ-አደር አካባቢዎች ከፍተኛ ድርቅ ተከስቷል። ይህ የአየር ንብረት ለውጥን ተከትሎ በኢትዮጵያ አንዳንድ አካባቢዎች የተከሰተው ድርቅ የሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድና የዘላቂ ልማት ግቦች በሙሉ አቅም ከማስፈፀምና ከመፈፀም አኳያ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ቀላል ባይሆንም እንደተለመደው የድርቁን የጉዳት መጠን፣ ጥልቀትና ስፋት በዝርዝር በማጥናት የአንድም ሰው ህይወት ሳይጠፋ በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ የድርቅ አደጋውን በመቀልበስ የትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን ዓላማና ግቦች በተቀመጠላቸው ደረጃ ለማሳካት በሀገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ርብርብ በመደረግ ላይ ነው።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ መንግስት የአየር ንብረት ለውጥን ተከትሎ በ2008 እና በ2009 በሀገሪቱ ውስጥ የተከሰተውን ከፍተኛ ድርቅ በብሔራዊ የአደጋ ክስተት ስጋት ሥራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂው መሠረት የልማት ኃይሎችን አስተባብሮ በመምራት እና በዝርዝር ጥናቶች በመደገፍ በድርቁ ምክንያት የአንድም ሰው ህይወት ሳይጠፋ የድርቁን አደጋ በመቋቋም የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት የተዘጋጀውን የሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተፈፃሚ በማድረግ በዕቅዱ የመጀመሪያ የትግበራ ዘመን መልካም ውጤት አስመዝግቧል። ይህም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ድርቅን የመቋቋም አቅሙ እያደገ መምጣቱን ያመለክታል።

## 7.2. ዘላቂ ልማት ለሁሉም (Leaving No One Behind)

የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች በማካተት የተዘጋጁ ሦስት ተከታታይ ሀገራዊ ዕቅዶችን ተፈፃሚ በማድረግ ኢኮኖሚውን በየዓመቱ በአማካኝ በ10.8 በመቶ ማሳደግ ተችሏል። ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ በ2002 ከነበረበት 377 የአሜሪካን ዶላር በ2008 መጨረሻ ወደ 794 የአሜሪካን ዶላር ከፍ ብሏል። ይህንኑ ተከትሎ ሀገራዊ የድህነት መጣኔ በ992 ከነበረበት 44.2 በመቶ በ2003 ወደ 29.6 በመቶ የቀነሰ ሲሆን በ2007 መጨረሻ ወደ 23.4 በመቶ ዝቅ እንደሚል ተገምቷል። ይህንን ሀገራዊ የድህነት መጣኔ በ2012 ወደ 16.7 በመቶ ለመቀነስ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ኢላማ ተቀምጦ እየተሠራ ይገኛል።

ከሰው ኃብት ልማት አኳያ የመጀመሪያ ደረጃ (ከ1ኛ-8ኛ ክፍል) ትምህርት ቤቶች ቁጥር በ2002 ከነበረበት 26,951 በ2007 ወደ 33,373 ከፍ ያለ ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ንጥር ተሳትፎ በ2002 ከነበረበት 82.1 በመቶ በ2007 ወደ 96.9 በመቶ እና በ2008 ወደ 97.6 በመቶ አድጓል። በሌላ በኩል የኢትዮጵያ መንግስት ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ስትራቴጂ ቀርፆ ማይምነትን በ95 በመቶ ለማስወገድ (ከ15-60 ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን ማንበብ፣ መፃፍና አነስተኛ የሂሳብ ስሌት እንዲችሉ ማድረግ) እየሠራ ይገኛል። በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ መረጃ መሠረት ማንበብ፣ መፃፍና አነስተኛ የሂሳብ ስሌት የማይችሉ እና ዕድሜያቸው ከ15-60 የሆኑ ዜጎች ቁጥር በ2004 የበጀት ዓመት 20.4 ሚሊዮን ነበር። ይህ ቁጥር በ2007 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 8.4 ሚሊዮን (58.82 በመቶ) ዝቅ ብሏል። በ2008 የበጀትም 6.9 ሚሊዮን ጎልማሶች ተግባር

ተኮር የጎልማሶች ትምህርት በመከታተል ላይ ነበሩ። በዚህም መሠረት እነዚህ ጎልማሶች ማንበብ፣ መፃፍና ቀላል ሂሳብ ስሌት ችለው ሲመረቁ የማይማን ቁጥር ወደ 1.5 ሚሊዮን (92.65 በመቶ) ዝቅ እንደሚል ይጠበቃል። ማይምነትን ለማጥፋት የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት በሁለተኛው የዕድገትና ተራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀናጀና የተደራጀ ሥራ ይሠራል። ሀገራዊ የጤና ሽፋን በ2002 ከነበረበት 89.6 በመቶ በ2008 ወደ 98 በመቶ ከፍ ያለ ሲሆን አጠቃላይ ሀገራዊ የመጠጥ ውሃ ሽፋን በሁለተኛው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ስታንዳርድ መሠረት በ2008 በጀት ዓመት መጨረሻ 68.1 በመቶ ደርሷል። ሆኖም በተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም እ.ኤ.አ. የ2016 የሰው ሀብት ልማት ሪፖርት መሠረት የትዮጵያ የሰው ሀብት ልማት አመልካች በዝቅተኛ (0.448) ደረጃ ላይ ይገኛል።

የድህነት ልየታ:- ኢትዮጵያ ድህነትን በግማሽ በመቀነስ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግብ ማሳካት ችላለች። ሀገራዊ የድህነት መጣኔ በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ጥናት መሠረት በ1992 ከነበረበት 44.2 በመቶ በ2003 ወደ 29.6 በመቶ እንዲሁም በ2007 መጨረሻ በተካሄደ የአፈፃፀም አዝማሚያ ትንተና ወደ 23.4 በመቶ ዝቅ እንደሚል ተገምቷል። በ2003 የድህነትና ልማት ትንተና ሪፖርት መሠረት ድህነት ከፆታ አንፃር ሲተነተን በከተማ የእማወራ ቤተሰብ ኃላፊዎች የድህነት መጣኔ ከአባወራ ቤተሰብ ኃላፊዎች እንደሚበልጥ እና በገጠር ግን የአባወራ ቤተሰብ ኃላፊዎች ለድህነት የመጋለጥ እድል እንዳላቸው ትንተናው ያመለክታል። ድህነት ከቤተሰብ ብዛት አንፃር ሲተነተን ደግሞ በሀገሪቱ በአጠቃላይ የቤተሰብ ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ የድህንት መጠን እየጨመረ እንደሚሄድ ሆኖም በከተማ የቤተሰብ ቁጥር ሲጨምር ከገጠሩ በበለጠ ድህነቱ እንደሚጨምር ያመለክታል።

በተመሳሳይ ድህነት ከትምህርትን ደረጃ አንፃር ሲተነተን የትምህርት ደረጃ በከተማም በገጠርም ድህነትን የመቀነስ አቅም እንዳለው ሆኖም በከተማ በተሻለ መልኩ የትምህርት ደረጃ በጨመረ ቁጥር ድህነትን የመቀነስ አቅም እንዳለው ያሳያል። እንዲሁም ድህነት ከቤተሰብ ኃላፊ ዕድሜ አንፃር ሲተነተን እድሜያቸው ከ30-64 የሆኑ የቤተሰብ ኃላፊዎች ለድህነት የመጋለጥ ዕድል 33 በመቶ፣ ዕድሜያቸው ከ65 ዓመት በላይ 29 በመቶ፣ እድሜያቸው ከ16-29 ወደ 16 በመቶ ለድህነት የመጋለጥ ዕድል እንዳላቸው ያመለክታል። ከዚህ በተጨማሪም የ2003 የድህነት ትንተና ሪፖርት በሽታ፣ ድርቅ፣ የእንስሳት ሞት፣ የሰብል መጥፋት፣ ሞት፣ ጎርፍ፣ የዋጋ ንረት፣ የሥራ አጥነት፣ የምግብ አቅርቦት እጥረት በገጠርም ሆነ በከተማ ለአደጋ ተጋላጭ የሚያደርጉ መንሴዎች እንደሆኑ አመልክቷል።

የ2030 የዘላቂ ልማት አጀንዳ በ2030 ድህነትንና ረሃብን የማጥፋት፣ የሰብዓዊ ሀብት ልማት በሁሉም መስክ ለሁሉም የሰው ልጆች በሁሉም አካባቢ የማረጋገጥ ዋና ዓላማ ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግስት የዘላቂ የልማት ግቦችን በሁለተኛው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በማካተት በ2030 በሀገሪቱ ድህነትን ለማጥፋት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ ዜጎች፣ ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ለህፃናት፣ ለወጣቶች፣ ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋዊያን፣ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የመሰረተ ልማት ጥራትና ተደራሽነት እጥረት ያለባቸው አካባቢዎች፣ ለዝናብና ምግብ አጠር ወረዳዎችና አካባቢዎች ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል።

የፖሊሲ አቅጣጫዎች:- የመንግስት የልማት ፖሊሲዎች መሠረተ-ሰፊና ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ ዕድገትን በማፋጠን፣ ማህበራዊና መሠረተ ልማትን በማስፋፋት፣ የአካባቢ ደህንነትና ልማትን በማረጋገጥ እና ድህነትን በማጥፋት ላይ ያተኮሩ ናቸው። የፖሊሲ አቅጣጫዎች ዜጎች በልማቱ ዕኩል ተሳታፊ እና ፍትሐዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ናቸው። በመሆኑም የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት የተዘጋጀው የሁለተኛው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሰረተ ሰፊና ሁሉን አቀፍ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት፣ መሠረተ ልማት፣ ማህበራዊ ልማት እና የአካባቢ ልማት ለማረጋገጥ የተለጠጡ ግቦችን ያስቀመጠ ነው። የገጠር የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራምን፣ የከተማ የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም፣ የቀጥታ ድጋፍ፣ የአካል ጉዳተኞች ማህበራዊ ዋስት ፕሮግራሞችን፣ ፍትሀዊ የመሠረተ ልማት ግንባታና የህዝብ ተሳትፎ፣ የጤና መድህን ስርዓት ግንባታ፣ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎትን እና የጤና ልማት ሰራዊት ግንባታ ማጠናከር እንዲሁም የህፃናትን እና የሴቶችን አጀንዳዎች

በሁሉም ዘርፎች ማካተት፣ የሴቶችንና የወጣቶችን ብቃት፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ ከተቀመጡ የማስፈፀሚያ መንገዶች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው።

የበጀት አደላደሉም በዋናነት ድህነትን ለማጥፋትና ቁጠባንና ኢንቨስትመንትን ለሚያበረታቱ ዘርፎችና ሴክተሮች ላይ ያተኮረ ሆኖ የበጀት ምንጩም በዋናነት በሀገር ውስጥ ገቢ ለመሸፈን ትኩረት ይሰጣል። ለዚህም የታክስ መሠረት በማስፋት፣ የመሰብሰብ አቅምን፣ የውጭ ምንዛሬ ገቢን፣ የሀገር ውስጥ ብድር ማሳደግን ታሳቢ ያደርጋል። በ2017 የፍቃደኝነት ግምገማ ዘላቂ ልማት ለሁሉም (Leaving No One Behind) የሚለውን የዘላቂ ልማት አጀንዳ ዋና መርህ ለግምገማው ከተመረጡ እያንዳንዱ ግብ ሥር የተዘረዘሩ የፖሊሲ አቅጣጫዎች፣ የማስፈፀሚያ ስልቶች፣ ተሞክሮዎች፣ ፈተናዎች መመለከት የሚቻል ሆኖ በዚህ ክፍል የፋይናንስ አካታችነት፣ የመንገድ ደህንነትና ትራፊክ ማኔጅመንት፣ የህፃናት ደህንነት፣ አሳታፊ የዘላቂ ልማት የክትትልና ግምገማ የሚሉ ርዕሶችን በተመለከተ የተካሄዱ ግምገማዎች ግኝቶችን በአጭሩ ለማቅረብ ተሞክሯል።

### 7.2.1. የፋይናንስ አካታችነት

የፋይናንስ አካታችነት የኢትዮጵያን የፋይናንስና ገንዘብ ሥርዓት ለማረጋጋት፣ የጥሬ ገንዘብ ግብይትን ወደ መደበኛ የባንክ ሥርዓት ለመቀየር፣ ቁጠባን ለማበረታታትና ለመደገፍ፣ የብድር ፍላጎትን ለማሟላት፣ ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ፣ የሥራ ዕድልን ለመፍጠርና ገቢን ለማሳደግ በሂደትም ድህነትን ለመቀነስ ትልቅ እገዛ ያደርጋል።

የፋይናንስ አካታችነት የፖሊሲ አቅጣጫ፡- የኢትዮጵያ የፋይናንስ አካታችነት የፖሊሲ አቅጣጫ የሀገሪቱን የልማታዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ልማት ማዕከል ያደረገ፣ እ.ኤ.አ. በ2025 ኢትዮጵያን ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተቀመጠውን ሀገራዊ ራዕይ እና የግብርናና የገጠር ልማት ፖሊሲን የማሳካት፣ ሁሉን አቀፍና ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማስቀጠል፣ በሀገሪቱ የተጀመረውን የትራንስፎርሜሽንና የህዳሴ ጉዞ የማፋጠን፣ ለሁሉም የሀገራችን አካባቢዎችና ሕዝቦች ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ የፋይናስና የገንዘብ ሥርዓት የመዘርጋት ዓላማ ያለው ነው። ይህንን ዓላማ ለማሳካት የፋይናንስና ተጓዳኝ መሠረተ ልማቶችን የማጠናከር፣ የተለያዩ ተስማሚ የፋይናንስ ምርቶች፣ አገልግሎቶችና የአገልግሎት መስጫ መዳረሻዎች አቅርቦት አጥጋቢ መሆናቸውን የማረጋገጥ፣ ጠንካራ የፋይናንስ ተገልጋዮች ጥበቃ የመዘርጋት፣ የፋይናንስ አገልግሎቶች ዕውቀትና ግንዛቤ ደረጃን የማሳደግ ስትራቴጂዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል።

አፈፃፀም፡- ኢትዮጵያ አሁን ያለችበትን የፋይናንስ አካታችነት (ተደራሽነትና ተጠቃሚነት) በመተንተን፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የሀገሪቱ የልማት አጀንዳዎች መሠረት በማድረግና የኢኮኖሚና ማህበራዊ አቅጣጫዎች ላይ በመመርኮዝ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፣ ብሔራዊ የፋይናንስ አካታችነት ካውንስልም በመንግስት ተቋቋሟል። በኢትዮጵያ በሥራ ላይ ያለውን የፋይናንስ ሥርዓትና አገልግሎት ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ ተወዳዳሪ፣ ጥራትና ሰፊ ሽፋን ያለው በማድረግ የሀገሪቱን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ እየተሠራ ይገኛል።

በሁለተኛው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ የባንክ ቅርጫፎችን ቁጥር ወደ 5,736 ለማሳደግ፣ ለ100 ጎልማሶች የተቀማጭ ሂሳብ ቁጥር ወደ 90፣ በመደበኛ የፋይናንስ ተቋማት የፋይናንስ አገልግሎት እንዲያገኙ ሪፖርት የሚያደርጉ ጎልማሶችን (ከ18 ዓመት በላይ) 60 በመቶ ለማድረስ ግብ ተቀምጧል። በዕቅድ ዘመኑ በሀገሪቱ በሁሉም አካባቢዎች ለሁሉም ህብረተሰብ የፋይናንስ ተደራሽነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በተሰራው ሥራ እስከ 2008 የበጀት ዓመት 16 የግል ባንኮች እና 2 የመንግስት ባንኮች በድምሩ 18 ባንኮች በሥራ ላይ ይገኛሉ። በ2008 የበጀት ዓመት 363 የግል ባንኮች ቅርንጫፎች እና 131 የመንግስት ባንኮች ቅርንጫፎች በድምሩ 494 አዳዲስ ቅርጫፎች በመከፈት ጠቅላላ የባንክ ቅርጫፎችን ቁጥር በ2007 ከነበረበት 3,187 በ2008 የበጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 3,681 ማሳደግ ተችሏል። በመሆኑም በ2007 የበጀት ዓመት አንድ የባንክ ቅርንጫፍ ለ33,448 ህዝብ አገልግሎት ይሰጥ የነበረ ሲሆን (1:3,3448) ይህንን ጥምርታ በ2008 የበጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 1:28,932 ዝቅ ማድረግ ተችሏል።

በተመሳሳይ 17 የመድን ሰጪ ድርጅቶች፣ 35 አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት እና 5 የሊዝ ኩባንያዎች ተቋቁመዋል። ከዚህ በተጨማሪ በሀገሪቱ የገጠር አካባቢዎች 1.8 ሚሊዮን አባላት ያሏቸው 18,000 የቁጠባና ብድር ሕ/ሥ/ማህበራት እንዲስፋፉ ተደርጓል። በዚህም በ2008 የበጀት ዓመት የባንክ ተቀማጭ ሂሳቦች ወደ 19.3 ሚሊዮን፣ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ደንበኞች ተቀማጭ ሂሳቦች ወደ 11.4 ሚሊዮን በድምሩ ወደ 30.7 ሚሊዮን የተቀማጭ ሂሳቦች ማሳደግ ተችሏል። ይህ የፋይናንስ አካታችነት እየተመዘገበ ላለው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት፣ የቁጠባና ኢንቨስትመንት፣ የስራ ዕድል ፈጠራና ገቢ፣ የድህነት ቅነሳ እገዛ አድርጓል። በዚህ ሂደትም አርሶ-አርብቶ አደሮች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ የጥቃቅን፣ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች በቀጥታና በተዘዋዋሪ ተሳታፊና ተጠቃሚ ሆነዋል።

### 7.2.2. የህጻናት መብትና ደህንነት

የፖሊሲ አቅጣጫ፡- በሀገራችን የህጻናትን መብትና ደህንነትን የማረጋገጥ፣ እንክብካቤና ድጋፍ፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነታቸውን የማሳደግ የመንግስት ቁርጠኝነት ተልዕኮ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስትን፣ የሀገሪቱን የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂን፣ ዓለም አቀፍ የህጻናት መብቶች ስምምነትና የአፍሪካ ቻርተርን፣ ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አዋጅን፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስትራቴጂን፣ መመሪዎችን መሰረት ያደረገ ነው። ለውጤታማነቱም መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማትና አጋር አካላት ጋር በትብብር መስራትን፣ የህጻትን፣ የህብረተሰቡን፣ ሁሉንም ተቋማት ተሳትፎና ባለቤትነት ታሳቢ ባደረገ መልኩ የህጻናትን መብትና ደህንነትን የማረጋገጥ አቅጣጫ የተከተለ ነው።

አፈፃፀም፡- የሴቶችና የህፃናት ጉዳዮች በሁሉም ዘርፎች ተካትተው ተፈፃሚ የሚደረጉ ቢሆንም መንግስት ለጉዳዮቹ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት እዚህን ጉዳዮች በሀገር አቀፍ ደረጃ በባለቤትነት ይዞ የሚመራ እና የሚያስተባብር የሚኒስቴር መ/ቤት አቋቁሟል። እንዲሁም በእያንዳንዱ የፌዴራል አስፈፃሚ መ/ቤት የሴቶችንና የህጻናትን ጉዳዮች የሚከታተል የሥራ ክፍል ተቋቁሞ እየሠራ ይገኛል። በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች ደረጃም የሴቶችን የህፃናትን ጉዳዮች በባለቤትነት ይዘው የሚመሩና የሚያስተባብሩ ቢሮዎች ተቋቁመው የልማት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ናቸው።

የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦችን በኢትዮጵያ ተፈፃሚ በማድረግ ሂደት በተከናወኑ የልማት ሥራዎች በህጻናት መብትና ደህንነት ዙሪያ አመርቂ ውጤቶች ተመዝግበዋል። ለምሳሌ ዕድሚያቸው 5 ዓመት ሳይሞላ ይሞቱ የነበሩ ህፃናት ቁጥር በ1982 ከነበረበት 204/1000 በ2007 መጨረሻ ወደ 64/1000 ዝቅ ብሏል። በ2008 የበጀት ዓመት እና በ2009 የመጀመሪያ ግማሽ የበጀት ዓመት የህፃናት መብትና ደህንነትን በተመለከተ የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት በተዘጋጀው ሁለተኛው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በርካታ የልማት ሥራዎች ተከናውነዋል። ለምሳሌ ብሔራዊ የህጻናት ፖሊሲ ተዘጋጅቶ እና በመንግስት ፀድቆ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል። የህፃናት መብት ደህንነት መረጃ ሥርዓትም በክልሎች በመዘርጋት ላይ ይገኛል። በፌዴራል ደረጃ የህጻናት ደህንነት የመረጃ ሥርዓት ለመዘርጋት የዳታ ቤዝ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል። የህጻናት ተሀድሶ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የግንባታ ስራዎች፣ ለህጻናት ተስማሚ የሆኑ ልዩ ችሎቶችን በፍ/ቤቶች የማቋቋም ስራ ተጀምሯል፣ የህጻናትን ጉዳይ ተቋማዊ የማደረጉ ሰራ በሴክተር መ/ቤቶች በመጠናከር ላይ ይገኛል።

ለተለያዩ የፌዴራልና የክልል ኃላፊዎች፣ ባለሞያዎች፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ የህጻናት አደረጃጀቶችን ያሳተፈ በህጻናት መብት ደህንነትና ጥበቃና መሰል ጉዳዮች ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት ሴሚናሮችና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎች ተካሂደዋል። ከተለያዩ ሴክተሮችና አጋር አካላት ለተውጣጡ 21,860 ኃላፊዎችና ባለሞያዎች በህፃናት መብትና ደህንነት፣ በህጻናት ህገ-ወጥ ዝውውር፣ በጉልበት ብዝበዛ፣ ፆታዊ ጥቃትና በህፃናት መልካም አስተዳደግ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ሥራዎች ተሰርተዋል። በህፃናት ላይ በሚፈፀሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ ጥቃቶች፣ ጉልበት ብዝበዛ ዙሪያ ለ461,552 የህብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል። የህጻትን ተሳትፎ ከማሳደግና የኑሮ ሁኔታ ከማሻሻል አንፃር 447,683 ህጻናት የማህበረሰብ ድጋፍና ክብካቤ፣ 67,844 ህጻናት በአደራ ቤተሰብ፣ 945 ህጻናት በሀገር ውስጥ ጉዲፈቻ፣ 63 ህፃናት

በውጭ ሀገር ጉዲፈቻ፣ 2,928 ህጻናት በመልሶ ማቀላቀል ፕሮግራሞች፣ 45,808 ህጻናት የልዩ ትምህርት ድጋፍ ተጠቃሚ በማድረግ ተችሏል፡፡ ለህጻናት የድጋፍና ክብካቤ ጥምረት፣ ለህጻናት መብት ኮንቬንሽን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣ ከህጻናት ፓርላማና ከክበብ አባላት ለተውጣጡ 8,402 ተሳታፊዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

የኢትዮጵያ ህፃናት ፓርላማ፡- የኢትዮጵያ መንግስት የተለያዩ የህግና የፖሊሲ ማዕፎች በማውጣት እና ዓለም አቀፍ የህፃናት መብት ኮንቬንሽንን በመፈረም የህፃናትን መብትና ደህንነት ለማስጠበቅ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በተለይም የህፃናትን ተሳትፎ ለማሳደግ በየደረጃው እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች የሚያበረታቱ ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር ህፃናት የሚሳተፉባቸው የተለያዩ አደረጃጀቶችን እና የተሳትፎ መድረኮችን በማመቻቸት ለተጠናከረ እንቅስቃሴያቸው ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ በዋነኝነት የሚጠቀሱ ተግባራ ናቸው፡፡ በመሆኑም በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች የህፃናት ፓርላማዎችና የህፃናት መብቶች ክበባት ተቋቁመው በርካታ ሥራዎች በማከናወን ላይ ናቸው፡፡

የህፃናት ፓርላማ ዓላማ፡- የህፃናት ፓርላማ ዋና ዓለማ ህፃናት በፓርላማቸው አማካኝነት የተደራጁ ድምፆቻቸውን በማሰማት ከየትኛውም አካባቢያዊና ቤተሰባዊ ተፅዕኖ አካልንና አዕምሮን የሚጎዱ ልማዳዊ ድርጊቶች ራሳቸውን ጠብቀው ሌሎች ህፃናትን መከላከል እንዲችሉ በሚመለከታቸው የጋራ ጉዳዮች ላይ የተደራጁ ጥያቄዎች በማቅረብና በመወያየት የጋራ አቋማቸውን እንዲያራምዱ የህፃናት ፓርላማን በመጠቀም ድምፃቸውን ለቤተሰብ፣ ለማህበረሰብ፣ በየደረጃው ለሚገኙ የመንግስትና የፍትህ አካላት እንዲያሰሙ ዕድል በመፍጠር መብታቸውን ማስከበርና ተግባርና ኃላፊነታቸውን በብቃት እንዲወጡ ማስቻል ነው፡፡

የህፃናት ፓርላማ አሠራርና አደረጃጀት፡- ከአደረጃጀት አንፃር የኢትዮጵያ ህፃናት ፓርላማ የየራሳቸው የሥራ ድርሻ ያላቸው ስድስት የቋሚ ኮሚቴ አደረጃጀቶች ያሉት፡፡ እነዚህም (1) የህፃናት መብት ጥበቃ ቋሚ ኮሚቴ (2) የማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ (3) የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ቋሚ ኮሚቴ (4) የባህልና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ (5) የሥርዓተ ፆታ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እና (6) የሥነ-ምግባርና የህፃናት ትምህርት ተሳትፎ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ናቸው፡፡ አሠራርን በሚመለከት የህፃናት ፓርላማ በአፈ-ጉባዔ የሚመራ ሲሆን እያንዳንዱ የህፃናት ፓርላማ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ ፀሀፊ እና ሁለት አባላት አሉት፡፡ የቋሚ ኮሚቴዎቹ ተጠሪነትም ለፓርላማው አፈ-ጉባዔ ነው፡፡ ጠቅላላ የህፃናት ፓርላማ አባላት ቁጥር 8428 ሲሆን ከዚህ ውስጥ የሴት ህፃናት ፓርላማ አባላት ቁጥር 44424 ነው፡፡

የህፃናት ፓርላማ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት መካከል ዋና ዋናዎቹ (1) በማህበራዊ መስክ ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ህፃናትን ለመደገፍ የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ድጋፍ ማድረግ እና በትምህርት ቤት ውስጥ ከህፃናት የትምህርት ውጤት መሻሻል፣ የጤና አጠባበቅና የአካባቢ እንክብካቤ ጋር በተያያዘ የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን (2) በህፃናት መብቶች ዙሪያ በቤተሰብ፣ በአካባቢ ህብረተሰብና በትምህርት ቤት ውስጥ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን መስጠት፣ መጤ ባህልን፣ ጎጂ ልማዳዊና ኢሰብአዊ ድርጊቶችን በሚመለከት ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ትምህርቶችን መስጠት እና (3) በኢኮኖሚ ጉዳዮች ዙሪያ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በመተባበር የቁጠባ ባህል ለማዳበር የህፃናት ፓርላማ አባላት እንዲቆጥቡና ለታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ቦንድ በመግዛት አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ማበረታታት ናቸው፡፡

### 7.2.3. የመንገድ ደህንነትና ትራፊክ ማኔጅመንት

የፖሊሲ አቅጣጫ፡- በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን የህዝብ ብዛት፣ የከተሞች መስፋፋት የኢንዱስትሪ፣ የንግድ፣ የትምህርት፣ የጤና እና ሌሎች አገልግሎቶችን ለማሟላት እና እ.ኤ.አ. በ2025 ሀገራችንን ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍ የመንገድ መሠረተ ልማትን ማስፋፋትና የትራፊክ ደህንነትን ማረጋገጥ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የመንገድ መሠረተ ልማት ማስፋፋትና ጥራቱን ማስጠበቅ፣ የትራፊክ አደጋን የመከላከልና የመቀነስ አቅምን መገንባት፣ የማስፈፀሚያ የህግ ማዕቀፍ የማዘጋጀትና የመተግበር፣ የሚደርሱ አደጋዎችንና ተጎጂዎችን በአግባቡ ማስተዳደር ቅድሚያ የሚሰጣቸው የፖሊሲ አቅጣጫ ናቸው፡፡ ስለሆነም የሀገሪቱን ትራፊክ ማኔጅመንት ውጤታማና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ፣ ዘመናዊ የመንገድ ደህንነትና የመንገድ ትራፊክ ባለሞያዎች

አቅም በማሳደግ፣ የተሻሻለና ዘመናዊ የመንገድ ትራንስፖርት ሥርዓት በመገንባት እና በጥናትና ምርምር በመደገፍ በትራፊክ አደጋ ምክንያት የሚደርሰውን የሰው ሞት፣ የአካል ጉዳትና ንብረት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ በመንግስት ቁርጠኛ አቋም ተይዞ እየተሰራ ነው።

አፈጻጸም፡- የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማቶችን ለማፋጠን በመንገድ መሠረተ ልማት ግንባታ ረገድ መንግስት ከፍተኛ ሀብት በመመደብ የግንባታ ሥራዎችን በማካሄድ ላይ ይገኛል። በዚህም የመንገድ ተደራሽነትንና የመንገድ ደህንነትን ለማረጋገጥ እንዲሁም የኢኮኖሚና የማህበራዊ አገልግሎቶችን አስተዋፅኦ ለማሻሻል በዋና ዋና የሀገሪቱ ኮሪደሮች ሰፋፊ የፍጥነት መንገዶች በመገንባት በትራፊክ መጨናነቅ የሚደርሰውን አደጋ ለመቀነስ በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል። በዚህም መሠረት ክረምት ከበጋ የሚያስኬዱ መንገዶች ርዝመት በ2008 የበጀት ዓመት 113,067 ኪ.ሜ. ደርሷል።

የ10 ዓመት የብሔራዊ የመንገድ ደህንነት ዕቅድ የድርጊት መርሐ-ግብር ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እተደረገ ሲሆን የድርጊት መርሐ-ግብሩን ለመተግበር ብሔራዊ የመንገድ ደህንነት ምክር ቤት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተቋቁሟል። የአሽከርካሪ እና የትራንስፖርት ትራፊክ ብቃት ማረጋገጫ አዋጅ ማሻሻያ ተዘጋጅቶ ለመንግስት ቀርቧል። የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ተሻሽሎ ተግባራዊ እየተደረገ ሲሆን የመንገድ ደህንነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች የተሠጡ ሲሆን በትምህርት ቤቶች ስለ ትራፊክ አደጋ ግንዛቤ የሚሰጥ ካሪኩለም ተቀርፆ ትምህርት በመሰጠት ላይ ይገኛል። የሰስተኛ ወገን የመድህን ሽፋን ተግባራዊ እየተደረገ ነው። በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ በተሽከርካሪ የሚደርስ የሞት አደጋን ወደ 27/10,000 ተሽከርካሪ ዝቅ ለማድረግ በዕቅድ ተይዞ እየተሰራ ሲሆን አሁን ላይ ያለው የሞት አደጋ መጠን በጣም ከፍተኛ ነው።

### 7.2.4. አሳታፊ የዘላቂ ልማት ክትትልና ግምገማ ሥርዓት

የዘላቂ ልማት ግቦች ለሁሉም (Leaving No One Behind) ዓለም አቀፍ መርህ ማረጋገጫ ሌላው መንገድ ሁሉም የሀገሪቱ ሕዝቦች ስለ ዘላቂ ልማት ግንዛቤ ሲያገኙ እና በዕቅድ ዝግጅት፣ በትግበራ፣ በክትትልና ግምገማ በንቃት እና በግልፀኝነት ሲሳተፉና አስተዋፆ ሲያደርጉ ነው። በመሆኑም በኢትዮጵያ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች በማካተት በተዘጋጁ የዘላቂ ልማትና ድህነት ቅነሳ ፕሮግራም (1995-1997)፣ በተፋጠነ ዘላቂ ልማት ድህነትን የማጥፋት ዕቅድ (1998-2002) እና በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2003-2007) እንዲሁም የ2030 የዘላቂ ልማት አጀንዳን በማካተት በተዘጋጀው የሁለተኛው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012) ሁሉም ባለድርሻ አካላት በተወካዮቻቸው አማካኝነት በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በዕቅድ ዝግጅት ተሳትፈዋል።

ኢትዮጵያ የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት ባዘጋጀችው የሁለተኛው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን በዕቅድ ዝግጅት ወቅት እና በ2008 የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ ረቂቅ ሪፖርት ላይ በተዘጋጁ የምክክር መድረኮች የግሉ ዘርፍ፣ የሲቪል ማህበረሰብ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ፓርላማ)፣ የተቋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች.. ወዘተ በተወካዮቻቸው አማካኝነት በንቃት ተሳትፈዋል። ከምክክር መድረኩ የተገኙ ግብረ መልሶችም የዕቅድና የግምገማ ሪፖርቶችን ለማሻሻል በግብዓትነት ተወስደዋል። ይህ የአሳታፊነት ጉዳይ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት በግልፅ የተደነገገ በመሆኑ አማራጭ ሳይሆን ግዴታም ነው። በመሆኑም በቀጣይም ተጠናክሮ ይቀጥላል።

## 7.3. የዋና ርዕስ ትንተና፡- ድህነትን ማጥፋትና ብልጽግናን ማስፋፋት

የመንግስት የፖሊሲ አቅጣጫዎች፡- የኢትዮጵያ መንግስት የልማት ዓላማ ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ የመሠረተ-ልማት፣ ማህበራዊ ልማት፣ የአካባቢ ልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በማፋጠን ድህነትን ማጥፋት እና የዜጎችን ብልፅግና ማረጋገጥ ነው። ከዚህ አንፃር እ.ኤ.አ. በ2025 ኢትዮጵያን ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍ መንግስት ሀገራዊ ራዕይ አስቀምጦ እየሠራ ይገኛል። ሁሉም የመንግስት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶች እና ፕሮግራሞች የተጀመረውን የህዳሴ ጉዞ ለማፋጠን፣ ድህነትን በማጥፋትና የዜጎችን ብልፅግና በማረጋገጥ ላይ ያተኮሩ ናቸው።

የመንግስት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች በተቀናጀና በተደራጀ አግባብ ሥራ ላይ በዋሉባቸው ባለፉት አሥራ-አምስት ዓመታት ዜጎችን በየደረጃው ተጠቃሚ ያደረጉ ስኬታማ የልማት ውጤቶች ተመዝግበዋል። እነዚህ የልማት ውጤቶች ሥራ አጥነትንና ድህነትን በመቀነስ ረገድ ቁልፍ ሚና ተጫውተዋል። በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በየአምስት ዓመቱ በተካሄዱ የቤተሰብ ገቢና የፍጆታ ወጪ እንዲሁም የኑሮ ደህንነት እና የዲሞግራፊና ጤና ጥናቶች መሠረት የኢትዮጵያ የድህነት መጣኔ በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል። በመሠረተ-ልማት፣ በትምህርት እና በጤና ከፍተኛ ስኬቶች ተመዝግበዋል። እነዚህን ስኬታማ ውጤቶች አጠናክሮ በማስቀጠል ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. በ2030 ድህነትን ከነሁሉም መገለጫዎቹ ለማጥፋት የተቀመጠውን ዓለም አቀፍ ግብ ማሳካት እንደምትችል ማሳያዎች ናቸው።

ከፍ ብሎ ለመግለፅ እንደ ተሞከረው ድህነትንና ሥራ አጥነትን ከመቅረፍ አንፃር እስከ 2007 የበጀት ዓመት መጨረሻ የተከናወኑ የልማት ሥራዎች ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል። ይሁን እንጂ አሁንም በኢትዮጵያ ያለው የድህነት መጣኔ እና ሥራ አጥነት በጣም ሰፊ ነው። በተለይም የሴቶችና የወጣቶች ሥራ አጥነት በጣም ከፍተኛ ነው። ይህም በቀጣይ ፈጣንና ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ መሠረተ-ልማት፣ ማህበራዊ ልማት እና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በማስቀጠል ድህነትንና ሥራ አጥነትን በፍጥነት ለመቀነስ ከፍተኛ ርብርብ የሚጠይቅ ነው። ከዚህ አንፃር ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ እና የዘላቂ ልማት ግቦችን በማስተሳሰር የተዘጋጀውና በመንግስት ፀድቆ በትግበራ ላይ በሚገኘው ሁለተኛው የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለሴቶችና ለወጣቶች ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷል።

የማስፈፀሚያ መንገዶች፡- ሁሉን አቀፍ እና መሠረተ ሰፊ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ መሠረተ-ልማት፣ ማህበራዊ ልማት፣ የአካባቢ ልማት እና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በማፋጠን ድህነትን ለማጥፋት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴዎችን ለማስፈፀም የኢትዮጵያ መንግስት የሚከተለው የሀብት ክፍፍል መንገድ ህገ-መንግስቱን መሠረት ያደረገ፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሚዘጋጅና ጊዜውን ጠብቆ ወቅታዊ በሚደረግ ቀመር የተደገፈ ሲሆን በጣም ፍትሀዊ የሚባል ነው። እንዲሁም የወጪ በጀት ድልድሉ የፊስካል ፖሊሲውን ተከትሎ በየበጀት ዓመቱ የሃብት ክምችትን ለሚፈጥሩ የኢንቨስትመንት ወጪዎች ቅድሚያ በመስጠት የሚፈፀምና ከጠቅላላ የመንግስት ወጪ ውስጥ በአማካይ 70 በመቶ ያህሉ ድህነትን በመቀነስ ረገድ ቁልፍ ሚና ለሚጫወቱ አምስት የልማት ዘርፎች ማለትም ለትምህርት፣ ለጤና፣ ለግብርና፣ ለውሀና ሳኒቴሽን እና ለገጠር መንገድ ግንባታ እንዲውል የሚደረግ ነው።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ለሁሉም ኢትዮጵያውያን የትምህርት፣ የጤና፣ የንጹህ መጠጥ ውሃ፣ የመኖሪያ ቤት፣ የምግብና የማህበራዊ ዋስትና አገልግሎት እንዲኖር መንግስት ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ እንዳለበት ይደነግጋል። ይህንን ድንጋጌ ተፈፃሚ ለማድረግ መንግሥት የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች የማህበራዊ አገልግሎቶችን ለህዝቦች በማቅረብ ፍትሀዊ ተደራሽነት እንዲኖራቸው ለማድረግ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሀብት እየመደበ እና ተፈፃሚነቱን እያረጋገጠ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። በዚህም በማህበራዊ ልማት ዘርፍ ስኬታማ ውጤቶች ተመዝግበዋል።

በሌላ በኩል መንግስት ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት ፈጣንና ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ የመሠረተ-ልማት፣ የማህበራዊ ልማት፣ የአካባቢ ልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ለማረጋገጥ፣ ኢትዮጵያን እ.ኤ.አ. በ2025 ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍ፣ ድህነትን ለማጥፋት እና የተጀመረውን የትራንስፎርሜሽንና የህዳሴ ጉዞ ለማፋጠን የሀገር ውስጥ ሀብት የማሰባሰብ አቅሙን በማጠናከር ላይ ይገኛል። በዚህም መሠረት የሀገሪቱ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ በ2002 የበጀት ዓመት ብር 53.9 ቢሊዮን የነበረ ሲሆን ከአምስት ዓመት በኋላ በ2007 የበጀት ዓመት መጨረሻ ብር 186.6 ቢሊዮን ደርሷል። እንዲሁም በ2008 የበጀት ዓመት መጨረሻ ወደ ብር 231.8 ቢሊዮን አድጓል። ይህ በየጊዜው እያደገ የመጣ የሀገር ውስጥ ገቢ የማሰባሰብ አቅም ኢትዮጵያ በራሷ አቅም ሰፋፊ የልማት ፕሮጀክቶችን ለማካሄድ አስችሏታል።

እንዲሁም የሀገር ውስጥ ቁጠባን ለማሳደግ በትኩረት ተይዞ

በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች የተደራጁና የተቀናጁ የልማት ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው። ከዚህ አንፃር የቁጠባ ባህልን ለማሳደግ ህብረተሰቡን ማስተማርና ማነሳሳት፣ የኢኮኖሚ ዕድገት ማፋጠንና በዚህም የሥራ ዕድሎችን ማስፋፋት፣ የፋይናንስ ተቋማትን በማስፋፋት ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ፣ የግል እና የመንግስት ማህበራዊ ዋስትና አገልግሎቶችን ማጠናከር፣ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቁጠባ ቦንድ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ለሽያጭ ማቅረብ፣ የመኖሪያ ቤት ቁጠባ እና የኢንቨስትመንት መሣሪያዎች የቁጠባ ፕሮግራሞችን ማጠናከር፣ የመንግስት ወጪን በዋነኝነት የካፒታል ክምችት ለሚፈጥር የኢንቨስትመንት ወጪ በመመደብ በቅልጥፍና እና በውጤታማነት ለታለመለት የልማት ሥራ እንዲውል ለማድረግ ከፍተኛ የልማት ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው።

የሥርዓተ ፆታ ዕኩልነት፡- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል መሆናቸውን በአንቀፅ 25 ይደነግጋል። እንዲሁም ስለ ሴቶች እኩልነትና መብት በሚደነግገው አንቀፅ 35 ሴቶች በኢኮኖሚ ልማት፣ በማህበራዊ ልማትና እና በፖለቲካ ዘርፍ በሚደረጉ ማናቸውም እንቅስቃሴዎች ከወንዶች እኩል መብት እንዳላቸው ያስቀምጣል። እነዚህን ህገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ለማድረግ የሴቶችን እኩልነትና መብት ይበልጥ ለማረጋገጥ የሴቶች ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና የልማት ፓኬጅ ተቀርፆ ሥራ ላይ ውሏል። ከዚህ በተጨማሪ በአለፉት የመንግስት ሥርዓቶች ሴቶች ያጧቸውን የሥርዓተ-ፆታ ዕኩልነት መብቶች የሚያካክሱ እርምጃዎች (Affirmative Actions) የሚወሰዱባቸው የህግ አግባቦች በግልፅ ተቀምጠዋል። የሴቶችን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና የልማት ፓኬጅ ተፈፃሚ ለማድረግም ተቋማዊ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በመዘርጋትና አስፈላጊውን የሰው ኃይል በመመደብ መንግስት በዕቅድ የተደገፉ የልማት ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል። ሴቶችም በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና በፖለቲካ እንቅስቃሴዎች እየተሳተፉ ይገኛሉ።

በተመሳሳይ የኢትዮጵያ መንግስት የወጣቶችን ፖሊሲና የልማት ፓኬጅ በማዘጋጀት ተቋማዊ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን ዘርግቶ አስፈላጊውን የሰው ኃይል በመመደብ ፖሊሲውንና የልማት ፓኬጁን ተፈፃሚ በማደረግ ላይ ይገኛል። ይሁን እንጂ በወጣቶችና በሴቶች አካባቢ የሚታየው ሥራ አጥነት በጣም ከፍተኛ ነው። ይህንን የሥራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ መንግስት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። በዚህም መሠረት በመደበኛነት ከሚካሄዱ የልማት ሥራዎች በተጨማሪ የኢትዮጵያ መንግስት በ2009 የበጀት ዓመት ለወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጠራ የብር 10 ቢሊዮን ተዘዋዋሪ ፈንድ በአዋጅ በማቋቋም በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ይህንኑ ተፈፃሚ ለማድረግ የተቀናጁና የተደራጁ የልማት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል።

መሠረተ-ልማት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን ለማፋጠን ወሳኝ ሚና ። በህዝቦች፣ በክልሎች እና በአካባቢዎች መካከል ጥብቅ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ትስስሮችን ለመፍጠር ያስችላል። ማህበራዊ አገልግሎቶችን ፈጣን በሆነ አግባብ ለህዝቦች ተደራሽ ለማድረግ የጎላ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን የአካባቢ ልማትን ለማስፋፋትም የሚጫወተው ሚና በጣም ከፍተኛ ነው። በአጠቃላይ መሠረተ ልማት የዘላቂ ልማት ግቦችን ከማረጋገጥ እና ድህነትን ከማጥፋት አንፃር የማይተካ ሚና የሚጨወት ሲሆን የግሉ ዘርፍ የኢኮኖሚው የዕድገት ሞተርነት ሚናውን እንዲወጣ እና ሀገራችን ከግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የምታደርገው መዋቅራዊ ሽግግር እንዲፋጠን ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። በመሆኑም መሠረተ ልማትን (ኢነርጂ፣ መንገድ፣ ባቡር፣ መስኖ፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ...ወዘተ) በፍጥነት ማስፋፋትና አስተማማኝ አገልግሎት ማረጋገጥ በትኩረት ተይዞ እየተሠራበት ያለ ወሳኝ የልማት እንቅስቃሴ ነው። በእስካሁን የልማት እንቅስቃሴ ውጤታማ እና ስኬታማ የመሠረተ ልማት ግንባታ ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን እነዚህ ውጤታማ የመሠረተ ልማት ሥራዎች ይበልጥ በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ ተጠናክረው ይቀጥላሉ።

የተለያዩ እና አስተማማኝ የመሠረተ ልማቶች አገልግሎትን በግብዓትነት በመውሰድ በተለይም ከታዳሽ የኃይል ምንጮች በአስተማማኝነት በሚመነጭና ከብክለት በፀዳ

የኤሌክትሪክ ኃይል የሚንቀሳቀሱ የአምራች ኢንዱስትሪዎች በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች በፓርኮች እና በክላስተሮች እየተደራጁ በመስፋፋት ላይ ። ይህም የኢትዮጵያን ኢንዱስትሪያላይዜሽን እና የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን እንደሚያፋጥን፣ ሰፊ የሥራ እድል እንደሚፈጥር እና የዜጎችን ገቢ በማሳደግ ድህነትን ለማጥፋት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ ይታመናል።

ኢትዮጵያ ሰፊ የገጸ-ምድርና የከርሰ-ምድር የውሀ ሀብት ባለቤት ናት። በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ መንግስት የሀገሪቱን የውሀ ኃብት በአግባቡ ለማልማትና ለመጠቀም የውሃ ዘርፍ አጠቃቀም ፖሊሲ ቀርፆ ተፈፃሚ በማድረግ ላይ ይገኛል። ከዚህ አንፃር የውሀ ሥነ ምህዳርን ለዘላቂ ልማት በመጠበቅ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ልማትን ለማፋጠን የተደራጁና የተቀናጁ የልማት ሥራዎች በመሥራት ላይ ናቸው። በሀገሪቱ የገጠር አካባቢዎች በከፍተኛ የህዝብ ንቅናቄ ከፍተኛ የአፈርና የውሀ ጥበቃ እንዲሁም የተፋሰስ ልማት ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው። በዚህም የደን ሽፋንን ማሳደግ፣ ትላልቅ ግድቦችን ከደለል መከላከል፣ የብዝሀ-ህይወት ሀብትን መጠበቅ፣ የገጸ-ምድርና የከርሰ-ምድር ውሀ ሀብትን ማበልፀግ...ወዘተ ተችሏል። በዚህም በገጠሩ አካባቢ የንፁህ መጠጥ ውሀ አቅርቦትን ለማሳደግ፣ በአነስተኛ አርሶ-አደሮች አካባቢ የመስኖ ሥራን በማስፋፋት የግብርናን ምርታማነት ማሳደግ፣ የምግብ ዋስትናን ማጠናከር እና ድህነትን መቀነስ ተችሏል።

የኢትዮጵያ መንግስት ከሀገራችን ድህነትን ከነሁሉም መገለጫዎቹ ለማጥፋት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ሲሆን የህዝቦች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ እና ዕኩልነታቸው እንዲረጋገጥ በቁርጠኝነት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ከዚህ አንፃር የሀገሩን ድንበር ለስደተኞች ክፍት በማድረግ በሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ ችግሮች ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ የጎረቤት ሀገሮች ስደተኞችን ተቀብሎ በማስተናገድ ላይ ይገኛል። ይህ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ዕውቅና የተሰጠው በጎ ተግባር የኢትዮጵያ መንግስት በህዝቦች ሰብዓዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች አያያዝ ዙሪያ የሚከተለውን የዕኩልነት መርህ ማሳያ ነው።

በአጠቃላይ ኢ.ኤ.አ. በ2030 ድህነትን ከነሁሉም መገለጫዎቹ ከምድረ-ገፅ ለማጥፋት የተቀመጠውን ዓለም አቀፍ ግብ በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ለማሳካት የኢትዮጵያ መንግስት በቁርጠኝነት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ይህንን ግብ ለማሳካት የኢትዮጵያ መንግስት በተለያዩ ደረጃዎች አስቀድሞ በሥራ ላይ ያዋላቸው የህግ ማዕፎች፣ ፖሊሲዎች እና አደረጃጀቶች አስቻይ ሁኔታዎች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ በአሁኑ ጊዜ መንግስት እየወሰዳቸው ያሉ የጥልቅ ተሀድሶና የሪፎርም እርምጃዎች በ2030 ድህነትን ለማጥፋት ተጨማሪ አቅሞች ናቸው።

እንዲሁም የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት፣ የማህበራዊ ልማት፣ የአካባቢ ልማት እና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በተቀናጀና በተደራጀ የረጅም ጊዜ ዕይታ በመምራት የተጀመረውን ሀገራዊ የህዳሴ ጉዞ ለማፋጠን፣ ድህነትን ከነሁሉም መገለጫዎቹ ለማጥፋትና የዜጎችን ብልፅግና ለማረጋገጥ መንግስት የዘላቂ ልማት ግቦችን በይዘትና በትግበራ ጊዜ ያስተሳሰረ የረጅም ዘመን (2008-2022) ሀገራዊ የልማት ዕቅድ በማዘጋጀት ላይ ይገኛል። የዚህ የረጅም ዘመን ሀገራዊ የልማት ዕቅድ የመጀመሪያ ምዕራፍ (2008-2012) የሆነው የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት ተዘጋጅቶና በመንግስት ፀድቆ በትግበራ ሂደት ላይ ይገኛል። ዕቅዱ ወደ ትግበራ ከገባ አንድ ዓመት ተኩል የሆነው ሲሆን በእስካሁን የትግበራ ሂደት መልካም የሚባሉ አፈፃፀሞች ተመዝግበዋል።

ፈታኝ ሁኔታዎች፡- የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ወደ ትግበራ የገባው የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በመጀመሪያው የትግበራ ዘመን (በ2008 የበጀት ዓመት) በኢትዮጵያ በተከሰተውና ሁሉንም የሀገራችን አካባቢዎች በስፋት ባዳረሰው ከፍተኛ ድርቅ ፈተናዎች ያጋጠሙት ቢሆንም መንግስት የድርቁን የጉዳት መጠን፣ ጥልቀትና ስፋት በዝርዝር በማጥናት ተፅዕኖዎችን በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ በመቋቋም የአንድም ሰው ህይወት ሳይጠፋ የኢኮኖሚውን ፈጣን ዕድገት፣ ማህበራዊ ልማትና የአካባቢ ልማት ማስቀጠል ተችሏል። በዕቅዱ ሁለተኛ የትግበራ ዘመንም በሀገራችን ውሀ አጠር እና አርብቶ-አደር አካባቢዎች ከፍተኛ ድርቅ ተከስቷል። ይህ የአየር ንብረት ለውጥን ተከትሎ በኢትዮጵያ አንዳንድ አካባቢዎች የተከሰተው ድርቅ የሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድና የዘላቂ ልማት ግቦች

በሙሉ አቅም ከማስፈፀምና ከመፈፀም አኳያ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ቀላል አይደለም።

በሌላ በኩል እ.ኤ.አ. በ2030 ድህነትን ከነሁሉ መገለጫዎቹ ከምድረ-ገፅ ለማጥፋት የተቀመጠውን ዓለም አቀፍ ግብ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ለማሳካት የማስፈፀም አቅም ውስንነት (በአመለካከት፣ በቴክኒካዊ ዕውቀት፣ በቴክኖሎጂ፣ በፋይናንስ) ትልቅ ፈተና ተደርጎ ይታያል። ይህንን የአቅም ውስንነት ለመቅረፍ በሀገሪቱ የተለያዩ የአስተዳደር ዕርከኖች በአመራር፣ በአስፈፃሚና በፈፃሚ ደረጃ የተጀመረውን የጥልቅ ተሀድሶ እና የሪፎርም ዕንቅስቃሴ አጠናክሮ በማስቀጠል በልማታዊ የፖለቲካል ኢኮኖሚ አቅጣጫ የአመለካከት ለውጥ መምጣቱን ማረጋገጥ፣ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በመፈተሽ ጉድለቶች መለየት እና አግባብነት ያላቸው የማስተካከያ ዕርምጃዎችን መውሰድ በትኩረት ተይዞ የሚሠራ ጉዳይ ይሆናል።

ከዚህ በተጨማሪ ብሔራዊ ቁጠባን ማሳደግ፣ የኢኮኖሚ ልማቱ የሚያመነጨውን የታክስ ገቢ በተደራጀ፣ በተቀናጀ እና ፍትሀዊ በሆነ አግባብ ማሰባሰብና ውጤታማ በሆነ አግባብ መጠቀምና የዓለም አቀፍ የልማት አጋርነትን ማጠናከር ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው።

## 7.4. የስድስቱ ዘላቂ የልማት ግቦች ዝርዝር ግምገማ

የ2030 የዘላቂ ልማት አጀንዳ በ17 ግቦችና በ169 ኢላማዎች የተደራጀ ነው። አስራ ሰባቱ የዘላቂ ልማት ግቦችም (1) ድህነትን ማጥፋት (2) ረሃብን ማጥፋት (3) ጤናማ ህይወትና ደህንነት (4) ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም (5) የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት (6) የንፁህ ውሃና የንፅህና አገልግሎት (7) አቅምን ያገናዘበ ታዳሽ ኢነርጂ (8) ምቹ ሥራና የኢኮኖሚ ዕድገት (9) ኢንዱስትሪ ፈጠራና መሠረተ ልማት (10) አድሏዊ ልዩነትን መቀነስ (11) ዘለቄታዊነት ያላቸው ከተሞችና መንደሮች መመሥረት (12) ዘለቀታዊነት ያለው የሃብት አጠቃቀምና የአመራረት ሥርዓት (13) የአየር ንብረት ለውጥ ለመቋቋም እርምጃ መውሰድ (14) የውሃ ስነ-ምህዳርን ለዘላቂ ልማት መጠበቅ (15) የመሬት ስነ-ምህዳርን ለዘላቂ ልማት መጠበቅ (16) ሰላም ፍትህና ጠንካራ ተቋማት (17) ዓለም አቀፋዊ ትብብር ለዘላቂ ልማት ናቸው።

እነዚህ የዘላቂ ልማት ግቦች ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ተጣጥመው እየተተገበሩ ይገኛሉ። በዓለም አቀፍ ደረጃ የዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 ክትትልና ግምገማን በሚመለከት እ.ኤ.አ. 29 ጁላይ 2016 ዓ.ም. የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ ባሳለፈው ውሳኔ A/RES/70/299) መሠረት የዘላቂ ልማት ግቦች የ2017 ዓ.ም. የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ ዋና ርዕስ ድህነትን ማጥፋትና እየተለወጠ ባለ ዓለም ውስጥ ብልፅግናን ማስፋፋት ነው።

ከዚህ አንፃር ዋናው ርዕሱን በሚመለከት ከፍ ብሎ ጠቅለል ያሉ ግምገማዎች ተቀምጠዋል። እ.ኤ.አ. የ2017 የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማው በዝርዝር የሚመለከታቸው የዘላቂ ልማት ግቦች ስድስት ሲሆኑ እነዚህም (1) ድህነትን ማጥፋት (2) ረሀብን ማጥፋት (3) ጤናማ ህይወትና ደህንነት (4) የሥርዓተ-ፆታ ዕኩልነት (5) መሠረተ-ልማት ግንባታና የኢንዱስትሪ ፈጠራ እና (6) የውሀ ሥነ ምህዳርን ለዘላቂ ልማት መጠበቅ ። እንዲሁም ዓለም አቀፋዊ ትብብር ለዘላቂ ልማት ከእነዚህ ስድስት የዘላቂ ልማት ግቦች ጋር በማገናዘብ ተገምግሟል። በዚህም መሠረት በኢትዮጵያ ድህነትን ከማጥፋት እና ብልፅግናን ከማስፋፋት አኳያ የስድሰቱ ዘላቂ የልማት ግቦች አፈፃፀም ግምገማ እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 7.4.1. ግብ 1፡- ድህነትን ማጥፋት

የመንግስት ፖሊሲ አቅጣጫዎች፡- የኢትዮጵያ መንግስት ዋነኛው የልማት አጀንዳ ድህነትን ማስወገድ ነው። የመንግስት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ፈጣን፣ መሰረተ-ሰፊና ሁሉን-አቀፍ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ መሰረተ-ልማት፣ ማህበራዊ ልማት፣ የአካባቢ ልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በማረጋገጥ ድህነትን ማጥፋትና ሀገሪቱ የጀመረችውን የትራንስፎርሜሽን እና የህዳሴ ጉዞ ማፋጠን ነው።

እነዚህ የመንግስት ፖሊሲዎች፣ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች በሥራ ላይ በዋሉባቸው ባለፉት 15 ዓመታት በኢኮኖሚ ዕድገት፣ በመሠረተ ልማት፣ በማህበራዊ ልማት፣ በአካባቢ ልማትና በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በርካታ ስኬቶች ተመዝግበዋል። ኢኮኖሚው በተከታታይ በከፍተኛ ፍጥነት አድጓል። መሠረተ-ልማትና ማህበራዊ ልማት ተስፋፍቷል። በአካባቢ ልማት ዙሪያ ለረጅም ጊዜ በተሠሩ

የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በተለይ በሀገሪቱ ገጠር አካባቢ የሚኖረው ህዝብ በአካባቢ ልማት ላይ በቂ ግንዛቤ ይዞ በሙሉ ዕምነትና ተነሳሽነት እንዲሁም በተቀናጀና በተደራጀ ህዝባዊ እንቅስቃሴ በመንግስት እየተመራ በአፈርና ውሀ ጥበቃ፣ በብዝሀ-ህይወት ጥበቃ እና በተፋሰስ ልማት ለሌሎች ሀገሮች ተምሳሌት የሚሆን የልማት ሥራ እያከናወነ ይገኛል። በዚህም የግብርናን ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ እያሳደገ እና የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ሥራ እያጠናከረ ይገኛል። በተመሳሳይ የዲሞክራሲ ተቋማትን አቅም በማጠናከር፣ የህዝብ ተሳትፎን በማጎልበት፣ በመሠረታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ሀገራዊ መግባባት በመፍጠር ለዘላቂና የተረጋጋ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ አስተማማኝ መሠረት ለመጣል ተችሏል።

ህዝቡን በየደረጃው በማሳተፍ እና ፍትሀዊ ተጠቃሚ በማድረግ ባለፉት 15 ዓመታት በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች በተከናወኑ የልማት ሥራዎች በተመዘገበው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት፣ መሠረተ ልማት እና የማህበራዊ ልማት ውጤቶች ተመዝግበዋል። በዚህም የዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢ ፈጣን ዕድገት አሳይቷል። ድህነት በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል። ለምሳሌ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የቤተሰብ ገቢና የፍጆታ ወጪ ጥናት መሠረት አጠቃላይ ድህነት እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1992 ከነበረበት 44.2 በመቶ በ1997 ወደ 38.7 በመቶ፣ በ2003 ወደ 29.6 በመቶ እና በ2007 ወደ 23.4 እንደሚወርድ ተገምቷል። እንዲሁም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት (በ2012 መጨረሻ) ወደ 16.7 በመቶ እንደሚቀንስ ትንበያዎች ያሳያሉ።

የዘላቂ ልማት ግቦችን በማስተሳሰር የተዘጋጀውን ሁለተኛው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በተቀመጠለት ዓላማ እና ግቦች መሠረት ተፈፃሚ በማድረግ በሁሉም የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጮች የሥራ ሥምሪትን በማሳደግ፣ ምርታማነትን በማሻሻል፣ ጥራትንና ተወዳዳሪነትን በማረጋገጥ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚጠበቀውን የመዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት የተደራጁና የተቀናጁ የልማት ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው። የሁለተኛው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ባለፉት ዓመታት የተመዘገበውን ሁሉን-አቀፍ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በማስቀጠል የሀገራችንን የህዳሴ ጉዞ ከማሳካት፣ የኢኮኖሚ መሠረተ-ልማቶችንና ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለዜጎች በፍጥነትና በጥራት ተደራሽ ከማድረግ፣ የሥራ ስምሪትን በማሳደግ ድህነትን ትርጉም ባለው ሁኔታ ከመቀነስና በሂደትም ከማስወገድ፣ የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ከማሻሻል እና በ2017 ኢትዮጵያን ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተቀመጠውን ሀገራዊ ራዕይ ከማሳካት አንፃር ቁልፍ የመዳረሻ ምዕራፍ ነው።።

**ዝርዝር አፈጻጸም፡-** በ2008 የበጀት ዓመት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአማካይ በ8 በመቶ አድጓል። ግብርና፣ ኢንዱስትሪና አገልግሎት በቅደም ተከተል በ2.3 በመቶ፣ በ20.6 በመቶ እና በ8.7 በመቶ አድገዋል። በበጀት ዓመቱ የተመዘገበው ዕድገት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የአየር ንብረት ለውጥ ባስከተለው ከፍተኛ ድርቅ በተፈተነበት እና የዓለም ኢኮኖሚ መቀዛቀዝ ባሳየበት ወቅት በመሆኑ ፈጣን የሚባል ነው።




በ2008 በኢትዮጵያ የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት በዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም እ.ኤ.አ. በጥቅምት 2016 ዓ.ም. ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ትንበያ መሠረት ከሠሀራ በታች የሚገኙ ሀገራት ያስመዘግቡታል ተብሎ ከሚጠበቀው የ1.4 በመቶ አማካይ የኢኮኖሚ ዕድገት እና በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ የዓለም ሀገራት ካስመዘገቡት የ3.7 በመቶ ዕድገት ጋር ሲነፃፀር በኢትዮጵያ የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት ከእጥፍ በላይ ነው። በተመሳሳይ የዓለም ባንክ እ.ኤ.አ. በ2016 ባወጣው የዓለም ኢኮኖሚ ትንበያ ሪፖርት መሰረት ሀገራችን ያስመዘገበችው የኢኮኖሚ ዕድገት ከሰሀራ በታች የሚገኙ የአፍሪካ ሀገራት ያስመዘግቡታል ተብሎ ከሚጠበቀው የ2.5 በመቶ አማካይ የኢኮኖሚ ዕድገት አንጻር ሲለካ በ3 ዕጥፍ የላቀ መሆኑን መረጃው ያመለክታል።

እንዲሁም በ2008 በጀት ዓመት በኢትዮጵያ የተመዘገበው የ8 በመቶ ዓመታዊ አማካይ የኢኮኖሚ ዕድገት በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሀገራት እ.ኤ.አ.በ2030 ምቹ ሥራና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋጥ በየዓመቱ ማስመዝገብ ካለባቸው ቢያንስ የ7 በመቶ የኢኮኖሚ ዕድገት ከፍ ያለ በመሆኑ በዘላቂ ልማት ግብ 8 የተቀመጠውን በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሀገራት በየዓመቱ እንዲያሚሉ የሚጠበቅባቸውን ዓመታዊ የጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት ኢላማ በአስተማማኝ ያሳካ ነበር። ድህነትን ለመቀነስና በሂደትም ከነሁሉም መገለጫዎቹ ለማስወገድ የኢትዮጵያ መንግስት በቁርጠኝነት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ከዚህ አንፃር ፖሊሲዎቹን ለማስፈፀም የኢትዮጵያ በጀት ድህነት ተኮር ሲሆን ይህንን ተከትሎ ከበጀት አመዳደብና አጠቃቀሙ ውስጥ በአማካይ ወደ 70 በመቶ የሚጠጋው ወጪ በዋነኛነት ዕድገትን በሚያፋጥኑና ድህነትን ለማጥፋት ቁልፍ ሚና ባላቸው የግብርና፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የውሃና ሳኒቴሽን እና የገጠር መንገድ ዘርፎች ላይ ያተኮረ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ መንግስት የወጪ በጀቱን በአብዛኛው የካፒታል ክምችትን በሚፈጥሩ የካፒታል ኢንቨስትመንቶች ላይ እንዲያተኩር እና የክልሎችን የተመጣጠነ ልማት ለማረጋገጥ እየሠራ ይገኛል። በዚህም መሠረት ከጠቅላላ የመንግስት ወጪ ውስጥ በየዓመቱ ከ50 በመቶ በላይ የሚሆነው ለካፒታል ወጪ እየዋለ ሲሆን ቀሪው ለመደበኛ ወጪ መሸፈኛ እየዋለ ነው። ይህ የመንግስት ወጪ ድልድል የሀገሪቱን የፊስካል ፖሊሲ አቅጣጫ ተከትሎ በአብዛኛው ተጨማሪ ኃብት በሚፈጥሩ የኢንቨስትመንት ሥራዎች እና ቁጠባን የበለጠ በሚያጠናክሩ ዘርፎች እየዋለ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። በአጠቃላይ በ2008 በጀት ዓመት የተመዘገበው የድህነት ተኮር ዘርፎች ወጪ በ2007 በጀት ዓመት ከተመዘገበው አፈፃፀም ጋር ሲነጻጸር የ26.3 በመቶ ዕድገት አሳይቷል። በበጀት ዓመቱ የሀገሪቱ የበጀት ጉድለት መጣኔ 2.4 በመቶ ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን የዋጋ ንረትም በነጠላ ተገድቦ እንዲቆይ ተደርጓል።

የዘላቂ ልማት ግቦችን በማስተሳሰር ተዘጋጅቶና በመንግስት ፀድቆ ወደ ሥራ የገባውን የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በ2009 የበጀት ዓመትም በተደራጀ እና በተቀናጀ አግባብ በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ተፈፃሚ የማድረጉ ሥራ ተጠናክሮ ቀጥሏል። የትግበራ አፈፃፀሙም በቅርብ ክትትል ተደግፎ በየደረጃው እና በየጊዜው እየተገመገመ ይገኛል። በዚህም መሠረት ኢኮኖሚው በ2008 የበጀት ዓመት በሀገሪቱ ተከስቶ የነበረው አስከፊ ድርቅ ያስከተለውን ተፅዕኖ እና በ2009 የበጀት ዓመት በውሀ-አጠር አርብቶ አደሮች አካባቢ የተከሰተውን ተመሳሳይ ድርቅ በመቋቋም እንዲሁም መልካም ዕድሎች አሟጥጦ በመጠቀም ለበጀት ዓመቱ የተቀመጠለትን የ11 በመቶ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት እንደሚያሳካ የስድስት ወራት የአፈፃፀም መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ሠፊ የሥራ ዕድል እየፈጠረና ዜጎችን በየደረጃው ፍትሀዊ ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል።

የግብርናው ዘርፍ ለኢኮኖሚ ዕድገት ዋና ምንጭ ሆኖ እንዲቀጥል የተጠናከረ የኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠትና አስፈላጊ የግብርና ግብዓቶችን በማቅረብ፣ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን ለማሳደግ የተደራጀ እና የተቀናጀ የኢንቨስተመንት እንቅስቃሴ በማካሄድ የግል ኢንቨስትመንትን ማበረታታት፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ማስፋፋት፣ የተፈጥሮ ኃብት ጥበቃና ልማት ሥራዎችን ማጠናከር እና በመንግስት የሚካሄዱ የልማት ፕሮግራሞችንና አነስተኛ ኩባንያዎችን ማጠናከር በትኩረት ተይዞ እተሠራ ያለ ሥራ ነው። በዚህም የተለያዩ ህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሰፊ የሥራ ዕድሎች ተፈጥረዋል። የተፈጠሩት የሥራ ዕድሎች በተለይም ከሥራ አጥነት አንፃር ከፍተኛ ችግር ያለባቸውን እና በዚህም ይበልጥ ተጎጂ የሆኑትን የማህበረሰብ ክፍሎች (ወጣቶችንና ሴቶችን) ተጠቃሚ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ እየተሰራ ይገኛል።

ከማህበራዊ ደህንነት እና ጥበቃ አኳያ በሥራ ላይ ያለውን ሥርዓት መሠረት በማድረግ የማህበራዊ ደህንነት አገልግሎትን ማስፋፋትና የዜጎችን ተጠቃሚነት የማረጋገጥ እንዲሁም የማህበራዊ ዋስትና ሽፋንን በማሳደግ በተለይ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ ሌሎች ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በሀገሪቱ ሁለንተናዊ ልማት ውስጥ ተሳታፊ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራ በትኩረት እየተሠራ ይገኛል። በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት በገጠር 1,113,676፣ በከተማ 115,120

በድምሩ 1,228,796 የመሥራት አቅም ለሌላቸው ዜጎች የልማታዊ ሴፍቲኔት የቀጥታ ድጋፍ በማድረግ ከድህነት የሚወጡበትን ሁኔታ የማመቻቸት ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው። በዚሁ መሠረት ለ886,000 ዜጎች (አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ ሴቶችና ህፃናትና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች) ልማታዊ ሴፍቲኔት የቀጥታ ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ በገጠር ለሚኖሩ ለ1,113,676 ዜጎች (አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች) የቀጥታ ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል።

ከሴፍቲኔት ፕሮግራም ጎን ለጎን በማህበራዊ ችግሮች ለተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች የማህበራዊ ደህንነት አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለማድረግ በተያዘው ዕቅድ መሠረት በ2008 በጀት ዓመት 584,849 እንዲሁም በ2009 በጀት ዓመት የመጀመሪያ 6 ወራት ጊዜ ውስጥ 196,801 በድምሩ 781,650 (51 በመቶ ሴቶች) የህብረተሰብ ክፍሎች የተለያዩ የማህበራዊ ደህንነት አገልግሎቶች (የአመራርና ምክር፣ የሙያ ስልጠና፣ የቁሳቁስ፣ የገንዘብ ድጋፍና የማቋቋም) ተሰጥተዋል። በአገልግሎቱ ተጠቃሚ ከሆኑት መካከል 224,703 አረጋውያን፣ 78,739 አካል ጉዳተኞች፣ 20,367 ጎዳና ተዳዳሪዎች፣ 7,350 ሴተኛ አዳሪዎች፣ 7,655 ለምኖ አዳሪዎች፣ 274,334 ህፃናትና ቤተሰብ፣ 113,819 ሌሎች በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ይገኙበታል።

የአካላዊ ተሃድሶ አገልግሎትን ከማጠናከር አንፃር በአለፉት አንድ ዓመት ተኩል ውስጥ ለ99,397 አካል ጉዳተኞች የአካላዊ ተሃድሶ አገልግሎት በመስጠት አገሪቷ ድህነትን ለመቀነስ በምታደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ በታቀደው መሠረት በድምሩ 76,978 አካል ጉዳተኞች አገልግሎቱን እንዲያገኙ ተደርጓል። ከተሰጡት አገልግሎቶች መካከል 5,108 አካል ጉዳተኞች የዊልቸር ድጋፍ፣ ለ29,724 አካል ጉዳተኞች የአካል ድጋፍ፣ ለ13,847 የሰው ሰራሽ አካል ድጋፍ፣ ለ12,185 የአካል ድጋፍ ጥገና አገልግሎት፣ ለ13,274 አካል ጉዳተኞች የፊዚዮቴራፒ አገልግሎት፣ ለ1,623 ነጭ በትርና ለ1,074 የብሬል የመሳሰሉት ድጋፎችን እንዲያገኙ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪ አገልግሎቱን ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ የአካላዊ ተሃድሶ ማዕከላት ቁጥርን ከፍ ለማድረግ በተያዘው አቅጣጫ መሠረት 16 የነበረውን የአካላዊ ተሃድሶ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ቁጥር ለማሳደግ በተደረገው እንቅስቃሴ ሁለት ማዕከላት (በአፋር እና ሶማሌ ክልሎች) ግንባታቸው በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል። በቀጣይ ቀሪ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ተጨማሪ 6 ማዕከላትን በየክልሎቹ በመገንባት አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል።

ድህነትን የማጥፋት ግብ ለማሳካት በተሰራው ስራና እየተመዘገበ ባለው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ምክንያት በከተሞችና በገጠር የሚታየውን የሥራ አጥነት መጣኔ መቀነስ ተችሏል።የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ባለፉት ዓመታት ባወጣቸው አገራዊ የሰው ኃይል ጥናቶች (National Labour Force Survey) መረጃዎች መሠረት በኢትዮጵያ ያለው የሥራ ስምሪት ሁኔታ እየተቀየረ እንደመጣ ያሳያል። ባለፉት ሶስት ተከታታይ አገራዊ የሰው ኃይል ጥናቶች (1991፣ 1997፣ 2005) ውጤት መሠረት የሥራ አጥነት መጣኔ በ1991 በአገር አቀፍ ደረጃ 8 በመቶ የነበረ ሲሆን በ1997 ወደ 5 በመቶ እና በ2005 ወደ 4.5 በመቶ ዝቅ ብሏል።

በከተማ ያለው የሥራ አጥነት ሁኔታ በወጣቶች እና ሴቶች አካባቢ በብዛት የተከማቸ ነው።ይህን በከተሞች ከድህነት ወለል በታች እየኖሩ ያሉትን የህብረተሰብ ክፍሎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ከምግብ ዋስትና እጦትና ተጋላጭነት ማላቀቅና በረዥም ጊዜ የኑሮ ሁኔታቸውን በማሻሻል ከድህነት እንዲወጡ እና የራሳቸውን ስራ ፈጥረው ገቢ እንዲያገኙ ለማድረግ በመንግስት አቅጣጫ ተቀምጦ የከተማ የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ተቋም በማቋቋም እና በተመረጡ ከተሞች የከተማ የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራምን ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ ለመተግበር 10 ቢሊዮን ብር ተመድቦ በሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች በተመረጡ ከተሞች ለመጀመር የሚያስችለውን አደረጃጀትና ሌሎች ቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ማጠናቀቅ ተችሏል።

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የሥራ ስምሪት አገልግሎትን በማጠናከር ድህነትን ለማጥፋት በተያዘው ዕቅድ መሠረት በ2008 በጀት ዓመት ለ1,050,000 ዜጎች እንዲሁም በ2009 በጀት ዓመት ግማሽ ዓመት ለ595,000 ዜጎች በድምሩ 1,645,000 ዜጎች ድጋፍ በመስጠት

በሀገራቸው ሥራ ላይ እንዲሰማሩ በታቀደው መሠረት ከዕቅዱ በላይ 3,455,395 ሥራ ፈላጊዎች ድጋፍ አግኝተው ሥራ ላይ እንዲሰማሩ በማድረግ ራሳቸውን ጠቅመው ሀገሪቷ ድህነትን ለማጥፋት በምታደርገው እንቅስቃሴ ውሰጥ ጉልህ አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ተደርጓል። እንዲሁም በ2008 በጀት ዓመት ለ1,000,000 እንዲሁም በ2009 በጀት ዓመት የመጀመሪያው 6 ወራት ጊዜ ውስጥ ለ449,882 በድምሩ 1,449,882 ሥራ ፈላጊዎች የምክርና የአመራር አገልግሎት ለመስጠት በታቀደው መሠረት 1,410,340 ሥራ ፈላጊዎች የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል።

በአገራችን በተመዘገበው ሁሉን አቀፍ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ባለፉት ስድስት ዓመታት (2003-2008) የዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢ በአማካይ የ13.8 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ በ2002 ከነበረበት የ373 የአሜሪካን ዶላር በጊዜው የገበያ ዋጋ በ2008 ወደ 794 የአሜሪካን ዶላር ከፍ ብሏል። ይህ አፈጻጸም በፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት፣ ማህበራዊ ልማት እና የአደጋ ተጋላጭነትን የመቋቋም አቅም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ከተደረገ በ2017 ዓ.ም ሀገራችንን ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተቀመጠውን ሀገራዊ ራዕይ ለማሳካት የሚያስችል ነው። የድህነት ምጣኔው በፍጥነት እየቀነሰ የመጣው በዋናነት በተመዘገበው መሠረተ ሰፊና ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት፣ከዕድገቱ በተጨማሪ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ ፕሮግራሞች፣ የማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋት በቀጥታና በተዘዋዋሪ ድህነትን ለመቀነስ አስዋጽኦ እንደነበራቸው የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ።

በአጠቃላይየኢትዮጵያመንግስትድህነትተኮርፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ዕቅዶችንና ፕሮግራሞችን አውጥቶ በበጀት በመደገፍ እና የልማት ኃይሎችን አስተባብሮ በመምራት በኢኮኖሚ ዕድገት፣ በመሠረተ-ልማት፣ በማህበራዊ ልማት፣ በአካባቢ ልማት እና በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ስኬታማ ውጤቶችን እያስመዘገበ ይገኛል። በዚህም የነፍስ ወከፍ ገቢ እና ፍትሀዊ የልማት ተጠቀሚነት እያደገ መጥቷል።

መንግስት የሚከተላቸው ድህነት ተኮር አጠቃላይ የግብርና-መር ፖሊሲና ስትራቴጂ፣ የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ፣ የግብርናና የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ፣ የማህበራዊ ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፣ በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ጉዳዮች፣ የልማታዊ ሴፍቲኔት እና የመሠረተ ልማት ፕሮግራሞች...ወዘተ. አጠቃላይ የልማት እንቅስቃሴውን ከማፋጠን፣ በዜጎች መካከል ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልን እና ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ እና በዚህም ድህነትን ትርጉም ባለው ሁኔታ ከመቀነስ አንፃር ወሳኝ ሚና እየተጫወቱ ነው። የዘላቂ ልማት ግቦች ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ተሳስረው በትግበራ ላይ በዋሉባቸው በአለፉት 18 ወራት በድህነትና በኑሮ ደህንነት ግቦች የተመዘገቡ የአፈፃፀም ውጤቶች የሚያመለክቱት አገራችን ድህነትን የማጥፋት የዘላቂ ልማት ግብ ለማሳካት ትክክለኛውን የፖሊሲና የስትራቴጂ አቅጣጫ የተከተለች መሆኑን ነው።

ድህነትን ለማጥፋት የተዘረጉ የማስፈጸሚያ መንገዶች፡- ድህነትን በማጥፋት ላይ ያተኮሩ የመንግስት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና የልማት ፕሮግራሞች የኢትዮጵያ ህዝቦች ካሉበት ድህነትና ኋላቀርነት የሚላቀቁባቸው ዋና መንገዶች ናቸው። የሀገር ውስጥ ገቢ የማሰባሰብ አቅምን በመገንባት እነዚህን ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ድህነት ተኮር የመንግስት ወጪ አደላደልና ያልተማከለ አስተዳደር ሥርዓት መተግበር፣ ከፍተኛ የፖለቲካ ቁርጠኝነት ባለው ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ መንግስት ኢኮኖሚውን በተቀናጀና በተደራጀ አግባብ የልማት ኃይሎችን አስተባብሮ መምራት፣ የገበያ ጉድለቶች ባሉባቸው የልማት መስኮች በተመረጠ አግባብ ጣልቃ በመግባት የኢኮኖሚ ልማቱን በዘላቂነት ማፋጠን እና የግሉን ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን ልማታዊ ተሳትፎ በማጠናከር የሚጠበቅበትን ሚና እንዲጫወት ማስቻል ዋና ዋናዎቹ የማስፈፀሚያ መንገዶች ናቸው። እነዚህን ትስስርና ተመጋጋቢነት ያላቸው የማስፈፀሚያ መንገዶች በተቀናጀና በተደራጀ አግባብ ተፈፃሚ በማድረግ ዜጎች በኢኮኖሚ ልማቱ እኩል ተሳታፊና ፍትሀዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማስቻል ድህነትን ማጥፋት፣ የኢትዮጵያን የህዳሴ ጉዞ ማፋጠን እና የህዝቦችን ብልፅግና ማረጋገጥ ይቻላል።

በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ መንግስት በሀገራችን ያለውን አስካፊ ድህነት ለማጥፋት ሀገራችን የጀመረችውን የትራንስፎርሜሽንና የህዳሴ ጉዞ በማፋጠን በ2017 ኢትዮጵያን ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ

ለማሰለፍ እና በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የዘላቂ ልማት ግቦችን በተቀመጠላቸው የጊዜ ማዕቀፍ መሠረት ለማሳካት ከፍተኛ የልማት ሥራዎች እየተካሄዱ ነው። ከዚህ አንፃር በሁለተኛው የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012) ሀገሪቱ ከያዘችው የብር 2.30 ትሪሊዮን የወጪ ምደባ ግብ 70 በመቶ የሚሆነው (ብር 1.61 ትሪሊዮን) ወጪ የኢኮኖሚ ዕድገትን በሚያፋጥኑና ድህነትን በሚቀንሱ ዘርፎች (በጤና፣ በትምህርት፣ በንፁህ ውሀና ሳኒቴሽን፣ በገጠር መንገድ እና በግብርና) ላይ ተመድቦ ሥራ ላይ እንደሚውል ሰነዱ ያሳያል። ይህም የኢትዮጵያ መንግስት ህገ-መንግስቱን እና የህገመንግስቱ ድንጋጌዎችን ተፈፃሚ ለማድረግ የወጡ ህጎችን፣ ፖሊሲዎችን እና ፕሮግራሞችን መሠረት በማድረግ የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሀገራዊ የልማት ማዕቀፍ ጋር በማስተሳሰር ድህነትን ለማጥፋት ምን ያህል ቁርጠኛ እና በተግባርም ስኬታማ የልማት ስራዎችን እያከናወነ እንደሆነ የሚያመለክት ነው።

የፊስካልና የታክስ ፖሊሲዎችን በውጤታማነት በማስተዳደር የሀገር ውስጥ ገቢን ለማሳደግ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ሲሆን ከ2008-2012 ባለው የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የታክስ ገቢው ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ ወደ 17.2 በመቶ ለማሳደግ እየተሠራ ይገኛል። በዚህም የሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማስፈፀም በአምስት ዓመቱ የዕቅድ ዘመን በሀገር አቀፍ ደረጃ ይሰበሰባል ተብሎ በዕቅድ ከተያዘው የብር 2.01 ትሪሊዮን ጠቅላላ የመንግስት ገቢ ዕቅድ ውስጥ ከ96 በመቶ (ብር 1.93 ትሪሊዮን) በላይ የሚሆነው የሚሰበሰበው ከሀገር ውስጥ ገቢ ነው። በዚህም መሠረት የመንግስት ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ በ2007 ከነበረበት ብር 186.6 ቢሊዮን በ2008 የበጀት ዓመት የ24.2 በመቶ ዕድገት በማሳየት ወደ ብር 231.8 ቢሊዮን ከፍ ብሏል። እንዲሁም የምርምር አቅምን በማሳደግ በተለይም የግብርና እና የአምራች ኢንዱስትሪ ምርምር አቅምን በማጎልበት የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘቡ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የማፍለቅ፣ ከውጭ የሚገቡ ቴክኖሎጂዎችን የማላመድና ምርታማነትን በከፍተኛ ደረጃ የማሳደግ ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪ በተደራጀና በተቀናጀ ህዝባዊ ንቅናቄ (Community Mobilization) በቁጠባና ኢንቨስትመንት እንዲሁም በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እና በተፋሰስ ልማት በመንግስት መሪነትና አስተባባሪነት እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎች በዕርግጥም ሩቅ በማይባል ጊዜ ውስጥ ድህነትን ለማጥፋት እንዲሚቻል በግልፅ አሳይተዋል። እነዚህ የልማት ሥራዎች በከፍተኛ ደረጃ ተጠናክረው የቀጠሉ ሲሆን ህዝቡም በግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ዕምነት እና ባለቤትነት ይዞ በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ ልማቱን ለማፋጠንና ድህነትን ታሪክ ለማድረክ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

በአጠቃላይ የመንግስት የሰላም፣ የማረጋጋትና የመልሶ ግንባታ ፕሮግራሞች፣ በ1993 ከተደረገው ተሀድሶ በኋላ የወጡ የመንግስት ድህነት ተኮር ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች በሀገሪቱ ሁሉም አካባቢዎች በሥራ ላይ በዋሉባቸው ዓመታት ድህነትን ከመቀነስ አኳያ አመርቂ ውጤቶች ተመዝግበዋል። ይህም በሀገሪቱ የኑሮ ደህንነትና የድህነት ክትትል ሥርዓት መሠረት ከ1988 ጀምሮ በየአምስት ዓመቱ በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የተደረጉ የቤተሰብ ገቢና የፍጆታ ወጪና የኑሮ ደህንነት ክትትል የናሙና ጥናቶች ተረጋግጧል። እነዚህ የልማት እንቅስቃሴዎች በቅርቡ በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በተካሄዱ የአመራርና የፈፃሚ ተቋማት ጥልቅ የተሀድሶ ንቅናቄዎች የተለዩ ዕጥረቶችን በማስተካከል እና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በአሠራር፣ በአደረጃጀት እና በሰው ኃይል ዙሪያ አጠናክሮ በማስቀጠል በዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 ድህነትን ከነሁሉም መገለጫዎቹ ለማጥፋት የተቀመጠውን ግብ ማሳካት የሚያስችሉ የልማት ሥራዎች ይሠራሉ።

*ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች*:- በ2008 የጀት ዓመት በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በሀገሪቱ ተከስቶ የነበረውና በ2009 ዝናብ አጠር በሆኑ የአርብቶ አደር አካባቢዎች የተከሰተው ድርቅ በኢኮኖሚው ውስጥ ውስን ሀብትን በመሻማት፣ በሀገሪቱ የእንስሳት ሀብትና በአጠቃላይም በግብርናው የልማት እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል። እንዲሁም የዓለም ኢኮኖሚ መቀዛቀዝ በሀገሪቱ የወጪንግድ ገቢ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረ ነው። እነዚህ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ድህነትን ለማጥፋት በሚደረገው የልማት እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።

*የተገኙ ተሞክሮዎች*:- ድህነትን ከማጥፋት አኳያ የመንግስት

ፖሊሲዎች ድህነት ተኮር መሆናቸው፣ የመንግስት ያልተማከለ አስተዳደር አገልግሎቶችን ለህዝቦች በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ማስቻሉ፣ የመንግስት ከፍተኛ ቁርጠኝነት መኖር እና በግንዛቤና በሀገራዊ የጋራ ጉዳዮች መግባባት ላይ የተመሠረተ የተደራጀና የተቀናጀ ህዝባዊ የልማት ንቅናቄ ድህነትን በተፋጠነ ሂደት ለማጥፋት በኢትዮጵያ የልማት ሂደት የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች ናቸው። ትላልቅ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸውን የልማት ፕሮጀክቶች በማቀድና በመተግበር ሂደት ሀገራዊ ንቅናቄ፣ መግባበትና መነሳሳት ተጠናክሮ መቀጠሉ ሌላው መልካም ተሞክሮ ነው።

### 7.4.2. ግብ 2፡- ረሀብን ማጥፋት

የመንግስት ፖሊሲ አቅጣጫዎች፡- ኢትዮጵያ የምትከተላቸው አጠቃላይ ሀገራዊና የሴክተር ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች በየደረጃው ዜጎችን በልማት እኩል ተሳታፊና ፍትሀዊ ተጠቃሚ የሚያደርጉ ናቸው። እንዲሁም የዜጎችን ሁለንተናዊ አቅም በማሳደግ ላይ ያተኮሩ ናቸው። እነዚህን የመንግስት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች የኢኮኖሚ ዕድገትን በማፋጠን፣ መሠረተ ልማትንና ማህበራዊ ልማትን በማስፋፋት፣ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን እና ሀገራችን የጀመረችውን የህዳሴ ጉዞ በማፋጠን የምግብ ዋስትናን በሀገር ደረጃ፣ በአካባቢ ደረጃ እና በቤተሰብ ደረጃ በማረጋገጥ ዜጎችን ከምግብ ተመፅዋችነት ለማላቀቅ የሚያስችሉ ናቸው።



የሰው ጉልበትን በዕውቀትና በክህሎት በማሳደግና በማጎልበት በሰፊው መጠቀም፣ መሬትን በአግባቡና በውጤታማነት መጠቀም፣ ከአካባቢ ሥነ-ምህዳር ጋር የተጣጣመ የግብርና የገጠር የልማት ፓኬጅ ማዘጋጀትና መተግበር፣ በገበያ የሚመራ የግብርና ልማት እንዲኖር ማድረግ፣ የገጠር የፋይናንስ ስርዓት ማሻሻል፣ የግል ባለ ሀብቶች በግብርና ልማት ዘርፍ በሰፊው እንዲሳተፉ ማበረታታት፣ የገጠር ልማትን ማስፋፋትን እና ከግብርና ውጭ ያሉ የገጠር ልማት እንቅስቃሴዎችን ማጠናከር የመንግስት የግብርናና የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ መሠረታዊ አቅጣጫዎች ናቸው። እነዚህን መሠረታዊ አቅጣጫዎች መሰረት በማድረግ በአለፉት 15 ዓመታት በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በተከናወኑ የተደራጁና የተቀናጁ የልማት ሥራዎች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና ረሀብን ለማጥፋት የሚያስችሉ አመርቂ ውጤቶች ተመዝግበዋል።

የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት እና ምርት ለማሳደግ በርከት ላሉ ዓመታት በተከናወኑ የሥልጠና፣ የምርምርና የኤክስቴንሽን አገልግሎት አቅርቦት ሥራዎች የዋና ዋና የምግብ ሰብል ምርታማነት እየጨመረ መጥቷል። በ2007 የበጀት ዓመት የዋና ዋና የምግብ ሰብሎች ምርት 270.3 ሚሊዮን ኩንታል ደርሷል። ይህም በሀገር ደረጃ ኢትዮጵያ በምግብ ሰብል ረሷን እንድትችል ያስቻለ ነው። በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመጀመሪያ የትግበራ ዓመት (2008) በአየር ንብረት ለውጥ በተከሰተው አስከፊ ድርቅ ምክንያት የዋና ዋና ሰብሎች ዓመታዊ የምርት መጠን 266.83 ሚሊዮን ኩንታል የነበረ ሲሆን በ2009 የበጀት ዓመት የበልግ ምርትን ሳያካትት የ8.12 በመቶ ዕድገት በማሳየት 288.50 ሚሊዮን ኩንታል እንደሚደርስ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የትንበያ ውጤት ያሳያል። እንዲሁም በሁለተኛው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት (በ2012) የዋና ዋና የምግብ ሰብሎችን የምርት መጠን ወደ 406.32 ሚሊዮን ኩንታል ለማድረስ ታቅዷል። ዕቅዱንም ለማሳካት የተደራጁና የተቀናጁ የልማት ዕንቅስቃሴዎች በመካሄድ ላይ ናቸው። የዋና ዋና ሰብሎች ምርት በግብርና ዓመታዊ ተጨማሪ ዕሴት (ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት) በአማካይ 40 በመቶ ድርሻ አላቸው።

የዘላቂ ልማት ግቦችን በማስተሳሰር የተዘጋጀው ሁለተኛው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የግብርና ዘርፍ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ የግብርና ልማትን በመከተል፣ ምርታማነትን እና ምርትን በማሳደግ ላይ

ያተኮረ ነው። በዚህም የማስፋት ስትራቴጂውን አሟልቶ በመተግበር እና የአነስተኛ አርሶ-አደሩን እና አርብቶ-አደሩን የግብርና ምርታማነት በማሳደግ እንዲሁም መንግስት አስፈላጊ ድጋፎችን በማመቻቸት የግል ባለሀብቱ በግብርና ልማት የሚኖረውን ድርሻ በማጎልበት እና እ.ኤ.አ. በ2030 ረሀብን ለማጥፋት የተቀመጠውን ዓለም አቀፍ ግብ ለማሳካት በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ይገኛል።

**ዝርዝር አፈፃፀም፡-** መንግስት የምግብ ዋስትናን በተለያዩ ደረጃዎች ለማረጋገጥ እና ሀገራችንን ከምግብ ተመፅዋችነት ለማላቀቅ የግብርናን ምርታማነት በሚጠበቀው ደረጃ በማሳደግ ወደ አምራች ኢንዱስትሪ የሚደረገውን መዋቅራዊ ሽግግር ማፋጠን ወሳኝ ጉዳይ አድርጎ ወስዷል። በዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 የተቀመጠውን ረሀብን የማጥፋት ግብ ለማሳካት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለግብርና ምርታማነት፣ ለአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እንዲሁም ለከተማ የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ልዩ ትኩረት በመስጠት ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል።

በ2008 የበጀት ዓመት የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነትና ምርት ለማሻሻል፣ የምግብ ዋስትናን በአካባቢና በቤተሰብ ደረጃ ለማረጋገጥ የግብርና ምርምር ስራዎችን የማጠናከር፣ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎትን የማስፋፋት፣ የግብርና ግብዓት አቅርቦትን የማሳደግ አበረታች ስራዎች ተከናውነዋል።በዚህም የግብርና ግብዓት ለአርሶ አደሩ በወቅቱና በበቂ መጠን ከማቀረብ አንፃር በበጀት ዓመቱ 752,282 ሜትሪክ ቶን ማዳበሪያ 2,203,541 ኩንታል ምርጥ ዘር ማቅረብ ተችሏል።። በተጨማሪም በ2008 የበጀት ዓመት የኤክስቴሽን አገልግሎትን ለአርሶ-አደሩ እና ለአርብቶ-አደሩ ለማዳረስ በተሠሩ የልማት ሥራዎች 15,735,000 አባወራ እና አማወራዎች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ሆነዋል። በ2008 የበጀት ዓመት የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎትን ለአርሶ-አደሮች እና ለአርብቶ-አደሮች ተደራሽ ከማድግ አንፃር አመርቂ ውጤቶች የተመዘገቡ ሲሆን በዚህም የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት ለማሳደግ እየተከናወኑ ያሉ የልማት ሥራዎች በትክክለኛ አቅጣጫ እየተጓዙ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ በሀገሪቱ ተከስቶ የነበረው አስከፊ ድርቅ በግብርናው ዘርፍ ምርታማነት እና ምርት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደነበረው መረጃዎች ያመለክታሉ።

በ2008 የበጀት ዓመት በሀገሪቱ ተከስቶ የነበረው አስከፊ ድርቅ በተለይ በግብርናው ዘርፍ የልማት እንቅስቃሴ ላይ ባሳደረው ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ ምክንያት ዋና ዋና የምግብ ሰብሎች ምርት በ2007 ከነበረበት 270.3 ሚሊዮን ኩንታል በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 266.8 ሚሊዮን ኩንታል ቀንሷል። በተመሳሳይ የሥጋ ምርት በ2007 ከነበረበት 1321 ሺህ ቶን በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 669 ሺህ ቶን ወርዷል። እንዲሁም የወተት ምርት በ2007 ከነበረበት 5304 ሚሊዮን ሊትር በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 4466.7 ሚሊዮን ሊትር ቀንሷል። በሌላ በኩል በ2008 የበጀት ዓመት የምግብ ዋስትናን ማረጋጋጥ የሚያስችሉ የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ሥራዎች በተደራጁና በተቀናጁ የህዝብ ንቅናቄዎች ተከናውነዋል። በዚህም መሠረት 1,028 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የተለያዩ የስነ-አካላዊና ስነ-ህይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች ተከናውነዋል።

ከዚህ በተጨማሪም የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ረሃብን ለማጥፋት ሥር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ያለባቸውን ቤተሰቦች በሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚ በማድረግ የቤተሰብ ጥሪት እንዲገነቡ ማስቻል እና ከልማታዊ ሴፍቲኔት ተመርቀው ራሳቸውን እንዲችሉ በመንግስት በተዘረጋ ሥርዓት መሠረት የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያን ከመተግበር አኳያ 108,228 ተጠቃሚ ቤተሰብ ኃላፊዎች በቤተሰብ ደረጃ ለጥሪት ግንባታ አገልግሎት የሚውል ብድር ብር 304,112,476 እንዲያገኙ ተደርጓል። በተጨማሪም ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት አንፃር በ2008 የበጀት ዓመት ከክምችት የምግብ እህል ለሚፈልጉ የተለያዩ የገጠር ሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞች የ105,300 ሜትሪክ ቶን የምግብ እህል ማቅረብ ተችሏል። እነዚህ የተደራጁ እና የተቀናጁ የልማት እንቅስቃሴዎች የኢትዮጵያ መንግስት የዜጎችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን ያመለክታሉ።

የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና ረሀብን ለማጥፋት የማስፈፀሚያ መንገዶች፡- የመንግስት የግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲንና ስትራቴጂን እንዲሁም

የምግብ ዋስትና ስትራቴጂን አሟልቶ ተፈፃሚ በማድረግ የግብርናን ምርታማነት እና ምርት በመጠንና በጥራት በማሳደግ ወደ አምራች ኢንዱስትሪ የሚደረገውን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ማፋጠን ወሳኝ ጉዳይ ነው። ከዚህ አንፃር የገጠርና የከተማ የሥራ ዕድል ፈጠራን ማስፋፋት፣ የመጠባበቂያ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ክምችቶች አቅምን ማጠናከር የምግብ ዋስትናን በተለያዩ ደረጃዎች ለማረጋገጥ በከፍተኛ ትኩረት ተይዞ እየተሠራ ይገኛል። በተለይ በግብርና ዘርፍ እየተከናወኑ ላሉ የልማት ሥራዎች ዋናው የማስፈፀሚያ መንገድ በኤክስቴንሽን አገልግሎት የተደገፈ፣ በግንዛቤ ላይ የተመሠረተና የተሟሉ የግብርና ግብዓት ፓኬጆችን በአግባቡ የሚጠቀም ሰፊ ጉልበት ነው።

ከዚህ አንፃር በግብርናው ዘርፍ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት የአርሶ አደሮች እና የአርብቶ አደሮች አቅም ግንባታ ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ተደርጓል። እንዲሁም የግብርና ምርምር፣ የሰብልና የእንስሳት ጤና ጥበቃ፣ የግብርና ግብዓት አቅርቦት፣ የብድር አቅርቦት፣ የግብርና ምርቶች ግብይት፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የንፁህ ውሃ አቅርቦት፣ የመንገድ መሠረተ ልማት ግንባታ፣ የኤሌክትሪክ እና የስልክ አገልግሎት ተደራሽነትና ሽፋን በጥራት የማስፋፋት ሥራ ይገኛል። እንዲሁም ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ የግብርና የልማት አቅጣጫ መሰረት በተቀናጀ የግብዓት አቅርቦት ሥርዓት ዝቅተኛ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ያላቸው የግብርና ግብዓቶችን በመጠቀም፣ አነስተኛ መስኖዎችን የማስፋፋት ሥራ እየተሠራ ይገኛል።

የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎትን ለአርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ተደራሽ በማድረግ፣ ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ሥርዓትን በመከተል፣ የግል ባለሀብቶች በግብርናው ዘርፍ ለአካባቢ ተስማሚ የሆኑ የኢንቨስትመንት ሥራዎችን እንዲያካሂዱ በማበረታታት እንዲሁም በጥናትና ምርምር የተደገፈ የግብርና ግብዓት በማቅረብ የግብርናን ምርታማነትና ምርት የማሳደግ እና በሀገር ደረጃ የምግብ ክምችት አቅምን የማጠናከር ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የተደረገ ሲሆን በ2008 የበጀት ዓመት 15 ሚሊዮን የሚሆኑ አርሶ-አደሮች እና አርብቶ-አደሮች በአገልግሎቱ ተጠቃሚ ሆነዋል።

ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች፡- በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በ2008 እና በ2009 በሀገሪቱ የተከሰተው ድርቅ በተለይ በግብርናው ዘርፍ ልማት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አስከትሏል። በ2008 የበጀት ዓመት 10.2 ሚሊዮን ህዘብ እንዲሁም በ2009 የበጀት ዓመት 5.2 ሚሊዮን ህዘብ በድርቁ ተጠቂ ሆኗል። የግብርና ዘርፍ በ2008 የበጀት ዓመት ከተቀመጠለት አጠቃላይ ሀገራዊ የምርት ዕድገት ግብ የ5.9 መቶኛ ነጥብ ቅናሽ አሳይቷል። ይህንኑ ተከትሎ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በበጀት ዓመቱ ከተቀመጠለት የ11.2 በመቶ የዕድገት ግብ የ3.2 መቶ ነጥብ ቅናሽ በማሳየት 8 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል። ድርቁ በእንስሳት ሀብት ላይ ጉዳት ከማስከተሉም በላይ በልማት ሥራ ላይ ሊውል ይችል የነበረ ውስን የሀገር ሀብትን ተሻምቷል። ከዚህ አንፃር በቀጣይ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ አቅም የበለጠ ለማጠናከርና የምግብ ዋስትናን በተለያዩ ደረጃዎች ለማረጋገጥ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ይገኛል።

የተገኘ ተሞክሮ፡- የኢትዮጵያ መንግስት የግብርና መር ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ እና የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ቀርፆ በሀገር ውስጥ ያለውን ሰፊ ሀብት (የሰው ጉልበት እና መሬት) በአግባቡ እና በስፋት በመጠቀም ገጠርንና ግብርናን ማዕከል ያደረጉ የልማት ሥራዎች በማከናወኑ እና ብሔራዊ የአደጋ ክስተት ስጋት ሥራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ዘርግቶ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ተፈፃሚ ማድረጉ በሀገራችን በ2008 እና በ2009 የተፈጠረውን አስከፊ የድርቅ አደጋ በአንድም ሰው ህይወት ላይ አደጋ ሳያደርስ በውስጥ አቅም መቀልበስ መቻሉ በመልካም ተሞክሮ የሚወሰድ ነው። ይህንን መልካም ተሞክሮ እንደ አንድ ትልቅ አቅም በመያዝ በቀጣይ የግብርናን ምርታማነት ማሳደግ፣ ሰፊ ጉልበት የሚጠቀሙ የማኑፋክቸሪንግ ኢንቨስትመንት ሥራዎችን ማስፋፋት፣ የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ሽግግር ማፋጠን እና የምግብ ዋስትናን በሀገር፣ በአካባቢ እና በቤተሰብ ደረጃ በማረጋገጥ ረሀብን እና ድህነትን በ2030 ለማጥፋት የተደራጁና የተቀናጁ የልማት ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው።

### 7.4.3. ግብ 3፡- ጤናማ ህይወትና ደህንነት

የመንግስት ፖሊሲ አቅጣጫዎች፡- በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 90 ንዑስ አንቀፅ 1 እንደተደነገገው መንግሥት የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንጹህ ውሃ፣ የመኖሪያ፣ የምግብና የማህበራዊ ዋስትና እንዲኖር ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ እንዳለበት አስቀምጧል። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 41 ንዑስ አንቀፅ 4 የተደነገገ ሲሆን በዚህም መንግሥት የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች የማህበራዊ አገልግሎቶችን ለሕዝብ ለማቅረብ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሀብት ለመመደብ ቁርጠኛ መሆን እንዳለበት በግልፅ ተቀምጧል።



የህገ-መንግስቱን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መንግስት የተለያዩ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ፕሮግራሞችን ዘርግቷል። በዚህም መሠረት መንግስት የሀገሪቱን የጤና ችግሮች እና የችግሮች መነሻዎችን በመለየት እንዲሁም ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ አዳዲስ የጤና ችግሮችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በመከላከል ላይ ያተኮረ የጤና አገልግሎት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና ፕሮግራም ተቀርጾ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል።

የሀገሪቱ የጤና ፖሊሲ ዋና ዓላማ ዜጎች የጤና አገልግሎት በቀላሉ የሚያገኙበት ሁኔታ በመፍጠር ሁሉም ዜጎች መሰረታዊ የጤና አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ማስቻል ነው። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ መንግስት የጤና መሠረተ ልማትን ማስፋፋት እና የጤናውን ዘርፍ የሰው ኃይል ልማት ማሻሻል ዋና መርህ በማድረግ እየሠራ ይገኛል። የጤና ፖሊሲውን በተደራጀ እና በተቀናጀ አግባብ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችል እና በሀገራችን የገጠር እና የከተማ አካባቢዎች ተፈፃሚ የሚደረግ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም በማዘጋጀት እና ፕሮግራሙን ተፈፃሚ ለማድረግ 38 ሺህ የሚሆኑ የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሠራተኞች ሠልጥነው ወደ ሥራ እንዲሠማሩ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪ የመሠረታዊ ጤና ክብካቤን በማጠናከር እና ከዘላቂ የልማት ግቦች ጋር በማስተሳሰር እ.ኤ.አ. በ2030 ጤናማ ህይወትና ደህንነትን ለማረጋገጥ በሁሉን አቀፍ የጤና ተደራሽነት ላይ ያተኮሩ የጤና ዘርፍ የልማት ሥራዎች በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ተፈፃሚ ለማድረግ አቅጣጫ ተቀምጦ ወደ ሥራ ተገብቷል።

**ዝርዝር አፈፃፀም፡-** ባለፉት ዓመታት መንግስት የልማት ኃይሎችን በየደረጃው አስተባብሮ በመምራት የጤናውን ዘርፍ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ፕሮግራም ከሌሎች አግባብነት ካላቸው የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር በማመጋገብ በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ ተፈፃሚ ሲያደርግ ቆይቷል። በዚህም የጤና ተቋማትን በማስፋፋት፣ አስፈላጊውን የሰው ኃይል በማሠልጠንና ወደ ሥራ በማሰማራት፣ የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን ማስፋፋት እና የአገልግሎት ሽፋኑን በ2008 የበጀት ዓመት መጨረሻ 98 በመቶ ማድረስ ተችሏል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይ የእናቶች እና የህፃናት ጤና ከፍተኛ መሻሻል አሳይቷል። እንዲሁም የተላላፊ በሽታዎች ክስተት እና ስርጭት በከፍተኛ ደረጃ ተገትቷል። ይህም ኢኮኖሚው የሚፈልገውን ጤናማ የሥራ ኃይል ምርታማነት በማሻሻል የኢኮኖሚውን ፈጣን ዕድገት ለማስቀጠል እና እ.ኤ.አ. በ2030 ድህነትን ከነሁሉም መገለጫዎቹ ለማጥፋት የጎላ አስተዋፅኦ አለው።

በምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች የትግበራ ሂደት የእናቶችን ሞት ለመቀነስ የተደራጁና የተቀናጁ ከፍተኛ የልማት ሥራዎች ተከናውነዋል። በዚህም በ2007 የበጀት ዓመት መጨረሻ የእናቶችን ሞት መጣኔ 420/100000 ማድረስ ተችሏል። ይህንን መልካም ውጤት እንደ መነሻ በመውሰድ እና መንግስት የዘረጋውን የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት

ፕሮግራም አሟልቶ በመተግበር የእናቶችን ጤና ይበልጥ ለማሻሻል በጤና የልማት ሠራዊት በመደገፍ በእናቶች የቅድመ ወሊድ፣ የወሊድ እና የድህረ ወሊድ ክትትል ዙሪያ በተከናወኑ የተጠናከሩ የልማት ሥራዎች የእናቶች ሞት በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 412/100000 መቀነስ ተችሏል። በሰለጠነ የጤና ባለሙያ የወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ሽፋንም በ2007 ከነበረበት 60 በመቶ በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 72.7 በመቶ ጨምሯል። ይህ አፈፃፀም ከወሊድ ጋር የተያያዘ የእናቶች ሞትን ከመቀነስ አንፃር ያለው አስተዋፅኦ የጎላ ነው።

የእናቶችን ሞት ለመቀነስ አስተዋፅኦ ካደረጉት መካከል የህብረተሰቡ ግንዛቤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣት፣ መንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት አጋሮች የሠሯቸው የተቀናጁ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እና የአምቡላንስ አገልግሎትን ጨምሮ የጤና አገልግሎት በሁሉም አካባቢዎች ተደራሽ መሆኑ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በአጠቃላይ መንግስት በተለያዩ ጥናቶች በመታገዝ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮችን በጤና እና ሌሎች ተመጋጋቢነት ባላቸው ፕሮግራሞችና በተቋም ደረጃ በማካተት የተሻሻለ የጤና ዘርፍ የሥርዓተ-ፆታ ማንዋል በማዘጋጀት በሥራ ላይ አውሏል። በዚህም በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በዘላቂ ልማት ግቦች የተቀመጡ የእናቶች ሞት ቅነሳ ኢላማዎችን እ.ኤ.አ. በ2030 ማሳካት እንደሚቻል አመላካች ነው።

የህፃናት ጤና አገልግሎትን በተመለከተ ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት ሞት መጣኔ እና የጨቅላ ህፃናት ሞት መጣኔ በቅደም ተከተል በ2007 የበጀት ዓመት 64/1000 እና 28/1000 የነበረ ሲሆን በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 67/1000 እና 29/1000 ከፍ እንዳለ የኢትዮጵያ የጤና ዲሞግራፊክ ሰርቬይ ሪፖርት ያመለክታል። ይህ አፈፃፀም በ2007 ከተመዘገቡ ውጤቶች ጋር ሲነፃፀር ወደኋላ የመመለስ አዝማሚያ የሚያመለክት በመሆኑ ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሠራ ይገባል። በሌላ በኩል ከሥርዓተ ምግብ ጋር በተያያዘ ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት መቀንጨር በ2007 ከነበረበት 40 በመቶ በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 38.4 በመቶ የቀነሰ ሲሆን ከ5 ዓመት በታች የሆኑ የህፃናት መቀጨጭ በ2007 የበጀት ዓመት 9 በመቶ ደርሶ የነበረ ቢሆንም በ2008 የበጀት ዓመት መጠነኛ (የ0.9 መቶኛ ነጥብ) ጭማሪ በማሳየት 9.9 በመቶ ደርሷል። በህፃናት ዙሪያ የሚታየውን ሞት ከሚያባብሱት የጤና ተቋማት ያልተቀናጁ የህፃናትና ጨቅላ ህክምና አገልግሎቶች መካከል የምግብ ዕጥረት አንዱ በመሆኑ ችግሩን ለማስወገድ እ.ኤ.አ. በጁላይ 2015 የሰቆጣ ስምምነት ተፈርሞ ከ2 ዓመት በታች ዕድሜ ያላቸው ጨቅላ ህፃናት መቀንጨርን እ.ኤ.አ. በ2030 ዜሮ ለማድረስ እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 2016 ጀምሮ የመጀመሪያ 1000 ቀናት የህፃናት ሥርዓተ ምግብ አገልግሎት ፕሮግራም በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል።

በጤና ልማት ዘርፍ በትኩረት ተይዘው እየተሠሩ ካሉ የጤና አገልግሎት ሥራዎች መካከል ሌላው ተላላፊ በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር ነው። ከዚህ አንፃር የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ በሰፊው ከሚሠራባቸው ተላላፊ በሽታዎች መካከል የኤች. አይ. ቪ. ኤድስ. የወባ በሽታ እና የቲቢ መከላከልና መቆጣጠር ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በመሆኑም እነዚህን ተላላፊ በሽታዎች ለመከላከልና ለመቆጣጠር ባለፉት ዓመታት መንግስት ሁሉንም የልማት ኃሎች አስተባብሮ በመምራት በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በርካታ የዘርፍ አቅም ግንባታ፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ፣ የማስፈፀሚያ ሀብት የማሰባሰብ፣ ተቋማዊ አሠራር፣ አደረጃጀትና ሌሎች የማስተባበሪያ መንገዶችን የማመቻቸት፣ የኤች. አይ. ቪ./ኤድስ ጉዳይን በተለያዩ የዘርፍ የልማት ፕሮግራሞችና ዕቅዶች የማካተት እና እንዲሁም የክትትልና ግምገማ ሥራዎች ተከናውነዋል፣ በዚህም ስኬታማ ውጤቶች ተመዝግበዋል።

በዚህም መሠረት በኢትዮጵያ በኤች. አይ. ቪ. ቫይረስ አዲስ የሚያዙ ሰዎች መጠን በከፍተኛ ደረጃ የቀነሰ ሲሆን በ2008 የበጀት ዓመት መጨረሻ መጣኔው 0.03 በመቶ ሆኗል። ይህንኑ መልካም ውጤት አጠናክሮ ለማስቀጠል እና ክስተቱን ዜሮ ለማድረስ መንግስት በየዓመቱ እስከ 10 ሚሊዮን የሚሆን ህዝብ የኤች.አይ.ቪ ቫይረስ የደም ምርመራ እያደረገ ቫይረሱ የተገኘባቸው ተመርማሪዎች መድኃኒት እንዲጀምሩ እና ነፃ የሆኑት ደግሞ በይበልጥ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ በማድረግ በሽታውን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር እየተንቀሳቀስ ይገኛል።

የቲቢ በሽታ ከመከላከልና ከመቆጣጠር አኳያ የሁሉም

አይነት የቲቢ በሽታ ልየታ መጠን እ.ኤ.አ. በ2014 በወጣው አለም አቀፍ የቲቢ ሪፖርት መሠረት ኢትዮጵያ በቲቢ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር መለኪያ በሆኑት፣ በሞትና በቲቢ በሽታ ስርጭት ምጣኔ (Mortality and Prevalence) የተቀመጡትን ግቦች ማሳካት ችላለች፡፡፡ በ2008 የበጀት ዓመት ዓመታዊ የጤና ዘርፍ አፈፃፀም ሪፖርት መሠረት የቲቢ ልየታ መጠን 61.3 በመቶ ደርሷል። በ2009 የበጀት ዓመት ሥራው ተጠናክሮ ቀጥሏል። በተመሳሳይ የቲቢ በሽታ ሕክምና የጨረሱ የህሙማን መጠንም በ2008 የበጀት ዓመት 92 በመቶ ደርሷል። ለዚህም የማሕበረሰብ አቀፍ የቲቢ ልየታ ፕሮግራም ተግባራዊ በመደረጉ እና እ.ኤ.አ. ከ2005 ጀምሮ የተጀመረው ቅንጅታዊ የቲቢ-የኤች.አይ.ቪ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር ተግባር ከነፃ የፀረ ኤች.አይ.ቪ መድሃኒት አገልግሎት መስፋፋት ጋር ተዳምሮ ለውጤቱ መገኘት ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ይታመናል።

እንዲሁም የወባ በሽታ ለአብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ የጤና ስጋት ሲሆን መንግስት በሠራቸው የተቀናጁና የተደራጁ የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራዎች ክስተቱን መቀነስ የሚያስችሉ አመርቂ ውጤቶች ተመዝግበዋል። ሆኖም በ2008 የተመዘገበው የ22/1000 የወባ በሽታ ክስተት ከ2007 አፈፃፀም (21/1000) ጋር ሲነፃፀር የ1/1000 ጭማሪ አሳይቷል። በበጀት ዓመቱ የታየው የወባ በሽታ ክስተት መጨመር ድርቁን ተከትሎ በሀገሪቱ ዝቅተኛ አካባቢዎች የተከሰተው የጎርፍ መጥለቅለቅ ለወባ ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎችን በስፋት በመሸፈኑ እና ከሌላ ጊዜ በተለየ ሁኔታ ለወባ ትንኝ መራባት ምቹ ሁኔታ በመፍጠሩ ምክንያት የወባ በሽታ ክስተት በመጨመሩ ነው። ከዚህ አንፃር የበሽታውን ክስተት ለመከላከል እና ስርጭቱን ለመቆጣጠር በኬሚካል የተነከረ የመኝታ አጎበር ለተጠቃሚው ማህበረሰብ የማዳረስ፣ ውሀ ያቆሩ የትንኝ መራቢያ ቦታዎችን የማጠንፈፍ እና የቤት ውስጥ የፀረ ወባ ትንኝ ኬሚካል ርጭት ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ተደርጓል።

በሌላ በኩል የተቀናጀ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች (የልብ ህመም፣ ካንሰር፣ ስኳር...ወዘተ) መከላከል እና መቆጣጠር ምላሽ ለመስጠት በተለያዩ የልማት ዘርፎች የማካተት እና አቀናጅቶ ተፈፃሚ የማድረግ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል። ክስተቱን በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስም በሀገራችን የልብ ህክምና ማዕከል እና የካንሰር ህክምና ማዕከል በማቋቋም አገልግሎቱ በመስፋፋት ላይ ይገኛል።

የአፍላ ወጣቶች የመውለድ መጠን በተመለከተ ባለፉት ዓመታት በተደረገው መጠነ ሰፊ የተቀናጀ የስነ ተዋልዶ ትምህርት አፍላ ወጣቶችን በከፍተኛ ደረጃ በማሳተፍ የባህሪይ ለውጥ እንዲመጣ በመደረጉ የአፍላ ወጣቶች የመውለድ መጠን በ2008 መጨረሻ 12/1000 መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። በቀጣይም የሥነ ተዋልዶ ትምህርትና አገልግሎት የበለጠ በማጠናከር የዘላቂ ልማት ግቡን ኢላማ ለማሳካት እየተሰራ ይገኛል። መንግስት በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች የዘረጋውን በመከላከል ላይ ያተኮረ የጤና ፖሊሲ በተሟላ ሁኔታ ተፈፃሚ በማድረግ ሂደት በተለይ ለጥናትና ለመሠረታዊ የጤና አገልግሎት (ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር) በልማት አጋሮች የተደረገው ድጋፍ አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው።

ጤናማ ህይወትና ደህንነትን ለማረጋገጥ የተዘረጉ ማስፈጸሚያ መንገዶች፡- ጤናማ ህይወትና ደህንነትን ለማረጋገጥ መንግስት ያወጣቸውን ህጎች፣ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ማድረግ መተኪያ የሌለው ሥራ ነው። ይህም ከተለያዩ የልማት አጋሮች ጋር በመቀናጀት ህብረተሰቡን አሳታፊና ባለቤት ያደረገ የጤና ዘርፍ ሥርዓት ግንባታን ማጠናከር፣ በየደረጃው የአቅም ግንባታ ስራዎች በማከናወን፣ የጥናት እና ምርምር ውጤቶች ሥርፀት በማጠናከር፣ አገር በቀል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን ከቴክኖሎጂ ጋር የማዋሀድ ሥልት በማከናወን የሚፈፀም ነው። እንዲሁም የመሠረታዊ ጤና እንክብካቤ እና የሆስፒታል አገልግሎቶች የሚኖራቸውን ትስስር ማጠናከር፣ የሁለተኛው ምዕራፍ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ማድረግ፣ የግሉን ዘርፍ በጤናው ዘርፍ ልማት በተጠናከረ መልኩ ማሳተፍ፣ ብዙ ያልተሰራበት የባህላዊ ህክምና ዘርፍም የበለጠ ድጋፍ ተደርጎለት እንዲሠራ ማበረታታት ሌላው በትኩረት የሚሠራ ሥራ ነው። በአጠቃላይ መንግሥት የሀገር ውስጥ ሀብት የማሰባሰብ አቅሙን በማሳደግ የተሟላ የጤና አገልግሎት ለሕዝብ ለማቅረብ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሀብት በመመደብ እና ከልማት አጋሮች የሚገኘውን ድጋፍ ግልፅ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ አግባብ ሥራ ላይ በማዋል የዘላቂ

ልማት ግቦችንና ኢላማዎችን በማስተሳሰር በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጡ የጤና ዘርፍ ግቦችን እና ኢላማዎችን ለማሳካት የተደራጁ እና የተቀናጁ የልማት ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ እየተደረገ ነው።

ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች፡- የአየር ንብረት ለውጥ በሀገራችን ያስከተለው ድርቅ እና ጎርፍ በጤናው ዘርፍ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ (የወረርሽኝ በሽታ መከሰት) አሳድሯል። እንዲሁም ድንበር ዘለል የጤና ችግሮችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተቀናጀ ጠንካራ ሥርዓት አለመኖር እና ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ስደተኞች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ መምጣት በጤና ተቋማት ተጨማሪ ጫና መፍጠሩ...ወዘተ የጤናው ዘርፍ ፈተናዎች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ የጤና አገልግሎት ጥራት ከአገልግሎት ተደራሽነት ጋር ተመጣጥኖ አለመጠናከሩ ሌላው ትልቅ ፈተና ነው።

የተገኙ ተሞክሮዎች፡- እ.ኤ.አ. ከ2003 ጀምሮ በሀገራችን ተግባራዊ የተደረገ እና ከፍተኛ ስኬቶች እየተመዘገቡበት ያለው የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ፕሮግራም ህብረተሰቡን በየደረጃው በማሳተፍ የተለያዩ የጤና ችግሮችን በመከላከልና በመቆጣጠር አመርቂ ውጤቶች እየተመዘገቡበት ይገኛል። የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ፕሮግራሙ የሚሸፍናቸው ዋና ዋና ዘርፎች የቤተሰብ ጤና፣ በሽታ መከላከል፣ የሃይጅን፣ ሳኒቴሽንና አካባቢ ጤና እንዲሁም የጤና ትምህርት ሲሆኑ በእነዚህ ማዕቀፍ ውስጥ ያሉትን ቁልፍ ተግባራት ወደ ህብረተሰቡ ለማድረስ ከ38,000 በላይ የሚሆኑ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ሠልጥነው ተሰማርተዋል። እንዲሁም በህብረተሰቡ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የሴቶችን የጤና ልማት ሰራዊት በማደራጀት የተቀናጁ ሥራዎች እየተከናወኑ ሲሆን እስከ 2009 የመጀመሪያ ግማሽ የበጀት ዓመት ድረስ በሀገሪቱ 439,497 የተደራጀ የሴቶች ጤና ልማት ቡድን እና 2,125,190 የአንድ ለአምስት አደረጃጀት ተፈጥሯል። በዚህም ቁልፍ የሆኑ መሰረታዊ የእናቶችና የህፃናት ጤና አገልግሎቶች በከፍተኛ ደረጃ ተሻሽለዋል።

ጤናማ ህይወትና ደህንነትን ለማረጋገጥ ታሳቢ ከተደረጉ ቀጣይ እርምጃዎች አንፃር የጤና ባለሙያዎችን ሥልጠና አጠናክሮ በመቀጠል የትራንስፎርሜሽን አጀንዳዎችን በየደረጃው ለመተግበር ቀልጣፋና አስተማማኝ የጤና ዘርፍ ልማት የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት በመቅረፅና ሥራ ላይ እንዲውል በማደረግ፣ የጤና ዘርፍ የልማት ሰራዊት እንቅስቃሴን በየደረጃው አጠናክሮ በማስቀጠል የህብረተሰቡን የጤና ባለቤትነት ማረጋገጥና ድንበር ዘለል የሆኑ የጤና ጉዳዮችን ከጎረቤት ሀገራት ጋር በመተባበር በጋራ ለመከላከል ዓለም አቀፍ የጤና ዲፕሎማሲ ስራዎች በትኩረት ተይዘው እንዲከናወኑ እየተደረገ ነው።

### 7.4.4. ግብ 5፡- የሥርዓተ-ፆታ ዕኩልነት

የመንግስት ፖሊሲ አቅጣጫዎች፡- የሀገሪቱ የበላይ ህግ የሆነው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ 25 ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል እንደሆኑ ይደነግጋል። እንዲሁም በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 35 ሴቶች በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና በፖለቲካው ዘርፍ በሚደረጉ ማናቸውም እንቅስቃሴዎች ከወንድ እኩል መብት እንዳላቸው በግልፅ ያስቀምጣል። እነዚህን የህገ-መንግስት ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ የሴቶች ፖሊሲ እና የሴቶች የልማትና የለውጥ ስትራቴጂ ተዘጋጅተው በሥራ ላይ ውለዋል። የሴቶችን ፖሊሲ ለማስፈፀምም ተቋማዊ አሠራሮችና አደረጃጀቶች በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ተዘርግተዋል።



የሴቶች ፖሊሲ ዋነኛ ዓላማ ሴቶች በኅብረተሰቡ ውስጥ በማንኛውም መስክ ሰብአዊ መብታቸው እንዲከበርና እኩልነታቸው እንዲረጋገጥ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊና በፖለቲካ እንቅስቃሴዎች በየደረጃው እኩል ተሳታፊ፣

ተጠቃሚና ውሳኔ ሰጭ የሚሆኑበትን የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር፣ በተለይም የገጠሯ ሴት መሠረታዊ የሆኑ ልዩ ልዩ ማኅበራዊ አገልግሎቶች፣ የሥራ ማቃለያ ዘዴዎችን የምታገኝበትንና ተጠቃሚ የምትሆንበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ ለዘመናት ሥር ሰዶ የቆየውን በፆታ ላይ የተመሠረተ ባህላዊና ልማዳዊና አድሎአዊ አስተሳሰብ ደረጃ በደረጃ ማጥፋትና ሴቶች በውሳኔ ሰጭነት ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ መንግስታዊ ስልጣንና የአስተዳደር ዕርከን በብዛት ተካፋይ እንዲሆኑ ማድረግ ነው።

የኢትዮጵያ መንግስት አጠቃላይ ሀገራዊ እና የሴክተር ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች የሴቶች መብትና ጥቅም የማስጠበቅ ጉዳዮችና አላማዎች የተካተቱባቸው ናቸው። የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት የተዘጋጀው የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አንዱና ዋነኛው የትኩረት አቅጣጫ የሴቶችንና የወጣቶችን ብቃት፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ ነው። በዚህም የሴቶችንና የወጣቶችን አደረጃጀቶች ማጠናከር፣ በእነዚህ አደረጃጀቶች አማካኝነት ሴቶችና ወጣቶች በሀገሪቱ የልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በመሳተፍ ተጠቃሚነታቸውን እንዲያረጋግጡ ማድረግ፣ እንዲሁም አደረጃጀቶቹ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅተው እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ ትኩረት የሚሰጣቸው ተግባራት ናቸው።

የሴቶችና የወጣቶች አጀንዳዎች በሁሉም የሀገሪቱ የልማት ዕቅዶች ተካትተው እየተፈፀሙ መሆናቸውን ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ ክትትል ለማድረግ አቅጣጫ ተቀምጧል። በተመሳሳይ የእናቶችንና የህጻናት ሞት መጣኔ ለመቀነስ፣ የቤተሰብ ምጣኔ፣ የቅድመ ወሊድና የድህረ ወሊድ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ፣ እናቶች በህክምና መስጫ ተቋማት እንዲወልዱ፣ በአመጋገብና ጤና አጠባበቅ ዙሪያ እንዲሁም በአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ዙሪያ ግንዛቤ እንዲያገኙ እና የጡትና የማህጸን ካንሰር ምርመራ እንዲያደርጉ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል። እንዲሁም የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን ለማሻሻል የህጻናት መረጃ ቋት (ዳታ ቤዝ) በመመስረት ከክልሎችና ከፌዴራል ተቋማት ጋር የማገናኘት ሥራ ይሰራል፣ የህጻናት ማህበራዊ ተጠቃሚነትም እንዲያድግ ይደረጋል።

**ዝርዝር አፈጻጸም፡-** መንግስት የሴቶችንና የወጣት ሴት ልጆችን ፍትሐዊ ተጠቃሚነትና እኩልነት ለማረጋገጥ የሴቶች ፖሊሲን፣ የሴቶች የልማትና የለውጥ ስትራቴጂ፣ የወጣቶችፖሊሲና የወጣቶች የልማት ፓኬጅን ቀርፆ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። የወጣቶች ፖሊሲ ለሴቶች የተለየ ትኩረት በመስጠት ወጣቶች በዲሞክራሲና በመልካም አስተዳደር ጉዳዮች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣ እንዲደራጁና መብታቸውን እንዲያስከብሩ ማስቻልና በትምህርትና በተለያዩ ሙያዊ ስልጠናዎች አቅማቸውን መገንባት ዋነኛ ዓላማ ሲሆን ፖሊሲውን ተፈፃሚ ለማድረግ ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ይገኛል። የሴቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ከማሳደግ አንጻር ባለፉት ዓመታት በርካታ የልማት ሥራዎች ተከናውነዋል። ከነዚህም መካከል በገጠር የሚገኙ ሴቶችን በተለያዩ የሥራ ዘርፎች እንዲሰማሩ መደገፍና የመሬት ባለቤት እንዲሆኑ ማድረግ ዋነኛው ነው። እንዲሁም ሴቶችን በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ በማንቀሳቀስ በየደረጃው በሚካሄዱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና የአካባቢ ልማቶች እንዲሁም የፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ውጤታማ ተሳትፎ እንዲያደርጉ እና ከሚካሄደው ልማት በበቂ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል የኢትዮጵያ ሴቶች የልማት እና የለውጥ ስትራቴጂ በ2009 በጀት ዓመት በመንግስት ፀድቆ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

ሴቶች በተለያዩ የግብርና ዘርፎች እንዲሰማሩ የግንዛቤ ሥራዎችንና ሥልጠና እንዲያገኙ ለማድረግ በታቀደው መሠረት በ2008 የበጀት ዓመት 4,324,000 ሴቶች በግብርና (የጓሮ አትክልት፣ በዶሮ ርባታ፣ በንብ ማነብ፣ ከብት ማድለብ ወዘተ)፣ እንዲሁም 895,188 ሴቶች በመስኖ ልማት ተሰማርተው ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። በተመሳሳይ ወቅት 9,520,763 ሴቶች በተፋሰስ ልማት የተሰማሩ ሲሆን 89.8 ሺህ ወጣቶች ባገገሙና እንደገና በለሙ መሬቶች ላይ ወደ ሥራ ገብተዋል። በበጀት ዓመቱ 1,371,062 አርሶ-አደር እማወራና ባለትዳር ሴቶች እና 218,000 አርብቶ-አደር እማወራ ሴቶች የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ የተደረጉ ሲሆን 2,568,920 ሴቶችንም የንፁህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል። በ2009 የበጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራትም 2,487,951 ሴቶች በገጠር በግብርና እና 923,226 ሴቶች ከግብርና ሥራ

ውጭ በመሰማራት ተጠቃሚ ሆነዋል። በገጠር መሬት ዋነኛ የኢኮኖሚ መሰረት እንደመሆኑ በ2008 በጀት አመት 276.1 ሺህ ሴቶች በጋራ ከባለቤቶቻቸው ጋር እና 61.7 ሺህ ሴቶች በግል እንዲሁም በ2009 ስድስት ወራት ደግሞ ለ432,011 ሴቶች በጋራ እና 71,169 ሴቶች በግል የሁለተኛ ደረጃ የመሬት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ደብተር እንዲያገኙ ተደርጓል።

በ2008 በጀት አመት የሴቶች በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና በመስጠትና በመደገፍ 99,833 ሴቶችን ከጥቃቅንና አነስተኛ ወደ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ማሸጋገር ተችሏል። በበጀት ዓመቱ 755,942 ሴቶች ወደ ጥቃቅንና አነስተኛ ሥራ እንዲገቡ የተደረገ ሲሆን በ2009 የበጀት ዓመት ስድስት ወራት ለ57,431 ሴቶች የመሥሪያና የመሸጫ ቦታ ተሰጥቷቸዋል። የሴቶችን የሥራ ጫና ለመቀነስ በተለይም በቤት ውስጥ ያለውን የሴቶችን የሥራ ጫና ለማቃለል በ2008 የበጀት ዓመት 883,421 ሴቶች ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።

እንዲሁም በ2009 የበጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት 563,765 ሴቶች የሶላር ማሾ፣ ጎንዝየና የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል።

በ2008 የበጀት ዓመት 7,629,320 ሴቶች ብር 2.9 ቢሊዮን በመቆጠብ የኢኮኖሚ አቅማቸውን ማጎልበት የቻሉ ሲሆን 1.8 ሚሊዮን ሴቶችን የብር 4.1 ቢሊዮን የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። በ2009 የበጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራትም 1,222,097 ሴቶች ብር 1,046,852,489 መቆጠብ የቻሉ ሲሆን 1,073,833 ሴቶች የብር 1,791,983,542 በረጅምና በአጭር ጊዜ የሚከፈል ተዘዋዋሪ የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል።

መንግስት የህብረተሰቡን የመኖሪያ የቤት ችግር ለመፍታት በከተሞች የቤቶች ግንባታን እያካሄደ ይገኛል። በዚህም መሠረት በመንግስት እየተገነቡ ካሉ የከተማ የጋራ መኖሪያ ቤቶች መካከል 30 በመቶ ያህሉን ለሴቶች ብቻ እያስተላለፈ ሲሆን 70 በመቶ ያህሉን ደግሞ ከወንዶች ጋር በጋራ በዕጣ እያስተላለፈ ይገኛል። የሴቶችን ማህበራዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በተለይ በትምህርትና በጤና አገልግሎት ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል። በትምህርት ዘርፍ በ2008 የበጀት ዓመት ለ5,529,128 የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ በመፍጠር 2,352,821 ሴቶች በተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ተሳታፊ መሆን ችለዋል።

ሴቶች በሀገሪቱ የፖለቲካ መድረክ የሚያደርጉት ተሳትፎ እያደገ መጥቷል። በዚህም በተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ መቀመጫ የያዙ ሴቶች ሽፋን 38.7 በመቶ ደርሷል። እንዲሁም በወረዳና ቀበሌ ምክር ቤቶች ያለው የሴቶች ተሳትፎ ድርሻ 50 በመቶ የደረሰ ሲሆን በክልል ምክር ቤቶች ደግሞ 48 በመቶ ላይ ይገኛል። የሴቶችን ችግር በመፍታት ሂደት ዋነኛ ኃይሎች ሴቶች ራሳቸው መሆናቸውን በመገንዘብ የሴቶች አደረጃጀቶችን ለመደገፍና ለማጠናከር በሴቶች የልማት ፓኬጅ ውስጥ ትኩረት እንዲሰጠው ተደርጓል። ሴቶችም እነዚህን አደረጃጀቶች በመጠቀም በተወካዮቻቸው አማካኝነት በመንግስት ም/ቤቶችና መንግስት በሚያመቻቻቸው መድረኮች ላይ የሚያደርጉት ተሳትፎ እያደገ መጥቷል።

በፌዴራል ተቋማት ውስጥ የሴቶችን ብቃትና ተሳትፎ ለማሳደግ በፌዴራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀፅ 13/3 በቅጥር፣ በደረጃ ዕድገት እና ድልድል ሲኖር የልዩነት ነጥቦችን መሠረት በማድረግ ህጉ በሚፈቅደው አግባብ ለሴቶች ቅድሚያ እንደሚሰጥ (Affirmative Action) በግልፅ ተቀምጧል። የሴቶች ጉዳዮች አካታችነትን ለማጎልበት የሲቪል ሰርቪስ መ/ቤቶች የለውጥና የመልካም አስተዳደር ዕቅዶች የሴቶችንና ወጣቶችን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ በማዘጋጀት እንዲተገብሩ እና በአጠቃላይ ለሴቶችና ለአካል ጉዳተኞች ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ። በተመሳሳይ የሴቶች፣ የህፃናት የወጣቶች የልማት ጉዳዮች በሀገራዊና በየደረጃው በሚዘጋጁ የልማት ዕቅዶች ውስጥ መካተታቸውን (Mainstreaming) የማረጋገጥ ሥራዎች በመሠራት ላይ ናቸው።

የሥርዓተ-ፆታ ዕኩልነትን ለማረጋገጥ የተዘረጉ የማስፈጸሚያ መንገዶች፡- መንግስት የዘረጋቸውን የሴቶች ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ለማስፈጸም ያስቀመጣቸው ዋና ዋና የማስፈፀሚያ ስልቶች ሴቶችንና ወጣት ሴቶችን ጐጂ

ከሆኑ ባህሎች ለምሳሌ የሴቶች ግርዛት፣ ያለ ዕድሜ ጋብቻ መከላከል፣ በማንኛውም ደረጃ በሚገኝ የትምህርት ተቋም ገብቶ በፈለጉት የትምህርት ዘርፍ የመሠማራት መብታቸውን መጠበቅና ማንኛውም ፀረ ሴት የሆኑ ሕጐች እየተለወጡ በምትካቸው የሴቶችን ጥቅም በሚያራምዱ ሕጐችና ደንቦች እንዲተኩና ባሕላዊ ፀረ ሴት የሆኑ አመለካከቶች ደረጃ በደረጃ እንዲቀሩ ማድረግ የሚሉ ናቸው። በተጨማሪም ኅብረተሰቡ ስለሴቶች ሴቶችም ስለራሳቸው ያላቸው ግንዛቤ እንዲያዳብሩ ጥረት የማድረግ፣ በማንኛውም መንግስታዊ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ውስጥ የሴቶችን ጉዳይ በባለቤትነት የሚከታተል መዋቅር በመምሪያ ደረጃ ማቋቋም፣ በዓለም አቀፍ እርዳታ ሰጪ መንግስታትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለሴቶች ተብሎ የሚደረገው ማናቸውም እንቅስቃሴ ድግግሞሽ እንዳይኖርበት፣ የተቀናጀ እንዲሆንና ተጠቃሚዎቹም ሴቶች መሆናቸውን የማረጋገጥ ስልቶች ተዘርግተው ፖሊሲው በመተግበር ላይ ይገኛል።

በተጨማሪም መንግስት የሴቶች ጉዳይን አፈፃፀምና አተገባበር የሚመራና የሚያስተባብር አካል በሚኒስቴር ደረጃ አቋቁሟል። በሁሉም የመንግስት ፈፃሚ ተቋማት የሴቶች ጉዳይ የስራ ሂደቶችን በዳይሬክቶሬት ደረጃ እንዲቋቋሙ አድርጓል። በተጨማሪም የሴቶች ጉዳይ በልማት ዕቅዶች ውስጥ በባለ ብዙ ዘርፍ (Cross cutting) ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል። የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አንዱ የማስፈፀሚያ ስልት የሴቶችንና የወጣቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ ነው። በከፍተኛ ትምህርት የሴት ተማሪዎችንና የሴት መምህራንን ተሳትፎ ለማሳደግ የልዩ ትኩረት ተግባር (Affirmative Action) በስራ ላይ ይውላል።

በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች፡- የሴቶችን ዕኩልነት ከማረጋገጥና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ከማስወገድ አኳያ የአመለካከት ችግሮች አሁንም ትልቅ ፈተናዎች ናቸው። በመንግስት ተቋማት በኩልም በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች የሴቶችን አደረጃጀትና የሴቶችን የልማት ቡድን በመደገፍና በማብቃት ረገድ የሚታዩ ውስንነቶች፣ ለሴቶች እየተሰጠ ያለው የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት በሽፋንና በጥራት ረገድ የሚፈለገውን ያህል አለመሆን፣ የሴቶችን የሥራ ጫና የሚያቃልሉና ፍላጎታቸውን ያገናዘቡ የእርሻና የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ቴክኖሎጂዎች በሚፈለገው ደረጃ አለመቅረብ፣ በአንዳንድ አካባቢዎች የእማወራ ሴቶች የመሬት ተጠቃሚነት መብት የመጋፋት ምልክቶች መታየትና የብድር አቅርቦቱ በተለይም ለድሀ ሴቶች በሚፈለገው መጠን አለመሆን የሚሉ ችግሮች ተስተውለዋል።

የተገኙ ተሞክሮዎች፡- ሴቶች በህብረተሰቡ ውስጥ በማንኛውም መስክ መብታቸው እንዲከበርና እኩልነታቸው እንዲረጋገጥ፣ ለገጠሯ ሴት ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለማዳረስና የሴቶችን ውሳኔ ሰጭነት ለማሳደግ በሚል ማዕከላዊ ዓላማ የሴቶች ፖሊሲና የወጣቶች ፓኬጅ በመንግስት ፀድቆ ሲተገበር ቆይቷል። እየተተገበረም ይገኛል። ሌላው ዋነኛ ጉዳይ በሴቶች ፓኬጅ ውስጥ በግልፅ እንደተቀመጠው የሴቶችን ችግር ለመፍታት ዋነኛ ሃይሎች ሴቶች ራሳቸው ናቸው። ይህንንም ለመተግበር ሴቶች በንቃት የሚሳተፉባቸው በሴቶች የሚመሩ አደረጃጀቶች እንዲመሰረቱ ተደርጓል። መንግስትም የእነዚህን አደረጃጀቶች ተቋማዊ ጥንካሬ ለማሳደግና የአመራሮቹን አቅም ለማጎልበት የሥልጠናና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ሠርቷል፤ በመሥራትም ላይ ይገኛል።

የሥርዓተ ፆታ ጉዳዮች በሁሉም የልማት ዘርፍ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ውስጥ ተካቶ እየተተገበረ (Gender Main-streaming) መሆኑና ሁሉን አቀፍ የሆነ ለፆታዊ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት የሚችል ኢኮኖሚ እየተገነባ መሆኑ በተጨማሪ የተገኙ ልምዶች ናቸው። በዚህ ረገድ ሴቶችን ወደ አመራርነት በማምጣት በኩል የተገኘው ውጤት የሚጠቀስ ነው። ሴቶች ባለፉት መንግስታዊ ስርዓቶች ያጧቸውንና ከወንዶች ኋላ እንዲቀሩ በተደረጉባቸው መስኮች ላይ ለውጥ ለማምጣት በማሰብ መንግስት ለሴቶች ብቻ በሚል የልዩ ትኩረት ተግባራትን (Affirmative Ac-tion) ሲተገበር ቆይቷል። ከነዚህ የልዩ ትኩረት ተግባራት መካከል ዋነኛው ወደ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ (11-12) ትምህርትና ወደ ዩኒቨርሲቲ መግቢያ የሚያስፈልገውን ነጥብ ከወንዶች አንፃር ለሴቶች ዝቅ ማድረግ ነው። በዚህም ጥሩ ውጤት ተገኝቷል። በተጨማሪም ሀገራችን የዘላቂ የልማት ግቦችን ተፈፃሚ ከማድረግ አንፃር የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ፣

ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ የላቀ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማጎልበትና ለማረጋገጥ የሀገራትን ውጤታማ ልምድና ተሞክሮ ለመቅሰም ትሻለች።

### 7.4.5. ግብ 9።- መሠረተ-ልማት ግንባታና የኢንዱስትሪ ፈጠራ

የመንግስት ፖሊሲ አቅጣጫዎች።- በኢኮኖሚ መሠረተ ልማት መስክ የሚታዩ ማነቆዎችን በማስወገድ የአገሪቱን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ትራንስፎርሜሽን ማሳለጥ፣ የመሠረተ ልማት ተደራሽነትን በመጨመርና ጥራቱን በማረጋገጥ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ ለተልዕኳቸው ብቁ የሆኑ የመሠረተ ልማት ተቋማት በመፍጠርና በማጠናከር ለቀጣይ ዕድገት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ መሠረተ ልማትን ከኢንዱስትሪ እና ከቴክኖሎጂ ልማት ጋር አስተሳስሮ በመፈጸም የልማቱን ቀጣይነት ማረጋገጥ፣ አብዛኞቹ መሠረተ-ልማቶች በመንግስት መቅረባቸው እንዲቀጥል የሚደረግ ቢሆንም በተመረጡት ላይ በመንግስትና በግል ሽርክና (Public-Private partnership) ሊለሙና ሊቀርቡ የሚችሉበት መንገድ በጥናት ተለይቶ ተግባራዊ ይደረጋል። ከመሠረተ ልማት ዘርፍ ዕድገት ጋር የተገናኙ የድህረ 2015 ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የልማት ግቦች ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ሀገራዊ የልማት አጀንዳዎች ጋር ተጣጥመው ሥራ ላይ እንዲውሉ እየተደረገ ይገኛል።

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በኢንዱስትሪ ልማት መስክ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን በምርትና ምርታማነት፣ በኤክስፖርት ድርሻ፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር እና ለዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ቀዳሚና የመሪነት ሥፍራ እንዲይዝ አቅጣጫ ተቀምጧል። እንዲሁም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን ዓላማ ለማሳካት ጠንካራ የሰው ሃብት ልማት በመገንባት ለልማታዊ ባለሀብቱ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ ከዘላቂ የአካባቢ ልማት ጋር የተጣጣመ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪን በመገንባት የማህበራዊ ልማትን የሚደግፍ፣ የአካባቢ ተጽዕኖ የማያስከትል አረንጓዴ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዕድገትን ማረጋገጥ የመንግስት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ናቸው።



የኢኮኖሚ መሠረተ ልማት በ2017 ሀገራችንን ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተቀመጠውን ራዕይ ለማሳካት የሚያስፈልገውን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት በሚደግፍ ደረጃ፣ ጥራትና ፍጥነት እንዲያድግና ኢኮኖሚው ተወዳዳሪ እንዲሆን እንዲሁም ሁሉን-አቀፍ ዕድገት እንዲመጣ ለማድረግ የላቀ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ ይገኛል። በተመሳሳይ ከመሠረተ ልማቶች ጋር የተሳሰረ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት የፓርክ እና የክላስተር አደረጃጀቶችን በመከተል በስፋት እየተከናወነ ይገኛል። በአጠቃላይ የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት የተዘጋጀው የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተለያዩ የመሠረተ ልማት ግንባታ አገልግሎቶችን ከኢንዱስትሪ ልማት እንቅስቃሴዎች ጋር በአጠቃላይ እና ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ጋር በተለይ በማስተሳሰር የተቀናጁ እና የተደራጁ የልማት ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ። በዚህም መሠረት በመሠረተ-ልማት ግንባታ እና በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ማስፋፋት የሚከተሉት የአፈፃፀም ውጤቶች ተመዝግበዋል።

*የመሠረተ-ልማት ግንባታ*

**ዝርዝር አፈጻጸም፡-** በመንገድ፣ በባቡር፣ በኢነርጂ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና በሌሎች መሠረተ-ልማቶች የተቀናጁ ሥራዎች በመካሄድ ላይ ናቸው። በዚህም መሠረት የመንገድ መሠረተ-ልማት ግንባታን በተመለከተ ሁሉንም የሀገሪቱ የገጠር ቀበሌዎች ክረምት ከበጋ ከሚያገለግሉ ዋና

መንገዶች ጋር ለማገናኘት መንግስት ከፍተኛ የማስፈፀሚያ ሀብት በመመደብ የልማት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል። ከዚህ አንፃር ክረምት ከበጋ የሚያስኬድ የመንገድ ርዝመት በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 110,414 ኪ.ሜ. በ2008 በጀት ዓመት ወደ 113,067 ኪ.ሜ. ማሳደግ ተችሏል። በዚህም በአማካይ ወደ ክረምት እና በጋ የሚያስኬዱ መንገዶች ላይ ለመድረስ የሚወስደው ጊዜ በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 1.7 ሰዓት በ2008 የበጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 1.6 ሰዓት እንዲሁም ክረምት እና በጋ ከሚያስኬዱ መንገዶች ከ5 ኪ.ሜ. በላይ ርቀው የሚገኙ አካባቢዎች ከ36.6 በመቶ ወደ 35..8 በመቶ ዝቅ እንዲሉ አስችሏል። የመንገድ ጥግግቱም በ2007 ከነበረበት 100.4 ኪ.ሜ/ ካሬ.ኪ.ሜ በ2008 መጨረሻ ወደ 108.2 ኪ.ሜ/ካሬ.ኪ.ሜ ማድረስ ተችሏል። በመንገድ ዘርፍ እየተመዘገቡ ያሉ ከፍተኛ የልማት ስኬቶች የኢኮኖሚ እድገትንና ማህበራዊ ልማትን በማፋጠን ድህነትን ለማጥፋትና የህዝቦችን ብልፅግና ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው።

የባቡር መሠረተ ልማትን በተመለከተ የዕቃና የሰው ትራንስፖርት ወጪ ቆጣቢና የአየር ብክለትን የማያስከትል የትራንስፖርት አገልግሎት ለማስፋፋት እና የቀጠና ትስስርን ለማጠናከር በመንግስት በተያዘው አቅጣጫ መሠረት የባቡር መሠረተ ልማት ግንባታን በማፋጠን ላይ ትገኛለች። ከዚህ አንፃር የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ምዕራፍ አንድ ፕሮጀክት ሥራው ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ በ2008 የበጀት ዓመት የትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። የሀገር አቀፍ የባቡር መሠረተ ልማት ግንባታን በተመለከተ የአዲስ አበባ-ሰበታ- መኢሶ-ደወንሌ የግንባታ ፕሮጀክት አፈጻጸም 99.2 ደርሷል።። በተመሳሳይ መቀሌ-ሀራ ገበያ እና አዋሽ-ሀራ ገበያ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በቅደም ተከተል 36.03 በመቶ እና 46.18 በመቶ ደርሷል። ይህም የባቡር መሠረተ-ልማት ግንባታ በተቀመጠለት አቅጣጫ እየተፈፀመ መሆኑን ያመለክታል።

የኢነርጂ መሠረተ ልማትን በተመለከተ አገራችን በ2017 ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለማሰለፍ እና የኢንዱስትሪ፣ የግብርናና የአገልግሎት ዘርፎች የሚፈልጉትን ሀይል እንዲያገኙ ጥረት እየተደረገ ይገኛል። በዚህም መሠረት ከታዳሽ ሀይል ማመንጫዎች ማለትም ከውሃ፣ ከጂኦተርማል፣ ከንፋስ እና ከፀሐይ ኃይል የማመንጨት ሥራዎች ተጠናክረው ቀጥለዋል። ከዚህ በተጨማሪ በአፍሪካ የመጀመሪያውና በአዲስ አበባ የሚገኘው ከደረቅ ቆሻሻ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት በግንባታ ላይ ያለው ፕሮጀክት ወደ መጠናቀቅ ደርሷል። ፕሮጀክቱ ከደረቅ ቆሻሻ ኤሌክትሪክ ማመንጨት ከማስቻሉ ባሻገር ለአዲስ አበባ ከተማ ጽዱና አረንጓዴ ልማት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ታምኖበታል። የሚመነጨው ሀይል በከተማም በገጠርም ኃይል ቆጣቢ በሆነ መንገድ ተደራሽ ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል። ይህም በአንድ በኩል የማገዶ ፍላጎትን በመቀነስ የህብረተሰቡን የኢነርጂ ፍላጎት ለማሟላት እና በሌላ በኩል የግብርና፣ የኢንዱስትሪ እና የአገልግሎት ዘርፎች ልማትን ከአየር ብክለት በፀዳ መልኩ ለመደገፍ አስተማማኝ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ማቅረብ ያስችላል።

በዚህም መሠረት የኤሌክትሪክ ኃሐሓሓይልየይል ማመንጨት ሀገራዊ አቅም በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 4,269.5 ሜ.ዋ. ማድረስ ተችሏል። በመገንባት ላይ ያሉ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች አፈፃፀምም በተቀመጠለት አቅጣጫ እየተከናወነ ነው። ከዚህ አንፃር በዓባይ ወንዝ ላይ እየተገነባ ያለው የታላቁ ህዳሴ የኃይል ማመንጫ ግድብ ፕሮጀክት አፈፃፀምም በ2009 የበጀት ዓመት 57 በመቶ ደርሷል። በአሁኑ ጊዜ የግድቡ ሥራ በሶስት ዙሮች የ24 ሰዓት የማያቋርጥ የሥራ እንቅስቃሴ በመከናወን ላይ ነው። በሌላ በኩል ከተለያዩ የኃይል ማመንጫዎች የሚመነጨውን ኃይል ወደ ተጠቃሚዎች ለማድረስ የኃይል ማስተላለፊያ መሥመሮች የዝርጋታ ሥራ እየተከናወነ ሲሆን የተዘረጋው መስመር በ2007 የበጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረበት 14,065 ኪ.ሜ. በ2008 ወደ 15,137 ኪ.ሜ. ከፍ ብሏል። የኤሌክትሪክ ማሰራጫ/ማከፋፈያ መሥመር ግንባታን በተመለከተ የመካከለኛ ማከፋፈያ መሥመር ርዝመትን በ2007 የበጀት ዓመት ከነበረበት 88,266 ኪ.ሜ. በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 94,351.8 ኪ.ሜ. እንዲሁም የዝቅተኛ ማከፋፈያ መሥመር ርዝመትን ከ100,939 ኪ.ሜ. ወደ 105,687.8 ኪ.ሜ. ከፍ ማድረግ ተችሏል። በዚህም መሠረት የደንበኞች ቁጥር በ2007 ከነበረበት 2.31 ሚሊዮን በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 2.49 ሚሊዮን የደረሰ ሲሆን፣ ሀገራዊ

የኤሌክትሪክ ሽፋንም በ2007 ከነበረበት 54.25 በመቶ በ2008 ወደ 56 በመቶ ደርሷል። ይህ አፈፃፀም ሀገራዊ የኤሌክትሪክ ሽፋኑን ይበልጥ ለማሳደግ ትኩረት ተሰጥቶ መሠራት እንዳለበት የሚያመለክት ነው።

የዲጂታል መሠረተ ልማትን በተመለከተ በቴሌኮሙኒኬሽን ንዑስ ዘርፍ የሞባይል ስልክ፣ የብሮድባንድ ኢንተርኔትና ዳታ፣ የናሮው ባንድ ኢንተርኔትና ዳታ እና የመደበኛ ስልክ ደንበኞችን ብዛት በቅደም ተከተል በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 40.0፣ 1.6፣ 8.0 እና 0.084 ሚሊዮን በ2008 በጀት ዓመት 46.0፣ 4.9፣ 8.7 እና 1.12 ሚሊዮን ማድረስ ተችሏል። ይህ አፈጻጸም በ2009 በጀት ዓመትም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ተደርጓል። የኢንተርኔትና ዳታ ስብጥርን (density) በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 3.3 በመቶ በ2008 ወደ 15 በመቶ እና የዓለም አቀፍ ሊንክ አቅምን ከ27.9 ጊጋ ባይት በሰከንድ ወደ 37.3 ጊጋ ባይት በሰከንድ ማድረስ ተችሏል።

የስኩልኔት አገልግሎቶችን ከማዳረስ አንፃር እስከ 2009 የበጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት 1,510 የመንግስት ትምህርት ቤቶች አገልግሎቱን እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 565 የብሮድባንድ ኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል። መንግስት የገጠሩን ህብረተሰብ የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለማድረግ በያዘው ሰፊ ዕቅድ መሠረት ከ1,600 በላይ የገጠር ሁለገብ የኮሙዩኒኬሽን ማዕከላት እንዲቋቋሙ የተደረገ ሲሆን በእነዚህ ማዕከላት ውስጥ ከ5,400 በላይ ለሚሆኑ ወጣቶች የሥራ ዕድል ለማስገኘት ተችሏል። በዚህም የገጠሩ ማህበረሰብ ለመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ቅርብ እንዲሆን በመደረጉ መረጃዎችን በአጭር ጊዜ እና በተፈለገው ሁኔታ እንዲያገኝ በማስቻል ምርትና አገልግሎቶችን በቀላሉ ወደ ገበያ ለማቅረብና የአኗኗር ዘዴውንም ለማሻሻል እንዲያስችል በሰፊው በመሠራት ላይ ያለ ነው።

በተመሳሳይ እስከ 2009 የበጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ዓለም አቀፍ ትብብርን ከማሳደግ አኳያ ኢትዮጵያ አባል በሆነችባቸው ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የዘርፉ ማህበራት የትብብርና የድጋፍ ሥራዎች ላይ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ላይ ትገኛለች። ሀገሪቱ ከውጭው ዓለም ጋር ለመገናኘት የሚያስችሉ ዓለም አቀፍ የመገናኛ መስመሮች (International Gateway) በኬኒያ፣ በጂቡቲ እና በሱዳን በኩል እንዲኖራት የተደረገ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ በሳተላይት አማካኝነት ዓለም አቀፍ ግንኙነቱ እንዲሰፋ ተደርጓል። የዓለም አቀፍ የንግድ አጋሮችን በሚመለከት ከ505 የሮሚንግ ፓርትነሮች፣ ከ26 የኢንተርኔት የድምጽ አጋሮች እና ከ5 የኢንተርኔት የግንኙነት አጋሮች ጋር ሥራዎች በጋራ በመካሄድ ላይ ይገኛሉ።

የአየር ትራንስፖርትን በተመለከተ የበረራ ደህንነትና ጸጥታ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማስቻል የአየር ትራንስፖርት አገልግሎትን ተቋማዊ አቅም የመገንባት፣ ብቃትና ተወዳዳሪነት ያለው የአየር ትራንስፖርት አገልግሎትን የመስጠት እና የአየር ትራንስፖርት አገልግሎትን ተደራሽነት የማስፋት ሥራዎች በትኩረት ተይዘው በመከናወን ላይ ናቸው። በዚህም መሠረት የመንገደኛ መቀመጫ አቅርቦት በኪሎ ሜትር በ2008 የበጀት ዓመት ለውጭ ሀገር በረራ 39.2 ቢሊዮን እና ለሀገር ውስጥ 666 ሚሊዮን በጥቅሉ 39.666 ቢሊዮን የመንገደኛ መቀመጫ ማቅረብ ተችሏል። በተመሳሳይ የጭነት መጠን በቶን ኪሎ ሜትር 1.4 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን ከአዲስ አበባ ወደ ውጭ መዳረሻዎች 71.5 ሚሊዮን ቶን ማጓጓዝ ተችሏል።

በ2009 የበጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት አፈፃፀም መረጃዎች መሠረት የመንገደኛ መቀመጫ ጠቅላላ አቅርቦት ወደ 42 ቢሊዮን ከፍ ብሏል። እንዲሁም የጭነት አቅርቦትን በቶን ኪሎ ሜትር 9.5 ቢሊዮን ማድረስ ተችሏል። አየር መንገዱ ተቋማዊ አቅሙን በማጠናከር፣ የገበያ ማስፋፊያና ማጠናከሪያ ሥራዎችን በመሥራት እና የአገልግሎት አድማሱን በማስፋት በዓለም አቀፍ የቀጥታ በረራ መዳረሻዎችን 98 እንዲሁም የሀገር ውስጥ መዳረሻዎችን 22 ማድረስ ተችሏል። በየ10 ሺህ በረራዎች የሚኖረውን የአደጋ አጋጣሚ ከዓለም አቀፍ ከሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ኦዲት ስታንዳርድ ኢንዴክስ (0.50) አንፃር ተፈፃሚ በማድረግ በአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም ቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በቀን ካለው አማካይ 220 በረራ የአደጋ መጠን አመልካች ኢንዴክሱን 0.505 ማድረስ ተችሏል።

በተቀናጀ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ረገድ የዘርፉን አገልግሎት ለማሳደግ ልዩ ልዩ ተግባራት ተከናውነዋል። አንድ የጭነት ተሽከርካሪ ዓመታዊ የኪ.ሜ

ሽፋን በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 99,000 ኪ.ሜ. በ2009 የበጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት 100,000 ኪ.ሜ ሲደርስ የአንድ አውቶቡስ በዓመት የሚሸፍነው ርቀት በአማካይ 95,000 ኪ.ሜ ደርሷል። በዚህም በመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት 400 ሚሊዮን ደንበኞችን ማጓጓዝ ተችሏል። የብዙሐን ትራንስፖርት ድርሻን 36 በመቶ ሲደርስ አገልግሎት ለማግኘት አማካይ የመጠበቂያ ጊዜን 18 ደቂቃ ማድረስ ተችሏል። ይሁን እንጂ በተሽከርካሪ ትራፊክ አደጋ ምክንያት በየ10,000 ተሽከርካሪዎች የሚደርሰውን የሞት አደጋ ትርጉም ባለው መልኩ መቀነስ ባለመቻሉ መጣኔው በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 60/10,000 በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 63/10,000 ከፍ ሲል በ2009 የበጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ወደ 62/10,000 ዝቅ ብሏል። በተሽከርካሪዎች ከሚደርሰው የሞት አደጋ አንፃር ባለፉት ዓመታት የተመዘገበው አፈፃፀም ትርጉም ባለው ሁኔታ አደጋው እየቀነሰ እንዳልሆነ ያመለክታል። ከዚህ አንፃር ችግሩን ከመሠረቱ ለማስወገድ መንግስት የ10 ዓመት የብሔራዊ የመንገድ ደህንነት ዕቅድ የድርጊት መርሐ-ግብር አዘጋጅቶ ወደ ትግበራ ገብቷል። የድርጊት መርሐ-ግብሩን አፈፃፀም በቅርብ እየተከታተለ ድጋፍ የሚያደርግ ብሔራዊ የመንገድ ደህንነት ምክር ቤት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተቋቁሟል። የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ተሻሽሎ ተግባራዊ እየተደረገ ሲሆን የአሽከርካሪ እና የትራንስፖርት ትራፊክ ብቃት ማረጋገጫ አዋጅ ማሻሻያ ተዘጋጅቶ ለመንግስት ቀርቧል።

የመጠጥ ውሃና መስኖ መሠረተ ልማትን በተመለከተ አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን ለማሳደግና የተሻሻለ የፍሳሽ አወጋገድ ስርዓት ለመፍጠር፣ የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት አገልግሎትን ደረጃ በማሻሻል ተደራሽነቱን ለማስፋት፣ የውሃ ሀብታችን መጠንና ጥራት በማወቅ በኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተጽዕኖ በመለየት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እንዲደግፍ ለማስቻል፣ በብሔራዊ ደረጃ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ መካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ እርሻዎችን ለማልማትና ለማስፋፋት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ይገኛል። በዚህም መሠረት የንፁህ መጠጥ ውሃ ሽፋን በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት በገጠር ከ59 በመቶ፣ በከተማ ከ51 በመቶ እና በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ58 በመቶ በ2008 በጀት ዓመት ወደ 61.1 በመቶ፤ 52.5 በመቶ እና 61 በመቶ ማሳደግ ተችሏል። በዚህም በገጠር 4.54፤ በከተማ 0.70፤ በድምሩ ለ5.24 ሚሊዮን ሰዎች የመጠጥ ውሃ ተደራሽ ለማድረግ ተችሏል። በመስኖ መሠረተ ልማት በመካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ ጥናትና ዲዛይን እና የመስኖ ግንባታ በቅደም ተከተል 71,291 ሄክታር እና 39,785 ሄክታር ማከናወን ተችሏል።

የኢንዱስትሪ ፈጠራ

**ዝርዝር አፈጻጸም፡-** የኢንዱስትሪ ዘርፍ አጠቃላይ ዕድገት በ2008 በጀት ዓመት 20.6 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል። ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻም በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 15 በመቶ በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 16.7 በመቶ አድጓል። የማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፍ በ2007 የበጀት ዓመት ከጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርት የነበረው የ4.9 በመቶ ድርሻ በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 5.4 በመቶ ከፍ ብሏል። በማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፍ በ2008 የበጀት ዓመት የተመዘገበው ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ አፈፃፀም ከቀዳሚው የበጀት ዓመት አፈፃፀም ጋር ሲነፃፀር መጠነኛ መሻሻል የታየበት ቢሆንም አሁንም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ የንዑስ ዘርፉን ኢንቨስትመንት ማስፋፋትና ምርታማነቱን ማሳደግ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሠራበት ይገባል።



የማስፈጸሚያ መንገዶች:- የመሠረተ ልማትና የኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት የማስፈጸሚያ መንገዶች በዋነኝነት የሀገር ውስጥ አቅም ነው። የመሠረተ-ልማት እና የኢንዱስትሪ ልማት የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ተፈፃሚ ለማድረግ የተዘረጉ ተቋማዊ አሠራሮችን እና አደረጃጀቶችን በቅልጥፍና እና በውጤታማነት በመጠቀም ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን የሀገር ውስጥ ሀብት በአግባቡ ማሰባሰብና መጠቀም፣ ቁጠባን በማሳደግ፣ በበቂ ግንዛቤ እና ሀገራዊ መግባባት ላይ በመመሥረት ህብረተሰቡን በተደራጀ እና በተቀናጀ አግባብ ለልማት ማንቀሳቀስ ዋና ዋና የማስፈፀሚያ መንገዶች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ የዓለም አቀፍ አጋርነትን በማጠናከር የሚገኙ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂ እና ቴክኒካል ድጋፎችን ውጤታማ በሆነ አግባብ መጠቀም በተጨማሪነት ታሳቢ የተደረገና እየተሠራበት ያለ የማስፈፀሚያ መንገድ ነው።

በዚህም መሠረት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን በፓርክና በክላስተር አደረጃጀት ከማስፋፋት አንፃር ጥራት ያለው የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ አቅሙና ፍላጎቱ ያላቸው የውጭ ባለሃብቶችንና ኩባንያዎችን በጥንቃቄ በመመልመል በተለይም ኤክስፖርት-ተኮር በሆኑ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች እንዲሠማሩ የማድረግ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል። በቀጣይም ተጠናክሮ ይቀጥላል። ጥራት ያለው የውጭ ኢንቨስትመንትን ከመሳብ እና አህጉራዊና አለም አቀፋዊ ግንኙነትን ከማጠናከር አንፃር መንግስት እያካሄደ ያለውን የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ይበልጥ በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥል በማድግ የተቀናጁና የተደራጁ ሥራዎች በመሠራት ላይ ናቸው። በተመሳሳይ የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት የምርታማነትና ተወዳዳሪነት የጥራትና የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው። ከዚህ አንፃር የካይዘን የአመራር ፍልስፍና ትግበራን ይበልጥ በማስፋፋት እና በጥቃቅን፣ በአነስተኛና መካከለኛ እንዲሁም በከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችና የኢንዱስትሪ ዘርፍ አቅምን በሚገነቡ የትምህርትና ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማት እንዲሁም የኤክስቴንሽን ድጋፍ ሰጪ ተቋማት በመተግበር የማያቋርጥና ተከታታይነት ያለው የተሻለ የምርታማነት፣ የጥራትና የተወዳዳሪነት፣ የወጪ ቅነሳና የሥራ አካባቢና ሠራተኛ ደህንነት ከሁሉም በላይ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት በትኩረት ተይዞ እየተሠራ ይገኛል።

ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የኢንዱስትሪ ልማት መገንባትን በተመለከተ ፈጣን፣ ቀጣይና አስተማማኝ የኢንዱስትሪ ዕድገትን ለማረጋገጥና ሂደትም ከላይ በየደረጃው የተቀመጡ ግቦችን በሚገባ ለማሳካት የአካባቢ ተጽእኖን የማያስከትሉ አረንጓዴ ኢንዱስትሪ ዕድገትን ከማረጋገጥ አንፃር የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ከብክለት የፀዳ አካባቢን ለመፍጠር አስፈላጊ የሆኑ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች እና ግብዓቶችን እንዲያሟሉ በማድረግ፣ ታዳሽ ያልሆኑ የሀይል ምንጮችን በንፋስ፣ በፀሃይ እና በሌሎች ታዳሽ ኃይል በመተካት የሙቀት አማቂ ጋዞችን (Green House Gases) የመቀነስ ስራዎች ይከናወናሉ። የዘርፉ ፋብሪካዎች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የመልሶ መጠቀም ሥርዓት እንዲዘረጉ እንዲሁም የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣርያ ጣቢያ እስከ ሁለተኛ ደረጃ እንዲኖራቸው ሙያዊ ድጋፍ የመስጠትና የመከታተል፣ የዓለም አቀፍ ህጎችና ስምምነቶችን በተመለከተ ሥልጠና እና የምክር አገልግሎቶችን የመስጠት ተግባራት በትኩረት እየተከናወኑ ሲሆን እነዚሁ ተጠናክረው ይቀጥላሉ። በተጨማሪም የደረቅ ቆሻሻ የመቀነስ እና መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል እና ኢንዱስትሪው ያለበት የአየር ብክለት ደረጃ (baseline) ጥናቶች የማካሄድ እና የጥናቱንም ውጤት ለተጠቃሚው የማስተዋወቅ እና ስራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል።

በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች:- በመሠረተ-ልማት እና በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት በተዘጋጀው ሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጡ ግቦችን ተፈፃሚ ለማድረግ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ውስንነት ትልቅ ፈተና ነው። በተለይ በፕሮጀክት ማኔጅመንት (በማቀድ፣ በመተግበር፣ በመከታተል፣ ኮንትራት በማስተዳደር) እንዲሁም በማኑፋክቸሪንግ ምርቶች መጠንና ጥራት ተወዳዳሪ ለመሆን የአቅም ውስንነቶች ከፍተኛ ፈተናዎች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ በ2008 እና በ2009 የበጀት ዓመታት በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የተከሰተው ድርቅ ውስን የሀገር ውስጥ ሀብትን ከመሻማት አንፃር በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጡ መሠረተ-

ልማት እና የኢንዱስትሪ ልማት ግቦችን ከማስፈፀም አንፃር አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል። እነዚህን ፈታኝ ሁኔታዎች ለመፍታት እና የትራንስፎርሜሽን ዕቅዱንና የዘላቂ ልማት ግቦችን በተቀመጠላቸው ኢላማና የትግበራ ጊዜ ተፈፃሚ ለማድረግ የተደራጁና የተቀናጁ የልማት ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው። ይሁን እንጂ የአየር ንብረት ለውጥን ተከትለው የሚከሰቱ አደጋዎችን ለመቀልበስ በዓለም አቀፍ እና በአህጉር አቀፍ ደረጃዎች ከምንጊዜውም በላይ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶና አስፈላጊው የማስፈፀሚያ ሀብት ተመድቦ ትስስርና ተመጋጋቢነት ያላቸው የልማት ሥራዎች መከናወን አለባቸው።

በአፈፃፀም ሂደት የተገኙ ተሞክሮዎች፡- የተሟላ መሠረተ-ልማት ለፈጣንና ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚ ዕድገት/ኢንዱስትሪ ልማት፣ ማህበራዊ ልማት እና አካባቢ ልማት እንዲሁም ድህነትን ለማጥፋት የሚደረገውን ሁሉን አቀፍ የልማት ዕንቅስቃሴ ለማፋጠን ወሳኝ ጉዳይ ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግስት ለመሠረተ-ልማት ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጡ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ በራሱ የውስጥ አቅም ያከናወናቸውና እያከናወናቸው ያሉ የመሠረተ ልማት ሥራዎች በተለይም የኃይል ማመንጫ ግንባታዎች (ለምሳሌ የታላቁ የህዳሴ ግድብ...ወዘተ) የሀገር ፖሊሲ ነፃነትን በማስጠበቅ ዜጎችን ከድህነት የሚያላቅቁ መሆናቸው ግልፅ ሆኗል። ይህም የኢትዮጵያ መንግስት በሚከተላቸው የልማት ፖሊሲዎች የተገኘ ትልቅ ተሞክሮ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያ ከግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ እያደረገች ባለችው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ሁሉንም አገልግሎቶች ከአንድ መስኮት ማግኘት የሚያስችል የኢንዱስትሪዎች ፓርክ እና ክላስተር አደረጃጀት ባለሀብቶችን በመሳብ የኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ከማስፋፋት አኳያ የሚወሰድ መልካም ተሞክሮ ነው።

### 7.4.6. ግብ 14፡- የውሀ ሥነ ምህዳርን ለዘላቂ ልማት መጠበቅ

የመንግስት ፖሊሲ አቅጣጫዎች፡- የሀገሪቱን የውሃ ኃብት ፖሊሲና ስትራቴጂ መሠረት በማድረግ ቀልጣፋና ተስማሚ በሆነ መልኩ ውሀን በመጠቀምና በማልማት ፈጣንና ዘላቂ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ማምጣት፣ ጐርፍና ድርቅን የመሳሰሉ ክስተቶችን መከላከልና መቆጣጠር ትኩረት የሚሰጣቸው ተግባራት ናቸው። የውሃ ሀብት አጠቃቀምና ልማት እንዲሁም ጥበቃና እንክብካቤው ጐን ለጐን የሚሄዱ መሆናቸውን በመገንዘብ የመጠጥ ውሃ፣ የመስኖ ልማት፣ የውሃ ነክ መሠረተ ልማቶች፣ የተፋሰስ አስተዳደርና እንክብካቤ የመሳሰሉት ተግባራት በተቀናጀ መልኩ እንዲካሄዱ ይደረጋል። የውሃ ኃብት አስተዳደር ከሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶችና ከሌሎች የዘርፍ ልማት ግቦች (ግብርና፣ ጤና፣ ማዕድን፣ ኢነርጂ፣ ወዘተ...) ጋር የተጣጣመና የተቀናጀ ሆኖ ተፈፃሚ ይሆናል። እንዲሁም የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት በተዘጋጀው ሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ዘመን (2008-2012) የመጠጥ ውሀ አቅርቦት፣ የመስኖና ድሬኔጅ ልማት፣ የውሀ ኃይል ጥናትና ዲዛይን፣ የከርሰ ምድርና የገፀ ምድር ውሀ ጥናት እና የተቀናጀ የተፋሰስ ማስተር ፕላን ማኔጅመንት በዘርፉ በትኩረት ተይዘው የሚከናወኑ ናቸው።



የውሀ ስነ ምህዳርን ለዘላቂ ልማት መጠበቅ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነትን እና የአካባቢ ደህንነትን ያጎለብታል። ከዚህ አንፃር የሀገራችን ዋና የልማት አለኝታ የሆኑት መሬት፤ ውሀ እና ሰፊ የሰው ጉልበት የመንግስት ፖሊሲ አቅጣጫዎችን መሠረት በማድረግ በመልማት ላይ ይገኛሉ። በዚህም መሠረት የከርሰ ምድር እና የገፀ-ምድር ውሀን የሚያበለፅጉ፣ ብዝሀ ህይወትን የሚጠብቁ፣ አፈርንና ውሀን ከመሸርሸር አደጋ የሚታደጉ፣ እየተገነቡ ያሉ ትላልቅ የኢነርጂ መሠረተ-ልማት ግድቦችን እና ሀይቆችን

ከደለል የሚከላከሉ፣ ለግድቦችና ለሀይቆች ዓመቱን ሙሉ አስተማማኝ የውሀ ፍሰት እንዲኖር የሚያስችሉ እና የወራጅ ወንዞች፣ የግድቦችና የሀይቆች የውሀ አካላትን ከግብርና የኬሚካል ግብዓት ቅሪቶች ብክለት የሚከላከሉ የተቀናጁና የተደራጁ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የተፋሰስ ልማት ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው።

የሀገሪቱን የውሀ ኃብት የፖሊሲ አቅጣጫዎች መሠረት በማድረግ የውሀ ስነ ምህዳርን ለዘላቂ ልማት ከመጠበቅ እና ጥቅም ላይ ከማዋል አንፃር በሀገር ውስጥ ክልሎችን አቋርጦ የሚፈስ ወይም ከክልሎች ጋር የሚዋስን የውሀ አካል በልዩ ልዩ የአገልግሎት ዓይነቶችና በክልሎች መካከል ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትን እና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ የመወሰን አቅጣጫ ተቀምጦ እየተሠራ ይገኛል። በወሰንና ወሰን ተሻጋሪ የውሀ አካላት አጠቃቀም ላይም ጥናቶችን በማካሄድ ዓለም አቀፍ ውሎችን የመደራደር እና አፈፃፀማቸውን የመከታተል፣ የመካከለኛና የከፍተኛ የመስኖ ልማት ሥራዎችን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የጥናት፣ ዲዛይንና የግንባታ ሥራዎችን እንዲካሄዱ የማድረግ ኃላፊነቶች በፌዴራል መንግስት እየተፈፀሙ ያሉ ሥራዎች ናቸው። በዚህም መሠረት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎሜሽን ዕቅድ የትግበራ ዘመን የውሀ ሀብትን ዘላቂነት ባለው አግባብ በመጠቀም ሀገራዊ ልማትን ለማፋጠን እየተከናወኑ ያሉ የልማት ሥራዎች አፈፃፀም እንደሚከተለው ቀርቧል።

**ዝርዝር አፈጻጸም፡-** አፈርንና ውሀን ከመሸርሸር አደጋ የሚጠብቁ በተለይ ከተፋሰስ ልማት ጋር የተያያዙ በርካታ የውሃና የአፈር ጥበቃ ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው። የተፋሰስ ልማት ሥራን በሚመለከት በ2008 የበጀት ዓመት በ130,446 ሄክታር መሬት ላይ የአፈርና የውሀ ጥበቃ ማከናወን ተችሏል። ለገፀ ምድር እና ለከርሰ ምድር ውሀ ዕጥረት ዋነኛው ምክንያት የመሬት መራቆትና የአፈር መሸርሸር ነው። ይህንንም ለመከላከል በ2008 በጀት ዓመት ብቻ 1.71 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ከንክኪ ነፃ ተደርጎ እንዲያገግም ተደርጓል። በተመሳሳይ በበጀት ዓመቱ በ1.03 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ የተለያዩ የስነ-አካላዊና ስነ-ህይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች እንዲሁም ጥገናና እድሳት ተደርጓል። በዚህም መሠረት ቀደም ብሎ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የተፋሰስ ልማት በተካሄደባቸውና በአገገሙ ተፋሰሶች ላይ መሬት አልባ የህብረተሰብ ክፍሎች የአካባቢ ሥነ-ምህዳርን በጠበቀ ሁኔታ እንዲደራጁ በማድረግ 89.8 ሺህ ወጣቶች በልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል። ይህም የወጣቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ከማሻሻሉ በተጨማሪ ለአፈርና ውሀ ጥበቃ አስተማማኝ መሠረት መጣል አስችሏል።

የውሀ ስነ ምህዳርን ለዘላቂ ልማት ከመጠበቅ እና ጥቅም ላይ ከማዋል አንፃር የአርሶ አደሩን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ በተከናወኑ በርካታ የልማት ሥራዎች በአነስተኛ መስኖ የለማ መሬት በ2008 በጀት ዓመት 2.72 ሚሊዮን ሄክታር የደረሰ ሲሆን ከተደራሽነት አንጻርም 6.8 ሚሊዮን አርሶ አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮች (ወንድ 5.9 ሚሊዮን እና ሴት 0.92 ሚሊዮን) የመስኖ ልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል። መካከለኛ እና ሰፋፊ የመስኖ ልማትን በሚመለከት በ2008 የበጀት ዓመት ለ71,291 ሄክታር መሬት የጥናትና ዲዛይን ሥራዎች እንዲሁም ለ39,785 ሄክታር መሬት የመስኖ ግንባታ ሥራዎች ተከናውነዋል። ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ ወንዞች የብክለት ደረጃን ለማወቅ የሚያስችሉ የውሃ ናሙና የሚወሰድባቸው ቋሚ ጣቢያዎችን የመለየት፣ ናሙና መውሰጃ ጣቢያዎችን የማቋቋም፣ የላቦራቶሪ ምርመራ የማካሄድ እና በውጤቱ መሰረት ዘገባ የማዘጋጀት ስራዎችን እየተካናወኑ ሲሆን ይህም ውሀን ከብክለት ለመታደግና አስፈላጊውን እንክብካቤ ለማድረግ እንደሚያስችል ታምኖበታል።

መንግስት የሀገሪቱን የተፈጥሮ ሀብት በመጠበቅ፣ በማልማት እና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን አስቀምጦ እና የማስፈፀሚያ ተቋማዊ አሠራሮችን እና አደረጃጀቶችን ዘርግቶ እየሠራ ሲሆን በሁለተኛው የዕደገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመንም የውሃ ስነም-ህዳርን በመጠበቅ የሀገሪቱን የዓሳ ምርት ለማሳደግ ትኩረት ተሰጥቷል። የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር እያከናወናቸው ያሉ የልማት ሥራዎች የውሀ ስነ ምህዳርን ለዘላቂ ልማት ከመጠበቅ አንፃር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያላቸው ናቸው። እንዲሁም የልማት ኃይሎችን በማስተባበር የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ዘርፍን የልማት ዕንቅስቃሴ በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ የሚመራ ተቋም በሚኒስቴር ደረጃ ተቋቁሞ ወደ ሥራ ገብቷል። ዘርፉ

የውሀ ስነ ምህዳርን ለዘላቂ ልማት ከመጠበቅ እና በተለይም በኢትዮጵያ የሚገኙ የዓሣ ዝርያዎችን ሥነ-ምህዳራቸው በተጠበቁ የውሀ አካላት (ሀይቆች፣ ወራጅ ወንዞች እና ግድቦች) ጠብቆ ለማልማት እና ኢኮኖሚ ጠቀሜታቸውን ለማሳደግ የላቀ ኃላፊነት አለበት።

በ2008 የበጀት ዓመት በሀገሪቱ ካሉ የውሀ አካላት የተመረተው ጠቅላላ የዓሣ ምርት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት የ0.1 በመቶ ድርሻ ነበረው። በወጪ ንግድ ረገድም በ2008 የበጀት ዓመት 658 ቶን ደረቅ ዓሣ እና 1975 ቶን በጨዉ የተዘጋጀ ዓሣ ኤክስፖርት ተደርጓል። በበጀት ዓመቱ ከትናንሽ የውሀ አካላት 1294 ቶን፣ ከትልልቅ ግድቦች 9671 ቶን፣ ከወንዞች 5397 ቶን፣ ከሃይቆች 31642 ቶን እና ከአኳካልቸር 99 ቶን በድምሩ 48,103 ቶን ማምረት ተችሏል።

ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች፡- የውሀ ስነ ምህዳርን ለዘላቂ ልማት ከመጠበቅ እና ጥቅም ላይ ከማዋል አንፃር የመረጃዎች ውስንነት ትልቅ ፈተና ነው። እነዚህን የመረጃ ውስንነቶች ለመቅረፍ ሰፊ ጥናትና ምርምር ይጠይቃል በሌላ በኩል የጥናት እና ምርምር ሥራዎችን በሰፊው ለማከናወን በቂ የማስፈፀሚያ ሀብት ይጠይቃል። ባጠቃላይ በዘርፉ የሚታዩ ፈታኝ ሁኔታዎች በሰለጠነ የሰው ኃይል፣ በማስፈፀሚያ ፋይናንስ እና በመረጃዎች ውስንነት የሚገለፁ ናቸው።

የተገኙ ተሞክሮዎች፡- መንግስት ከተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀም ጋር በተያያዘ በተለይ በሀገሪቱ የገጠር አካባቢዎች በሚኖረው ህብረተሰብ ዙሪያ ለረጅም ዓመታት በሠራቸው ተከታታይ የአቅም ግንባታ ሥራዎች (የማስተማር፣ የማሠልጠን፣ በጋራ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የጋራ ግንዛቤ የመፍጠር፣ የማደራጀት...ወዘተ) እና በሰጣቸው የአመራርና የማስተባበር ድጋፎች በተለይ አርሶ-አደሩን በሙሉ ዕምነት፣ ፍላጎትና ባለቤትነት ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የተፋሰስ ልማት ማንቀሳቀስ ችሏል። በዚህም የውሀ ስነ-ምህዳርን ለዘላቂ ልማት መጠበቅ የሚያስችሉ፣ የግብርናን ምርታማነት በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ የሚያስችሉ፣ ድህነትን በተፋጠነ ሂደት ለማጥፋት እና በሀገራችን የተጀመረውን የትራንስፎርሜሽንና የህዳሴ ጉዞ የሚያሳኩ ውጤቶች እየተመዘገቡ ነው። ይህ በአርሶ-አደሩ ሙሉ ዕምነት፣ ፍላጎት እና ባለቤትነት ተይዞ እየተሠራ ያለው የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የተፋሰስ ልማት ኢትዮጵያ በግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ሂደት ያገኘችው መልካም ተሞክሮ ነው።

# ፰. የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈፀሚያ ተቋማዊ አደረጃጀቶች

ኢትዮጵያ ያልተማከለ የአስተዳደር ሥርዓት የምትከተል ሀገር ናት። ያልተማከለ የአስተዳደር ሥርዓቱ የተዘረጋው የሀገሪቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በተወካዮቻቸው አማካኝነት የአፀደቁትን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት መሠረት በማድረግ ነው። ይህ ያልተማከለ የአስተዳደር ሥርዓት በርቀት ከሚገኘው ማዕከላዊ መንግሥት ይልቅ ለህዝብ ቅርበት ላላቸው የአካባቢ አስተዳደር ዕርከኖች በቂ ሥልጣን የሰጠ ነው። በዚህም የሕዝቡን ፍላጎት በየደረጃው በተሻለ ሁኔታ በማወቅ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ለማሳተፍ እና የመንግስት አገልግሎት አቅርቦትን በቀላሉ ተደራሽ በማድረግ የሕዝብን ፍላጎት ለማሟላት እንደሚያስችል ማረጋገጥ ተችሏል።

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በመረጧቸው ተወካዮቻቸው አማካኝነት ህገ-መንግስቱን ባፀደቁበት ወቅት አንድ የጋራ ኢኮኖሚ ማህበረሰብ እና አንድ የጋራ ሀገር ለመገንባት ቃል ገብተዋል። ይህንንም ተፈፃሚ ለማድረግ የፌዴራል መንግስት የሀገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና የልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ዕቅድ የማውጣትና የማስፈፀም ሥልጣን በህገ መንግስቱ ለፌዴራል መንግስት ተሰጥቷል። በዚህም መሠረት በፌዴራል መንግስት መሪነት እና አስተባባሪነት የዘላቂ ልማት ግቦችን ያካተተ ሀገራዊ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተዘጋጅቶ በሚኒስትሮች ምክር ቤት እና በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀ በኋላ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

አጠቃላይ ሀገራዊ እና የሴክተር ፖሊሲዎችን እንዲሁም ከክልሎችና ከከተማ አስተዳደሮች ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥመው የወጡ ፖሊሲዎችን በተቀናጀ ዕቅድና ፕሮግራም አማካኝነት ባለድርሻ አካላትን በአሳተፈ አግባብ ተፈፃሚ ለማድረግ የኢትዮጵያ መንግስት በተለያዩ የአስተዳደር ዕርከኖች የማክሮና የሴክተር ተቋማዊ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በአዋጅና በደንብ በመዘርጋት አስፈላጊውን የሰው ኃይል አሰማርቷል። ሀገራዊ የልማት ዕቅድ የማዘጋጀትና የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ኃላፊነቶችን ቅንጅት፣ ትስስርና ተመጋጋቢነት በአለው አግባብ የሚመራና የሚያስተባብር፣ ተጠሪነቱ ለሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የሆነ ብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን ተቋቁሞ በሥራ ላይ ይገኛል። እንዲሁም ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን የሆኑ እና ለሀገራዊ የልማት ዕቅድና የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን (የናሙና ጥናት/የቆጠራ እና የጂኦ-ስፓሻል መረጃዎችን) የሚያመነጩ እና ለተጠቃሚዎች የሚያሰራጩ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ ተቋቁመው ኃላፊነታቸውን መወጣት ከጀመሩ በርካታ ዓመታት ተቆጥረዋል። ተቋማቱ በተቋቋሙበት ኃላፊነት መስክ የዳበረ ተቋማዊ ልምድ አካብተዋል። ይህም የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሀገራዊ የልማት ማዕቀፍ ጋር በየደረጃው በማስተሳሰር ተፈፃሚ ለማድረግ የተቀናጀ፣ ትስስርና ተመጋገቢነት ያለው ተቋማዊ አሠራርና አደረጃጀት እንዳለ በግልፅ ያሳያል። በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮችም ተቀራራቢ ወይም ተመሳሳይ አደረጃጀቶች ተዘርግተው ኃላፊነታቸውን በመወጣት ላይ ናቸው።

በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ መንግስት በየደረጃው አስቀድሞ በዘረጋቸው ተቋማዊ አሠራሮችና አደረጃጀቶች እና በእነዚህ አደረጃጀቶች በአሰማራው የሰው ኃይል ባለድርሻ አካላትን በአሳተፈ አግባብ የዘላቂ ልማት ግቦችን በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዝግጅት እንደ አንድ መነሻ በመውሰድ እና የዝርዝር ዕቅዱ አካል በማድረግ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፀድቆ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ወደ ትግበራ እንዲገቡ አድርጓል። የዕቅዱ የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሥራዎችም ከፍ ብሎ በተገለፀው አግባብ ቀደም ብለው የተዘረጉ ተቋማዊ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በመከተል በመከናወን ላይ ናቸው።

የዘላቂ ልማት ግቦችን እንደ አንድ መነሻ በመውሰድ፣ በዝርዝር የትኩረት መስኮቹ እና በመሠረታዊ አቅጣጫዎቹ በማካተት እንዲሁም እንደ አግባቡ ከማክሮ-ኢኮኖሚ፣ ከክፍላተ-ኢኮኖሚ እና ከባለብዙ ዘርፎች ዕቅዶች ዒላማዎች ጋር በማስተሳሰር የተዘጋጀው የሁለተኛው የዕድገትና

ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የዝግጅት ሂደት የተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተሳተፉባቸው የዕቅድ ዝግጅት የሚኒስትሮች ኮሚቴዎችን (Ministrial Committes) እና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ያካተቱ የረቂቅ ዕቅድ የምክክር መድረኮችን በማደራጀት የተከናዋነ ነው። የዝግጅት ሂደቱ ቅንጅት፣ ትስስርና ተመጋጋቢነት ባለው አግባብ ተፈፃሚ እንዲሆን የዕቅድ ዝግጅት የሚኒስትሮች ኮሚቴዎች እና የረቂቅ ዕቅድ የምክክር መድረኮች የሥራ እንቅስቃሴዎች ክትትልና ድጋፍ የተደረገው በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እና በብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን ነው።

ከፍ ብሎ በተገለፀው አግባብ የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት የተዘጋጀው የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመንግስት ከፍተኛ የልማት ቁርጠኝነት በማያሻማ መንገድ ግልፅ ሆኖ የተቀመጠበት፣ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በተወካዮቻቸው አማካኝነት ተወያይተውበት፣ በሀሳቦቻቸውና በአስተያየቶቻቸው አዳብረውት፣ አምነውበት እና ለተፈፃሚነቱ በጋራና የየበኩላቸውን ድርሻ እንደሚወጡ ቃል የገቡበት የአምስት ዓመት (2008-2012) ሀገራዊ የልማት ማዕቀፍ ሰነድ ነው። የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የዝግጅት ሂደት በዚህ መልክ ተጠናቅቆ በመጀመሪያ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀጥሎም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀድቋል። በዚህ አግባብ ዕቅዱ የአምስት ዓመት አስገዳጅ ሀገራዊ የልማት ማዕቀፍ በመሆን በተለያዩ የመንግስት አስተዳደር ዕርከኖች በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች እየተሠራባቸው ያሉ አሠራሮችን፣ አደረጃጀቶችን እና የሰው ኃይል በማጠናከር እና የሶስቱን የልማት ኃይሎች (ፓርቲ፣ መንግስት እና ህዝብ) አቅም አሟጦ በተቀናጀና በተደራጀ ተቋማዊ መንገድ በመጠቀም ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እና የዘላቂ ልማት ግቦች የትግበራ ሂደት በተለያዩ የመንግስት አስተዳደር ዕርከኖች (ፌዴራልና ክልል/የከተማ አስተዳደር) ተቋማዊ ኃላፊነቶችን መሠረት በማድረግ ከአፊሴላዊ የመረጃ ምንጮች (ከአስተዳደራዊ መዛግብት እና ከናሙና ጥናት/ቆጠራ) የሚሰባሰቡ የማክሮ-ኢኮኖሚ፣ የክፍላተ ኢኮኖሚ እና የባለብዙ ዘርፎች የአፈፃፀም መረጃዎችን በግብዓትነት በመውሰድ በሚዘጋጁ የአፈፃፀም ሪፖርቶች በህግ አውጪውና በአስፈፃሚው የቅርብ ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ ሲሆን በቀጣይም ይኸው ተጠናክሮ ይቀጥላል።

# 9. የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈፀሚያ ዘዴዎች

የኢትዮጵያ መንግስት የሚያካሄዳቸው የልማት ሥራዎች ሙሉ በሙሉ ከሀገሪቱ ህዝቦች ፍላጎት የመነጩ ናቸው። የዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 ህዝቦችን ከድህነትና ከረሀብ ለማላቀቅ፣ መሬትን ከጥፋት ለመታደግ እና የሰው ልጆችን የተደላደለ ኑሮ እና ብልፅግና ለማረጋገጥ የተዘጋጀ ዓለም አቀፍ አጀንዳ ነው። ይህ ዓለም አቀፍ የዘላቂ ልማት አጀንዳ ከኢትዮጵያ ህዝቦች የልማት ፍላጎት ጋር የጠበቀ ትስስር ያለው ነው። በኢትዮጵያ እየተመዘገበ ያለውን መሠረተ ሰፊ፣ ሁሉን አቀፍ እና ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት፣ የኢኮኖሚ መሠረተ ልማት፣ የማህበራዊ ልማት፣ የአካባቢ ልማት፣ የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እና በአጠቃላይም የተሀድሶ ጉዞ የሚያፋጥን ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግስት የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም ተፈፃሚ ለማድረግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ቃል ገብቷል። በሀገር አቀፍ ደረጃም የዘላቂ ልማት ግቦችን በባለቤትነት ወስዶ የሀገሪቱ የልማት ማዕቀፍ አካል በማድረግ፣ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማስፀደቅ እና በሥራ ላይ ያሉ ተቋማዊ አሠራሮችን፣ አደረጃጀቶችንና የሰው ኃይል በማጠናከር ወደ ትግበራ ገብቷል።

የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት የተዘጋጀውንና በመንግስት ፀድቆ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ወደ ትግበራ የገባውን የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በየደረጃው ውጤታማ በሆነ አግባብ ተፈፃሚ ለማድረግ በዋነኝነት መንግስት በሀገር ውስጥ ሀብት አሰባሰብ እና አጠቃቀም ላይ በማተኮር እየሠራ ይገኛል። ከዚህ አንፃር የሀገሪቱ ፈጣን የልማት እንቅስቃሴ የሚያመነጨውን የሀገር ውስጥ ገቢ በአግባቡ በማሰባሰብ በልማት ሥራ ላይ ለማዋል የኢትዮጵያ መንግስት የታክስ ሥርዓቱን በማዘመን በየጊዜው የውስጥ አቅሙን በማሳደግ ላይ ይገኛል። ከዚህ አንፃር የገቢ ሰብሳቢ ተቋማትን በአመለካከት፣ በአሠራር፣ በአደረጃጀትና በሰው ኃይል አቅም የመገንባት ሥራ ተጠናክሮ ቀጥሏል። እንዲሁም ዜጎች ከሚያካሂዷቸው የሥራ እንቅስቃሴዎች የሚያገኙትን ገቢ በትክክል በማሳወቅ የሚጠበቅባቸውን የገቢ ግብር ክፍያ በአግባቡ እንዲወጡ መንግስት በተለያዩ መንገዶች የማስተማርና ግንዛቤ የመፍጠር ሥራዎች እያከናወነ ነው። በአጠቃላይ የኢትዮጵያ መንግስት የታክስ ገቢን ለማሳደግ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን (2008-2012) የታክስ መዋቅሩን ሁለንተናዊ አቅም በመገንባት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል።

በተለያዩ የመንግስት አስተዳደር ዕርከኖች የሀገር ውስጥ ገቢ የማሰባሰብ አቅምን ለማሳደግ እስካሁን በተደረጉ የተቀናጁና የተደራጁ የልማት ዕንቅስቃሴዎች የሀገሪቱ ገቢ የማሰባበሰብ አቅም እያደገ መምጣቱን መረጃዎች ያሳያሉ። በዚህም መሠረት የሀገሪቱ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ገቢ በ2002 የበጀት ዓመት ብር 53.9 ቢሊዮን የነበረ ሲሆን ከአምስት ዓመት በኋላ በ2007 የበጀት ዓመት መጨረሻ ብር 186.6 ቢሊዮን ደርሷል። ይህ የሀገር ውስጥ ገቢ አሰባሰብ አቅም በ2008 የበጀት ዓመት መጨረሻ ወደ ብር 231.8 ቢሊዮን አድጓል። ይህ በየጊዜው እያደገ የመጣ የሀገር ውስጥ ገቢ የማሰባሰብ አቅም ኢትዮጵያ በራሷ አቅም ሰፋፊ የልማት ፕሮጀክቶችን ለማካሄድ አስችሏታል። ሆኖም የሀገሪቱ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ዝቅተኛ ሲሆን (በ2007 መጨረሻ 13.3 በመቶ) በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ (በ2012) የታክስ ገቢው ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ ወደ 17.2 በመቶ ለማሳደግ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ነው።

ሌላው የሀገር ውስጥ ሀብት የማሰባሰብ አቅምን ለማጠናከር ቀደም ብለው የተጀመሩ የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል የማሳደግ የማስተማር እና የማነሳሳት እንቅስቃሴዎች፣ የፋይናንስ አገልግሎቶች የሚሰጡባቸውን ተቋማት የማስፋፋት፣ የወለድ መጣኔን የማሻሻል፣ የግል እና የመንግስት የማህበራዊ ዋስትና ሽፋንን ይበልጥ የማጠናከር፣ የቤት የቁጠባ ፕሮግራም እና የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቁጠባ ቦንድ እና ሌሎች የቁጠባ መሳሪያዎችን አጠናክሮ የማስቀጠል ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል። የመንግስት ወጪን በዋነኝነት የካፒታል ክምችት ለሚፈጥር የኢንቨስትመንት ወጪ በመመደብ ቁጠባን ለታለመለት ዓላማ ለማዋል እየተደረገ ያለው ጥረት ተጠናክሮ ይቀጥላል። በአለፉት ዓመታት ቁጠባን ለማሳደግ የተወሰዱ እርምጃዎች ከፍተኛ ውጤት ማስገኘታቸውን መረጃዎች ያሳያሉ።

በዚህም መሠረት የሀገር ውስጥ ቁጠባ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በ2002 የበጀት ዓመት መጨረሻ 9.5 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2007 በጀት ዓመት መጨረሻ 21.8 በመቶ ደርሷል። እንዲሁም በ2008 መጨረሻ ወደ 22.4 በመቶ ከፍ ብሏል። የሀገር ውስጥ ቁጠባ መጣኔውን በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጨረሻ (በ2012) ወደ 29.6 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ እየተሠራ ይገኛል። ይህም የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት ተዘጋጅቶና በመንግስት ፀድቆ በትግበራ ላይ የሚገኘውን የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የኢንቨስትመንት ፕሮግራሞች ለማስፈፀም ቁልፍ ሚና እንደሚጫወት ይጠበቃል።

ከዚህ በተጨማሪ በተለይ በገጠሩ ህብረተሰብ በሙሉ ዕምነትና ፍላጎት፣ በተቀናጀ እና በተደራጀ አግባብ እየተከናወኑ ያሉ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የተፋሰስ ልማት ሥራዎች የዘላቂ ልማት ግቦችን ከማስፈፀም አኳያ ከፍተኛ ትርጉም ያላቸው በመሆናቸው እነዚህ የልማት ሥራዎች በከፍተኛ አመራሩ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ እየተደረገላቸው ከምንጊዜውም በላይ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ተደርጓል። የዘላቂ ልማት ግቦችን ከማስፈፀም አኳያ በአንድ በኩል የሀገር ውስጥ ሀብት የማሰባሰብ አቅምን ማሳደግ እና በሌላ በኩል ደግሞ የመንግስት በጀትን ያለምንም ብክነት፣ በቁጠባና ውጤታማ በሆነ አግባብ በዋነኝነት የካፒታል ክምችት በሚፈጥሩ የኢንቨስትመንት ሥራዎች ላይ ማዋል በትኩረት ተይዞ እየተሠራበት ያለ ሥራ ነው።

የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አካል ተደርገው የተዘጋጁ የዘላቂ ልማት ግቦችን በማስፈፀም ሂደት የሀገር ውስጥ ሀብት አሰባሰብ እና የአጠቃቀም አቅምን ከማሳደግ በተጨማሪ ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የልማት አጋርነትን በማጠናከር በኢንቨስትመንት ፋይናንስ፣ በንግድ፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለመሆን ትኩረት ሰጥታ እየሠራች ትገኛለች። በአጠቃላይ የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር በማስተሳሰር በሥራ ላይ ያሉ ተቋማዊ አሠራሮችን፣ አደረጃጀቶችን እና የሰው ኃይሉን የበለጠ በማጠናከር እና በተለያዩ የመንግስት አስተዳደር ዕርከኖች እያንዳንዱ የሴክተር አስፈፃሚ አካል በየበጀት ዓመቱ የሴክተር ዕቅዱን በአስፈላጊ በጀት ደግፎ በመንግስት በማስፀደቅ ተፈፃሚ የማድረጉ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

# 10. የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማስፈፀም ቀጣይ እርምጃዎች

የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት የተዘጋጀውንና በመንግስት ፀድቆ በትግበራ ላይ ያለውን ሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በቀጣይ ውጤታማናስኬታማ አድርጎ ለማስፈፀምና ለመፈፀም የኢትዮጵያ መንግስት በፖለቲካ አመራሩ እና በፐብሊክ ሰርቪሱ ዙሪያ የጥልቅ ተሀድሶ እና የሪፎርም እንቅስቃሴዎች ጀምሯል፡፡ እየተገባደደ ባለው የበጀት ዓመት መጀመሪያ በፖለቲካ አመራሩ የተጀመረው የጥልቅ ተሀድሶ እንቅስቃሴ በተለያዩ የመንግስት አስተዳደር ዕርከኖች የኪራይ ሰብሳቢነት ችግሮችን የሚቀርፉ፣ ልማታዊ መልካም አስተዳደርን የሚያጎለብቱ፣ የትምክህት፣ የጠባብነት እና የሀይማኖት አክራሪነት አመለካከቶችን የሚያስተካክሉ ሥር ነቀል እርምጃዎችን መውሰድ ጀምሯል፡፡ በዚህም በሀገሪቱ የተጀመረውን የትራንስፎርሜሽንና የህዳሴ ጉዞ የበለጠ የሚያፋጥኑ እና የዘላቂ ልማት ግቦችን የሚያሳኩ ምቹ ሁኔታዎች መታየት ጀምረዋል፡፡ በቀጣይ የአመለካከት፣ የአሠራር፣ የአደረጃጀትና የሰው ኃይል ግንባታ ሥራዎችን በተቀናጀና በተደራጀ አግባብ ተፈፃሚ ለማድረግ ይህ የጥልቅ ተሀድሶ እና የሪፎርም እንቅስቃሴ ሥራ መልካም ጅምር ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

በተመሳሳይ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች በፐብሊክ ሰርቪሱ ዙሪያ በተካሄዱ የጥልቅ ተሀድሶ ንቅናቄዎች ኪራይ ሰብሳቢነትና ብልሹ የሙያሥነ-ምግባር፣ የተነሳሽነትና የህዝብ አገልጋይነት መንፈስ ደካማነት፣ የብቃትና የውጤታማነት ችግሮች...ወዘተ ተለይተው በፖለቲካ አመራሩ እና በፐብሊክ ሰርቫንቱ መካከል የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ በቀጣይ እነዚህን ችግሮች በተደራጀ፣ በተቀናጀ እና ሥር ነቀል በሆነ አግባብ በመቅረፍ የህዝብ አገልጋይነት የተላበሰ፣ ተልዕኮውን በብቃትና በውጤታማነት መፈፀም የሚችል፣ ከኪራይ ሰብሳቢነትና ከብልሹ የሙያ ሥነ-ምግባር የፀዳ፣ የመንግስት ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ዕቅዶችንና ፕሮግራሞችን ጠንቅቆ የሚያውቅና የሚፈፅም ፐብሊክ ሰርቪስ ለመገንባት የተጀመሩ የሪፎርም ሥራዎች ተጠናክረው የሚቀጥሉ ይሆናሉ፡፡ ይህም የሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እና የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

በሀገራችን የተጀመረውን የትራንስፎርሜሽንና የህዳሴ ጉዞ ይበልጥ በማፋጠን በ2017 ኢትዮጵያን ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍ፣ የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት፣ የዜጎችን በልማት ዕኩል ተሳታፊነትና ፍትሀዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና በዚህም አንድ የጋራ የኢኮኖሚና አንድ የጋራ ሀገር ለመገንባት የማይተካ ድርሻ ያለው ወሳኝ የልማት እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡ ይህ የልማት እንቅስቃሴ የዘላቂ ልማት ግቦችን በማካተት በትግበራ ላይ ያለውን የሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እንደ መጀመሪያ ምዕራፍ በመውሰድ ወደ ዝግጅት ሂደት እየገባ ያለ የረጅም ዘመን (የ15 ዓመታት) ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ነው፡፡ የረጅም ዘመን ሀገራዊ የልማት ዕቅዱ ከ2008 እስከ 2022 ወይም እ.ኤ.አ. ከ2016 እስከ 2030 ባሉት ዓመታት ኢኮኖሚውን በረጅም ጊዜ ዕይታ ለመምራት ሀገራዊ የልማት ማዕቀፍ ሆኖ ያገለግላል፡፡ የረጅም ዘመን ሀገራዊ የልማት ዕቅዱ በትግበራ ዘመንም ሆነ በይዘቶቹ የዘላቂ የልማት ግቦችን ሙሉ በሙሉ በማካተት የሚዘጋጅ ሲሆን በተቻለ አጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቅቆ እና በመንግስት ፀድቆ ሥራ ላይ እንደሚውል ይጠበቃል፡፡

የዘላቂ ልማት ግቦችን በተቀመጠላቸው የትግበራ ዘመን ውጤታማ በሆነ አግባብ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል የፋይናንስ ፍላጎት ጥናት (SDGs Needs Assessment) እና የፋይናንሲንግ ስትራቴጂ ዝግጅት ተጀምሯል፡፡ የፋይናንሲንግ ፍላጎት ጥናቱ የሥራ መዘርዝሮችን ጨምሮ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተጠናቀዋል፡፡ በኢትዮጵያ መንግስት በቀረበ ጥያቄ መሠረት ጥናቱን የሚያካሂዱ ኩባንያዎች በተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም የኢትዮጵያ ጽ/ቤት አስተባባሪነት ተመርጠዋል፡፡ ጥናቱ በተቀመጠለት ፕሮግራም መሠረት በጥራት እንዲፈፀምና የፋይናንሲንግ ስትራቴጂ ዝግጅቱም በተመሳሳይ ጥራቱን ጠብቆ በፍጥነት እንዲከናወን መንግስትና የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም የኢትዮጵያ ጽ/ቤት የተቀናጀና የተደራጀ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ የዘላቂ ልማት ግቦች የፋይናንሲንግ ፍላጎት ጥናት በእያንዳንዱ ዘርፍ የዘላቂ ልማት ግቦችን ከማሳካት አኳያ ያሉ ምቹ ሁኔታዎች፣ ፈተናዎች፣ መልካም አጋጣሚዎች እና በቀጣይ መወሰድ ያለባቸው ዕርምጃዎች

ተለይተውና በምክረ-ሀሳቦች ተደግፈው ይቀርባሉ ተብሎ ይጠበቃል። ይህም የየዘርፎችን ሀገራዊና ሁሉን አቀፍ የ15 ዓመት የልማት ዕቅድ በማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ በማካተት የተጠቃለለ የረጅም ዘመን ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ለማዘጋጀት ያስችላል።

ከዚህ በተጨማሪ በትግበራ ሂደት ላይ የሚገኘውን እና የረጅም ዘመን ሀገራዊ የልማት ዕቅድ (በትግበራ ሂደት ላይ ያለ) የመጀመሪያ ምዕራፍ የሆነውን የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እና የዘላቂ ልማት ግቦችን በተለያዩ ደረጃዎች ግልፅነትንና ተጠያቂነትን ይበልጥ ማጠናከር እና ውጤታማና ስኬታማ በሆነ መንገድ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችል ሀገራዊ የዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ የፖሊሲ ማዕቀፍ ዝግጅት በመገባደድ ላይ ይገኛል። ይህ ሀገራዊ የዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ የፖሊሲ ማዕቀፍ ዝግጅት በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቅቆ በመንግስት እንደሚፀድቅና እንደ ሀገራዊ ፖሊሲ በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥሞ ተፈፃሚ እንደሚሆን ይጠበቃል። በዚህም መሠረት የፖሊሲ ማዕቀፉ በመንግስት ከፀደቀ በኋላ ውጤታማ በሆነ አግባብ በሥራ ላይ ለማዋል በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች በስትራቴጂክ እና በቴክኒካል ደረጃዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የአቅም ግንባታ ሰፊ ሥልጠናዎች እንደሚሠሩ ታሳቢ ተደርጓል። ይህም የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ እንደሚጠይቅ ታምኖበታል። በአጠቃላይ የዘላቂ ልማት ግቦችን በተሟላ ሁኔታ ተፈፃሚ ከማድረግ አኳያ በልማት ዕቅድ እና በአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ዙሪያ በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በተለይ በመንግስት ተቋማት የተቀናጀ፣ የተደራጀ እና ቀጣይነት ያላቸው የአቅም ግንባታ ሥራዎች እንደሚሠሩ ይጠበቃል። እነዚህ የአቅም ግንባታ ሥራዎች በአመለካከት፣ በተቋማዊ አሠራር፣ በአደረጃጀት እና በሰው ኃይል ዙሪያ የሚያተኩሩ ይሆናሉ።

# 11. ክትትል፣ ሪፖርትና ግምገማ

የዘላቂ ልማት ግቦች የትግበራ አፈፃፀም ክትትል በሥራ ላይ ባሉ አሠራሮች፣ አደረጃጀቶች እና የሰው ኃይል በመታገዝ በሀገር አቀፍ እና በክልሎች ደረጃ የሁለተኛው ሀገራዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እና ከዚሁ ዕቅድ ተመንዝረው የተዘጋጁ ክልላዊ ዕቅዶች የትግበራ አፈፃፀም ክትትል አካል በመሆን እየተከናወነ ያለ ሥራ ነው። የክትትል ሥራው በሀገር አቀፍ ደረጃ ሴክተሮችን ማዕከል በማድረግ የሚመለከተው የፌዴራል የሴክተር አስፈፃሚ አካል በትግበራው የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ እና በሴክተር-ሴክተር የሥራ ግንኙነት (Functional Relationship) እስከ ታችኛው የአስተዳደር ዕርከን በመዘለቅ የሚከናወን ሲሆን የክትትል ሂደቶቹ የግምገማው አካል ተደርገው ሊወሰዱ ይገባል። በሥራ ላይ ባሉ አሠራሮች እና የመረጃ ቋቶች መሠረት ሴክተሮችን ማዕከል ያደረጉ የአፈፃፀም ክትትል መነሻዎች (Baseline Data) እንዳሉ እና የዘላቂ ልማት ግቦችን አፈፃፀም ለመገምገም ሥራ ላይ እንደዋሉ በግምገማ ሪፖርቱ ዘርዘር ባለ ሁኔታ መታየት አለባቸው።

በሀገር አቀፍ ደረጃ የአፈፃፀም ክትትል መረጃዎች በየሴክተር አስፈፃሚ አካላት ተደራጅተው፣ ተተንትነውና በሪፖርት መልክ ተዘጋጅተው ለብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን እንደሚቀርቡና በዚህ መልክ ለኮሚሽን መ/ቤቱ የሚቀርቡ አፈፃፀም ክትትል ሪፖርቶች ከመረጃ ወጥነት፣ በሴክተሮች መካከል መኖር ከሚገባው ተመጋጋቢነት፣ ከተሟሉ መረጃዎች ወቅታዊነት እና ትኩረት ከሚሹ ሀገራዊ ጉዳዮች አንፃር ተተንትነውና ተገምግመው የተጠቃለለ ሀገራዊ የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሪፖርት ለመንግስት እንደሚቀርብ በግምገማ ሪፖርቱ ውስጥ ሊመለከት ይገባል። የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሪፖርቱን መንግስት ካፀደቀው በኋላ በክልሎች እና በፌዴራል ደረጃ በሚዘጋጁ የምክክር መድረኮች ባለድርሻ አካላት እንዲወያዩበትና ቀጣይ የትግበራ ሂደቶችን ሊያፋጥኑ የሚችሉ ጠቃሚ ግብዓቶች እንደሚሰባሰቡበት ሰፋ ባለ ሁኔታ በግምገማው መታየት አለበት።

በክልል ደረጃ የሚከናወኑ የዕቅድ አፈፃፀም ክትትል ሥራዎችም ተመሳሳይ ባህሪያት ያሏቸው ናቸው። ይህም የክልል ሴክተሮችን ማዕከል በማድረግ ከታችኛው እስከ ላይኛው የክልል የአስተዳደር ዕርከን ትስስርና ተመጋጋቢነት ባለው አግባብ የሚፈፀም ነው። የተጠቃለሉ የሴክተር ዕቅድ አፈፃፀም የክትትል ሪፖርቶች በየሚመለከታቸው የክልል/የከተማ አስተዳደር የሴክተር አስፈፃሚ አካላት ለየክልሎቹ የፕላን ተቋማት ይቀርባሉ። የፕላን ተቋማቱ የቀረቡላቸውን የተለያዩ የሴክተር ዕቅድ ትግበራ አፈፃፀም የክትትል ሪፖርቶች ከፍ ብሎ በሀገር አቀፍ ደረጃ በቀረበው አግባብ እና በየክልሎቹ ተጨባጭ ሁኔታ የአፈፃፀም ሪፖርቶች ተጠቃልለው ለክልሎች ካቢኔዎች እንዲቀርቡና እንዲፀድቁ ይደረጋል። የክልሎች የአፈፃፀም ሪፖርቶች በሀገር አቀፍ ከሚዘጋጀው ሪፖርት ጋር በጋራ የክልሎች የምክክር መድረኮች ተገምግመው በቀጣይ የዕቅድ ትግበራውን የሚያፋጥኑ ጠቃሚ አስተያየቶች በግብዓትነት ይወሰዳሉ። እነዚህ ሂደቶችም በክልሎች ግምገማዎች በግልፅ ሊቀመጡ ይገባል።

በሀገራችን እስካሁን ባለው አሠራር እና አደረጃጀት የዕቅድ አፈፃፀም ክትትል ሥራዎች የሚከናወኑት ሁለት ዋና ዋና የመረጃ ምንጮችን መሠረት በማድረግ ነው። እነዚህም አስተዳደራዊ መረጃዎች (70 በመቶ) እና የመስክ ናሙና ጥናት/የቆጠራ መረጃዎች (30 በመቶ) ናቸው። አስተዳደራዊ መረጃዎች በመንግስት ሴክተሮች አስፈፃሚ አካላት (የባለድርሻ አካላት በሚሳተፉባቸው ሴክተሮች የሚያመነጯቸውን መረጃዎች ይጨምራል) የሚመነጩ ሲሆን የመስክ ናሙና ጥናት እና የቆጠራ መረጃዎች በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የሚመነጩ ናቸው። ከዚህ አንፃር በሥራ ላይ ያለውን አሠራር እና አደረጃጀት በመከተል የዘላቂ ልማት ግቦችን አፈፃፀም ውጤታማና ስኬታማ በሆነ መንገድ ለመከታተል መከናወን ያለባቸው የአቅም ግንባታ ሥራዎች በዚህ አግባብ ሊታዩ እንደሚገባ በግምገማው በዝርዝር ሊፈተሽ ይገባል። ከዚህ አንፃር ሀገራዊ የክትትልና ግምገማ ሥርዓቱን ለማጠናከር እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን በግምገማው በግልፅ ማሳየት አስፈላጊ ነው።

የዘላቂ ልማት ግቦች የትግበራ አፈፃፀም ክትትል የሁለተኛው

የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የአፈፃፀም ክትትል አካል በመሆን በበጀት ዓመቱ ውስጥ በሂደቶች ላይ እና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሂደቶችን ጨምሮ በኢላማዎች (Targets) የአፈፃፀም ውጤቶች አመልካቾች ላይ በማተኮር በመከናወን ላይ ይገኛል። በዚህም መሠረት እ.ኤ.አ. በ2017 ዝርዝር የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ እንዲካሄድባቸው ከተመረጡ የዘላቂ ልማት ግቦች አፈፃፀም ግምገማ አንፃር አግባብ ያላቸው ሴክተሮችን የአፈፃፀም ውጤቶች በአመልካቾች በመታገዝ በግልፅ ለማስቀመጥ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የ2008 አፈፃፀም እና የ2009 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት አፈፃፀም ሪፖርቶች በግብዓትነት ተወስደዋል።

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የዕቅድ አፈፃፀም ክትትል ሥራዎች በአስተዳደራዊ መዛግብት በየጊዜው የሚያዙ እና ከናሙና ጥናቶች የሚገኙ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ በተለያዩ የመንግስት አስፈፃሚ አካላት የሚዘጋጁ የአፈፃፀም ሪፖርቶችን በግብዓትነት የሚወስዱ ናቸው። እነዚህ የክትትል ሥራዎች እንደ አስፈላጊነቱ በመስክ ምልከታ የሚታገዙ ናቸው። የአፈፃፀም ሪፖርቶች ሲዘጋጁ በትራንስፎርሜን ዕቅዱ የፖሊሲ ማትሪክስ የተቀመጡ አመልካቾች አፈፃፀም ከበጀት ዓመቱ ኢላማ እና ከመነሻ ዓመቱ አፈፃፀም ተነፃፅሮ ይተነተናል፣ ችግሮች ካሉም እንዲለዩ ይደረጋል። በዚህም በትንተና የተለዩ ችግሮች ካሉ የመፍትሄ እርምጃዎችን በመውሰድ የዕቅዱን ቀጣይ አፈፃፀም የሚያፋጥኑ ሥራዎች እንዲሠሩ ይደረጋል።

## 11.1.መረጃ፣ ስታቲስቲክስ እና አመልካቾች

መረጃ ለዕቅድ፣ ለአፈፃፀም ክትልና ግምገማ እንዲሁም ለውሳኔ አሰጣጥ ተኪ የሌለው ግብዓት ነው። በመሆኑም የተሟላ፣ ወቅታዊ እና ጥራት ያለው መረጃ የሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እና የዘላቂ ልማት ግቦችን አፈፃፀም ለመከታተል፣ ለመገምገምና በሚደረስባቸው ውጤቶች መሠረት የፖሊሲ እርምጃዎችን ለመውሰድ ወሳኝ ነው። በሥርዓት በሚመራ የልማት ሂደት ከፖሊሲ ቀረፃ እስከ ፕሮጀክት ዝግጅትና ትግበራ ጥራት ያለው ወቅታዊ መረጃ ወሳኝ መሆኑን አስቀድሞ የተረዳው የኢትዮጵያ መንግስት ሀገራዊ የስታቲስቲክስ ተቋማዊ አሠራር እና አደረጃጀት ዘርግቶ የመካከለኛ ዘመን የስታቲስቲክስ ልማት ብሔራዊ ስትራቴጂ በመቅረጽ ተፈፃሚ በማድረግ ላይ ይገኛል።

በዚህም መሠረት የማዕከላዊ ስታቲስክስ ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ በጥናት ላይ የተመሠረቱ መረጃዎችን የማመንጨትና የማሰራጨት ሀገራዊ ኃላፊነት ያላቸው የፌዴራል መንግስት ተቋማት ናቸው። የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የሀገሪቱን የልማት ፍላጎት መሠረት ያደረጉ የሶሽዮ-ኢኮኖሚ መረጃዎችን በናሙና ጥናት እና በሙሉ ቆጠራ በማመንጨት ለተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል። በተመሳሳይ የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ የጂኦ-ስፓሺያል መረጃዎችን በማመንጨት ለተጠቃሚዎች ያቀርባል። የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲና የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ የተቋቋሙባቸውን የህግ ማዕቀፎች መሠረት በማድረግ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ሲሆን የሚያመነጯቸው መረጃዎች ለሀገራዊ የልማት ዕቅድ ዝግጅትና የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ መሠረታዊ መነሻ እና ግብዓት በመሆናቸው ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን እንዲሆን በአዋጅ ተወስኗል። በመሆኑም ብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን ሀገራዊ የዕቅድ ዝግጅት እና የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ኃላፊነቱን ለመወጣት ትልቅ ሀገራዊ አቅም ተፈጥሮለታል።

ከዚህ አንፃር የዘላቂ ልማት ግቦች የ2017 የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ የመረጃ ግብዓቶች ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የናሙና ጥናትና ቆጠራ እንዲሁም ከተለያዩ የመንግስት የዘርፍ አስፈፃሚ መ/ቤቶች አስተዳደራዊ መረጃዎች የተወሰዱ ናቸው። መረጃዎቹም የስታቲስክስ ልማት ብሔራዊ ስትራቴጂውን መሠረት በማድረግ የዘላቂ ልማት ግቦችን በማስተሳሰር ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ የዋለውን የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የአፈፃፀም ሂደት ለመከታተል በዕቅዱ የፖሊሲ ማትሪክስ ተደራጅተው የተቀመጡ ቀጥተኛ እና ወካይ (Proxy) አመልካቾችን ተከትለው የመነጩ፣ የተተነተኑ እና የተገመገሙ ናቸው። በዚህም መሠረት መረጃዎቹ አግባብ ባለው ሁኔታ እየተነተኑ እና እየተገመገሙ የዋና ሪፖርቱ አካል የተደረጉ ሲሆን ዝርዝር መረጃዎች የዋናው ሪፖርት አባሪ ተደርገው ቀርበዋል።

## 11.2. የክትትል፣ ሪፖርትና ግምገማ ዘዴዎች

ኢትዮጵያ ያልተማከለ የአስተዳደር ሥርዓት የምትከተል ሀገር ብትሆንም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ህገ-መንግስት መግቢያ በግልፅ የተቀመጠውን አንድ የጋራ ኢኮኖሚ የመገንባት አስፈላጊነት ተግባራዊ ለማድረግ የፌዴራል መንግስት በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 51 ንዑስ አንቀፅ 2 በተደነገገው መሠረት የሀገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ዕቅድ ያወጣል፣ ያስፈፅማል። በዚህም መሠረት በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚመለከታቸውን አስተባብሮ በመምራት ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ለማዘጋጀት እና አፈፃፀሙን ለመከታተል ብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 281/2005 መሠረት ተቋቁሟል።

የብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን ቀጥታ ተጠሪነት ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ሲሆን ሥርዓቱን ተከትሎ የዕቅድ አዘገጃጀት እና አፈፃፀም መመሪያዎችን በማዘጋጀት ሥራ ላይ ያውላል፣ እያዋለም ይገኛል። በዚህም መሠረት የዘላቂ ልማት ግቦችን በማስተሳሰር የተዘጋጀው የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከታችኛው እስከ ላይኛው የመንግስት አስተዳደር ዕርከን በክፍላተ-ኢኮኖሚ የልማት ፕሮግራሞች (ለምሳሌ የትምህርት ዘርፍ የልማት ፕሮግራም፣ የጤና ዘርፍ የልማት ፕሮግራም፣ የመንገድ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም፣ የግብርና ዘርፍ ልማት ፕሮግራም፣ የውሀና ሳኒቴሽን ዘርፍ ልማት ፕሮግራም...ወዘተ) እና በማክሮ ዘርፍ የተደራጀ ነው። የዕቅዱ አፈፃፀም የክትትል፣ የሪፖርት እና የግምገማ መንገድም የክፍላተ-ኢኮኖሚ እና የማክሮ ተቋማዊ አደረጃጀቶችን የተከተለ ነው።

በዚህም መሠረት የዘላቂ ልማት ግቦችን በማስተሳሰር የተዘጋጀውን የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በማስፈፀም ሂደት በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ በክፍላተ-ኢኮኖሚ እና በማክሮ ደረጃ የተከናወኑ እና እየተከናወኑ ያሉ የልማት ሥራዎች አፈፃፀም የክትትል ሪፖርቶች የዕቅዱን አደረጃጀቶች ተከትለው ለብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን እንዲቀርቡ የሪፖርቶች ይዘቶችን እና የማቅረቢያ የጊዜ ገደብ ያካተተ ሰርኩላር ከሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜው ቢያንስ አንድ ወር ተኩል ቀደም ብሎ ለሁሉም የፌዴራል አስፈፃሚ አካላት በብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን ይተላለፋል። በዚህም መሠረት ከተለያዩ የፌዴራል የክፍላተ ኢኮኖሚ እና የማክሮ-ኢኮኖሚ አስፈፃሚ አካላት የአፈፃፀም ክትትል ሪፖርቶች ለብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን እንዲቀርቡ ይደረጋል።

ከፍ ብሎ በተገለፀው መንገድ ከተለያዩ የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካላት የሚቀርቡ የአፈፃፀም ሪፖርቶች በብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን የክፍላተ-ኢኮኖሚ፣ የማክሮ-ኢኮኖሚ እና የክትትልና ግምገማ የሥራ ክፍሎች በተቀናጀና በተደራጀ አግባብ ይገመገማሉ። ያልተሟሉ፣ የተጓደሉ፣ ወቅታዊ ያልተደረጉ እና የወጥነት ክፍተት ያለባቸው መረጃዎች ከሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላት ጋር በመነጋገር እንዲታረሙ እና እንዲሟሉ ይደረጋል። በዚህም መሠረት በማክሮ-ኢኮኖሚ፣ በክፍላተ-ኢኮኖሚ እና በባለብዙ ዘርፎች የአፈፃፀም ሪፖርቶች መካከል ትስስርና ተመጋጋቢነት ያለው እና እንዲሁም የተተነተና የተገመገመ አጠቃላይ ሀገራዊ የግምገማ ሪፖርት በብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን ተዘጋጅቶ ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ይቀርባል።

## 11.3. ተሞክሮዎች፣ ፈተናዎች እና መልካም አጋጣሚዎች

የዘላቂ ልማት ግቦችን በማስተሳሰር ተዘጋጅቶ በትግበራ ላይ የሚገኘውን የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በተቀመጡለት ግቦች እና ኢላማዎች መሠረት ተፈፃሚ ለማድረግ በሁሉም የሀገራችን አካባዎች በተደረጉና እየተደረጉ ባሉ የልማት እንቅስቃሴዎች ተሞክሮዎችን፣ ፈተናዎችንና መልካም አጋጣሚዎችን ለመለየት ተሞክሯል። ከእነዚህም መካከል ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

### 11.3.1. ተሞክሮዎች

ዜጎች በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካ እንቅስቃሴዎች እኩል ተሳታፊና ፍትሀዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣ መንግስት የሚሰጣቸውን መሠረታዊ አገልግሎቶች ለዜጎች በቅርብ ተደራሽ በማድረግ አንድ የጋራ ኢኮኖሚ ለመገንባት ያልተማከለ አስተዳደር መዘርጋቱ፣ የመንግስት ሀገራዊ

አጠቃላይና የሴክተር ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ድህነት ተኮር መሆናቸው፣ ሰፊ የሰው ጉልበትና መሬት የሚጠቀሙና ለኢኮኖሚ መሠረተ ልማት እና ለሰው ሀብት ልማት ቅድሚያ ትኩረት የሰጡ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ሥራ ላይ መዋላቸው፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ እና ብሔራዊ የአደጋ ክስተት ሥጋት ሥራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ተቀርፀው ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረጉ እና በመንግስት መሪነት እና አስተባባሪነት በከፍተኛ ሕዝባዊ ንቅናቄ በየደረጃው እየተከናወኑ ያሉ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የተፋሰስ ልማት ሥራዎች በተጨባጭ የሚታዩ ስኬታማ ውጤቶች እየተመዘገቡባቸው ነው። በመሆኑም የዘላቂ ልማት ግቦችን ተፈፃሚ ከማድረግ አንፃር በተሞክሮነት ሊወሰዱ የሚገባቸው ናቸው።

በተጨማሪም በግብርና እና በጤና ዘርፎች እየተካሄዱ ያሉ የግብርና ኤክስቴንሽን እና የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሞች በርካታ ስኬቶች የተመዘገቡባቸው ናቸው። እንዲሁም በኢንዱስትሪ ዘርፍ እየተከናወኑ ያሉ ሰፊ የሰው ጉልበት እና የአንድ መስኮት አገልግሎት የሚጠቀሙ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የፓርክና የክላስተር አደረጃጀቶች የተጀመረውን የትራንስፎርሜሽን ጉዞና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ከማፋጠን አኳያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው በመሆኑ በተሞክሮነት የሚወሰዱ ናቸው። ባጠቃላይ የመንግስት የፖሊሲ አቅጣጫዎች፣ ተቋማዊ አደረጃጀቶች እና የአፈፃፀም እርምጃዎች ድህነትን ከነሁሉም መገለጫዎቹ ለማጥፋት፣ ዕኩልነትን ለማረጋገጥና ብልፅግናን ለማስፋፋት የማያሻሙ መንገዶች በመሆናቸው በተሞክሮነት የሚወሰዱ ናቸው።

## 11.3.2. ፈተናዎች

የዘላቂ ልማት ግቦችን በተቀመጠላቸው የጊዜ ሠሌዳ መሠረት አሟልቶ ተፈፃሚ ከማድረግ አንፃር በተደራጁ፣ በተቀናጁ እና ተመጋጋቢ በሆኑ ሀገራዊ የልማት ጥረቶች እና ዓለም አቀፍ አጋርነት እንደሚቀረፉ ከሚጠበቁ ፈታኝ ሁኔታዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በ2008 የበጀት ዓመት በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች የተከሰተው አስከፊ ድርቅ 10.2 ሚሊዮን ህዝብ ተረጂ እንዲሆን ማድረጉ እና ድርቁን ለመቀልበስ በተወሰዱ የተደራጁ እና የተቀናጁ ርምጃዎች ለልማት ሊውል ይችል የነበረ ውስን የሀገር ሀብት መሻማቱ እንዲሁም በ2009 የበጀት ዓመት በተወሰኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተከሰተው ድርቅ 5.2 ሚሊዮን የሚሆን ህዝብ ተረጂ እንዲሆን ማድረጉ፣ የልማት ሀብት መሻማቱ እና በእንስሳት ሀብት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ መሆኑ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ትልቅ ፈተና ነው።
2. በ2008 የበጀት ዓመት የዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ መቀዛቀዝን ተከትሎ የዓለም የሸቀጦች ዋጋ በመቀነሱ፣ የሸቀጦች መዳረሻ ሀገሮች ፍላጎትም በመዳከሙ እና የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ መሠረት ጠባብ፣ መጠኑ አነስተኛ እና በአብዛኛው በግብርና ምርቶች ላይ ጥገኛ በመሆኑ ከሸቀጦች የወጪ ንግድ የተገኘው የውጭ ምንዛሬ ገቢ ቅናሽ አሳይቷል። ይህም የንግድ ሚዛኑ ጉድለት እየሰፋ እንዲሄድ አድርጎታል። በዚህም በ2007 የነበረው 13.4 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የንግድ ሚዛን ጉድለት በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 13.9 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንዲሰፋ አደርጎታል። በመሆኑም የዓለም የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሌላው ፈተና ነበር።
3. ከአመለካከት እና ከማስፈፀም አቅም ጋር የተያያዙ የኪራይ ሰብሳቢነት እና የመልካም አስተዳደር ችግሮች ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አሁንም ትልቅ ፈተናዎች ናቸው። የዘላቂ ልማት ግቦችን በማስተሳሰር የተዘጋጀውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ግቦች እና ኢላማዎች በተለያዩ ደረጃዎች ከማስፈፀምና ከመፈፀም አንፃር የፈፃሚ አካላትን አስተሳሳብ ቀይሮ ከማነሳሳት፣ ከማደራጀት፣ አሰልጥኖም ከማስማራት አኳያ አሁንም በርካታ ውስንነቶች ይታያሉ። የኪራይ ሰብሳቢነት እና የመልካም አስተዳደር ችግሮች የኢኮኖሚና ማህበራዊ አገልግሎቶች በታቀደውና በተጠበቀው ደረጃ እንዳይፋጠኑ አሉታዊ ተፅዕኖ እየፈጠሩ ነው። ከዚህ አንፃር የአመለካከት ችግሮች እና የማስፈፀም አቅም ውስንነቶች አሁንም ሀገራችን ያልተሻገረቻቸው ፈተናዎች ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪ የኃይማኖት አክራሪነት እና ዓለም አቀፍ ሽብርተኝነት የልማት አጋርነትን በማጠናከር የልማት ሀብትን ከማሰባሰብ አኳያ በዕርዳታ፣ በብድር፣ በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል የሚል ስጋት አለ።

### 11.3.3. መልካም አጋጣሚዎች

የዘላቂ ልማት ግቦችን በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ተፈፃሚ ከማድረግ አንፃር ፈታኝ ሁኔታዎች ቢኖሩም በአንፃሩ በርካታ መልካም አጋጣሚዎች እንዳሉ በመገንዘብ እነዚህን መልካም አጋጣሚዎች አሟጦ መጠቀም ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ይሆናል። በተጨማሪም ፈታኝ ሁኔታዎችን ወደ መልካም አጋጣሚዎች መቀየር እና የዘላቂ ልማት ግቦችን አፈፃፀም ማፋጠን በትኩረት ተይዞ እንዲሰራበት ይደረጋል። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የዘላቂ ልማት ግቦችን ተፈፃሚ ለማድረግ በርካታ መልካም አጋጣሚዎች እንዳሉ ከፍ ብሎ በተሞክሮነት የተቀመጡትን የመንግስት የፖሊሲ፣ የአደረጃጀት እና የአፈፃፀም እርምጃዎች በጥሞና መመልከት ተገቢ ይሆናል። ከዚህ አንፃር የመንግስት ከፍተኛ የፖለቲካ ቁርጠኝነት እና በሀገራችን ያለውን ከፍተኛ ወጣት የሥራ ኃይል እንዲሁም ከአየር ንብረት ለውጥ አንፃር የዓለም አቀፍ የልማት አጋርነትን ማጠናከር እና ያሉ ዕድሎችን አሟጦ መጠቀም የዘላቂ ልማት ግቦችን ተፈፃሚ ከማድረግ አንፃር በትኩረት ተይዘው ሊፈፀሙ የሚገባቸው ናቸው።

# 12. ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ ምድረ ቀደምት እና ብዝሀነትን እያስተናገደች ያለች ሀገር ናት። የተለያዩ መንግስታዊ ሥርዓቶች የተፈራረቁባት፤ በቋንቋ፣ በኃይማኖት፣ በባህል እና በመልክዓ ምድር አቀማመጥ የተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ተከባብረው፣ ተፈቃቅደውና ተቻችለው በአንድ ላይ የሚኖሩባት እና የፌዴራል አደረጃጀትና ያልተማከለ የአስተዳደር ሥርዓት የምትከተል ሀገር ናት። የሀገሪቱ ጠቅላላ የቆዳ ስፋት 1.1 ሚሊዮን ካሬ ኪሎ ሜትር ሲሆን በማዕከላዊ ስታቲስክስ ኤጀንሲ የትንበያ መረጃ (Projection) መሠረት የህዝብ ብዛቷ በ2009 የበጀት ዓመት 92.304 ሚሊዮን ደርሷል።

የኢትዮጵያ መንግስት እ.ኤ.አ. ከ2000 እስከ 2015 በሥራ ላይ የዋለውን የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች አጀንዳ ከሀገራዊ የልማት ማዕቀፎች ጋር በማስተሳሰር እና የልማት ኃይሎችን አስተባብሮ በመምራት ባከናወናቸው የተቀናጁና የተደራጁ የልማት ሥራዎች ስኬታማ ውጤቶች አስመዝግቧል። ከልማት ሂደቱ ከተገኙ ተሞክሮዎችም ተምሯል። የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች አጠቃላይ አፈፃፀም በሀገር አቀፍ ደረጃ ገምግሞ የግምገማ ግኝቶችን ለዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 ዝግጅት ግብዓት እንዲሆኑ ድርሻውን ተወጥቷል።

ባለፉት 25 ዓመታት የኢትዮጵያ መንግስት ካለፈባቸው የልማት ሂደቶች የዳበረ ልምድ በመውሰድና መጪውን በመረጃዎች ላይ ተመሥርቶ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የ2030 የዘላቂ ልማት አጀንዳን ተቀብሎ አጽቋል። በዚህም መሠረት የዘላቂ ልማት ግቦችን በባለቤትነት በመውሰድና የሀገራችን የልማት ማዕቀፍ አካል በማድረግ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፀድቆ ወደ ትግበራ ገብቷል። እ.ኤ.አ. ኦገስት 2016 ዓ.ም. ከተባበሩት መንግስታት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ካውንስል (ECOSOC) በቀረበለት ጥያቄ መሠረት የዘላቂ ልማት ግቦች የ2017 የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ አካሂዷል።

በመንግስት መሪነትና አስተባባሪነት በተካሄደው የዘላቂ ልማት ግቦች የ2017 የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ ሁለት ዘዴዎች በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል። እነዚህም ኦፊሴላዊ ከሆኑ ምንጮች የዘላቂ ልማት ግቦች አፈፃፀምን የሚመለከቱ መረጃዎችን (ከአስተዳደራዊ መዛግብት እና ከናሙና ጥናቶች/ከቆጠራ ምንጮች) እና ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በተወካዮቻቸው አማካኝነት ያሳተፉ ምክክሮችን በማካሄድ ለግምገማ ሪፖርት ዝግጅት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን በማሰባሰብ ነው። በዚህም መሠረት በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በፌዴራል ደረጃ 20 የሚሆኑ የምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት እና ሰፊ ውይይቶች በማካሄድ ለግምገማ ሪፖርት ዝግጅቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በሀገር አቀፍና በክልሎች/በከተማ አስተዳደሮች ደረጃ የተካሄዱ የዘላቂ ልማት ግቦች የ2017 የፈቃደኝነት ግምገማዎች ተመሳሳይ የመረጃ ምንጮችን እንዲጠቀሙ በመደረጋቸው በሀገር አቀፍ እና በክልሎች/በከተማ አስተዳደሮች ደረጃ የተዘጋጁ የዘላቂ ልማት ግቦች የ2017 የፈቃደኝነት ግምገማ ሪፖርቶች ተመጋጋቢ እንዲሆኑ አስችሏል።

የግምገማ ሂደቶችን በሚመለከት ለዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 ዝግጅት ኢትዮጵያ ያበረከተችውን አስተዋፅኦ በግልፅ የማስቀመጥ፣ የዘላቂ ልማት ግቦችን በባለቤትነት በመያዝ ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የማስተሳሰር፣ በዕቅዱ ላይ በየደረጃው ሁሉም ባለድርሻ አካላት ግንዛቤ እንዲይዙና ለተፈፃሚነቱ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ማስቻል፣ የዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 በሁሉም ባለድርሻ አካላት ተፈፃሚ እንዲሆን የልማት ኃይሎችን አስተባብሮ የመምራት እና የዘላቂ ልማት ግቦችን ተፈፃሚ ከማድረግ አኳያ በሀገር አቀፍ ደረጃ አንድ ዕቅድ እና አንድ በጀት ብቻ በሥራ ላይ እየዋለ መሆኑን ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ግንዛቤ የማስጨበጥ ሂደቶች በግምገማው ተዳስሰዋል።

የዘላቂ ልማት ግቦችን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ልማት ማዕቀፍ አካል ከማድረግ አንፃር የዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 በኢትዮጵያ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እንደ አንድ መነሻ ተወስዷል። በዚህም መሠረት ሁሉም የዘላቂ ልማት ግቦች ከትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ 10 የትኩረት መስኮች (10 Priority Areas) ጋር እንዲተሳሰሩ ተደርጓል። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ተፈፃሚ ሊደረጉ የሚችሉ የዘላቂ ልማት ግቦች ኢላማዎችም በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ የማክሮኢኮኖሚ፣ የኢኮኖሚ

ልማት፣ የመሠረተ-ልማት፣ የማህበራዊ ልማት የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እና የባለብዙ ዘርፎች ልማት ኢላማዎች ጋር እንዲተሳሰሩ ተደርጓል። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ተፈፃሚ ሊደረጉ የማይችሉ የዘላቂ ልማት ግቦች ኢላማዎች እና አመልካቾችን በጥናት የመለየት ሥራ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል። የዘላቂ ልማት ግቦችን ተፈፃሚ ከማድረግ አኳያ በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች የሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማስፈፀም ቀደም ብለው ሥራ ላይ የነበሩ እና አሁንም በሥራ ላይ ያሉ ተቋማዊ አሠራሮች እና አደረጃጀቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ተደርገዋል።

ፖሊሲዎችና አስቻይ ሁኔታዎችን በሚመለከት የዘላቂ ልማት ግቦችን ተፈፃሚ ለማድረግ በኢትዮጵያ ምቹ ሁኔታዎች እንዳሉ ግምገማው ያመለክታል። የኢትዮጵያ መንግስት የዘላቂ ልማት ግቦችን ተፈፃሚ ለማድረግ ከፍተኛ የፖለቲካ ቁርጠኝነት አለው። መንግስት የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር ማስተሳሰሩ፣ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፀድቆ ለተፈፃሚነቱ የህግ አስገዳጅነት እንዲኖረው በማድረግ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ወደ ትግበራ እንዲገባ ማድረጉ ለፖለቲካ ቁርጠኝነቱ ጉልህ ማሳያ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያ መንግስት ዋነኛ የልማት አጀንዳ ድህነትን ማጥፋት ነው። በዚህም መሠረት ሁሉም የመንግስት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ድህነትን ከነሁሉም መገለጫዎቹ በማፋት ላይ ያተኮሩ ናቸው። በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግስት በየዓመቱ ከጠቅላላ ሀገራዊ ወጪው ውስጥ 70 በመቶ የሚሆነውን ድህነትን ለመቅረፍ ትልቅ አስተዋፅኦ ለሚያደርጉ ቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸው የማህበራዊ ልማትና መሠረተ ልማት ፕሮግራሞች ማለትም ለትምህርት፣ ለጤና፣ ለመንገድ፣ ለውሀና ሳኒቴሽን እና ለግብርናና የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞች እያዋለ ይገኛል።

ኢትዮጵያ ያልተማከለ የአስተዳደር ሥርዓት የምትከተል ሀገር ናት። ይህም በርቀት ከሚገኘው ማዕከላዊ መንግሥት (የፌዴራል መንግስት) ይልቅ ለህዝብ ቅርበት ላላቸው የአካባቢ አስተዳደር ዕርከኖች በቂ ሥልጣን በመስጠት የሕዝቡን ፍላጎት በየደረጃው በተሻለ ሁኔታ በማወቅ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ለማሳተፍ፣ የመንግስት አገልግሎት አቅርቦትን በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግና የሕዝብን ፍላጎት ለማሟላት ወሳኝ ነው። በመሆኑም ህዝቡን በየደረጃው በልማቱ ዕኩል ተሳታፊና ፍትሀዊ ተጠቃሚ ለማድረግ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ልማትን የማፋጠንና እና ድህነትን ከነሁሉም ገፅታዎች የማጥፋት ሥራዎች በተቀናጀና በተደራጀ አግባብ በመከናወን ላይ ይገኛሉ። የዘላቂ ልማት ግቦችን ከሀገራዊ የልማት ማዕቀፍ ጋር አስተሳስሮ ከማስፈፀምና ከመፈፀም አኳያም የጎላ ፋይዳ አለው።

የመንግስት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች በተቀናጀና በተደራጀ አግባብ ሥራ ላይ በዋሉባቸው ባለፉት አሥራ-አምስት ዓመታት ዜጎችን በየደረጃው ተጠቃሚ ያደረጉ ስኬታማ የልማት ውጤቶች ተመዝግበዋል። እነዚህ የልማት ውጤቶች ሥራ አጥነትንና ድህነትን በመቀነስ ረገድ ቁልፍ ሚና ተጫውቷል። በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በየአምስት ዓመቱ በተካሄዱ የቤተሰብ ገቢና የፍጆታ ወጪ እንዲሁም የኑሮ ደህንነት እና የዲሞግራፊና ጤና ጥናቶች መሠረት የኢትዮጵያ የድህነት መጣኔ በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል። በመሠረተ-ልማት፣ በትምህርት እና በጤና ከፍተኛ ስኬቶች ተመዝግበዋል። በዚህም መሠረት ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. በ2030 ድህነትን ከነሁሉም መገለጫዎቹ ለማጥፋት የተቀመጠውን ዓለም አቀፍ ግብ ታሳካለች።

በአለፉት አሥራ አምስት ዓመታት ኢትዮጵያ ፈጣን፣ ቀጣይና መሠረተ ሰፊ የኢኮኖሚ ዕድገት አስመዝግባለች። በዚህም በርካታ የሥራ ዕድሎች ተፈጥረዋል። በ2008 የበጀት ዓመትም ኢኮኖሚው በአማካይ በ8 በመቶ አድጓል። በበጀት ዓመቱ የተመዘገበው ዕድገት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የአየር ንብረት ለውጥ ባስከተለው ከፍተኛ ድርቅ በተፈተነበትና የዓለም ኢኮኖሚ መቀዛቀዝ ባሳየበት ወቅት በመሆኑ ፈጣን የሚባል ነው። ከዚህ በተጨማሪ የኢኮኖሚ ዕድገቱ በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሀገራት እ.ኤ.አ. በ2030 ምቹ ሥራና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ በየዓመቱ ማስመዝገብ ካለባቸው ቢያንስ የ7 በመቶ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ሲነፃፀር ከፍ ያለ ነው።

ድህነትን ከማጥፋት አንፃር ድህነትንና ሥራ አጥነትን ከመቅረፍ አንፃር እስከ 2007 የበጀት ዓመት መጨረሻ የተከናወኑ የልማት ሥራዎች ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል።

ይሁን እንጂ አሁንም በኢትዮጵያ ያለው የድህነት መጣኔ እና ሥራ አጥነት በጣም ሰፊ ነው። በተለይም የሴቶችና የወጣቶች ሥራ አጥነት በጣም ከፍተኛ ነው። ይህም በቀጣይ ፈጣንና ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ መሠረተ-ልማት፣ ማህበራዊ ልማት እና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በማስቀጠል ድህነትንና ሥራ አጥነትን በፍጥነት ለመቀነስ ከፍተኛ ርብርብ የሚጠይቅ ነው። ከዚህ አንፃር ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ እና የዘላቂ ልማት ግቦችን በማስተሳሰር የተዘጋጀውና በመንግስት ፀድቆ በትግበራ ላይ በሚገኘው ሁለተኛው የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ድህነትን ለመቀነስ ለሴቶችና ለወጣቶች ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷል። ባለፉት ዓመታት ዜጎችን ፍትሀዊ ተጠቃሚ ያደረገ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ተመዝግቧል። የኢኮኖሚ ዕድገቱ ሠፊ የሥራ ዕድል የፈጠረ ሲሆን የዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢም እንዲጨምር አድርጓል። ለምሳሌ የነፍስ ወከፍ ገቢ በጊዜው የገበያ ዋጋ በ2002 ከነበረበት 373 የአሜሪካን ዶላር በ2008 የበጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 794 የአሜሪካን ዶላር አድጓል።

በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የቤተሰብ ገቢና የፍጆታ ወጪ ጥናት መሠረት አጠቃላይ ድህነት እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1992 ከነበረበት 44.2 በመቶ በ1997 ወደ 38.7 በመቶ፣ በ2003 ወደ 29.6 በመቶ እና በ2007 በተደረገ ትንተና ወደ 23.4 እንደሚወርድ ተገምቷል። እንዲሁም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት (በ2012 መጨረሻ) ወደ 16.7 በመቶ እንደሚቀንስ ትንበያዎች ያሳያሉ። የተጀመረውን ፈጣንና መሠረተ-ሰፊ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ መሠረተ-ልማት፣ ማህበራዊ ልማት እና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ አጠናክሮ በማስቀጠል ዜጎችን በልማቱ እኩል ተሳታፊና ፍትሀዊ ተጠቃሚ በማድረግ ድህነትን እ.ኤ.አ. በ2030 ለማጥፋት የተቀናጁ ሥራዎች በመሥራት ላይ ናቸው።

ረሀብንከማጥፋትአንፃርመንግስትየምግብዋስትናንበተለያዩ ደረጃዎች ለማረጋገጥ እና ሀገራችንን ከምግብ ተመፅዋችነት ለማላቀቅ የግብርናን ምርታማነት በሚጠበቀው ደረጃ በማሳደግ ወደ አምራች ኢንዱስትሪ የሚደረገውን መዋቅራዊ ሽግግር ማፋጠን በወሳኝነት ይዞ እየሠራ ይገኛል። በዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 የተቀመጠውን ረሀብን የማጥፋት ግብ ለማሳካት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለግብርና ምርታማነት፣ ለአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እንዲሁም ለከተማ የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ልዩ ትኩረት ተሰጥቷል። በ2008 የበጀት ዓመት በሀገሪቱ ተከስቶ የነበረው አስከፊ ድርቅ በተለይ በግብርናው ዘርፍ የልማት ዕንቅስቃሴ ላይ ባሳደረው ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ ምክንያት ዋና ዋና የምግብ ሰብሎች ምርት በ2007 ከነበረበት 270.3 ሚሊዮን ኩንታል በ2008 የበጀት ዓመት ወደ 266.8 ሚሊዮን ኩንታል ቀንሷል። በሌላ በኩል በ2008 የበጀት ዓመት የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ የሚያስችሉ የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ሥራዎች በተደራጁና በተቀናጁ የህዝብ ንቅናቄዎች ተከናውነዋል። በዚህም መሠረት 1,028 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የተለያዩ የስነ-አካላዊና ስነ-ህይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች ተከናውነዋል። በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በ2008 እና በ2009 በሀገሪቱ የተከሰተው ድርቅ በተለይ በግብርናው ዘርፍ ልማት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አስከትሏል። በ2008 የበጀት ዓመት 10.2 ሚሊዮን ህዘብ እንዲሁም በ2009 የበጀት ዓመት 5.2 ሚሊዮን ህዘብ በድርቁ ተጠቂ ሆኗል። ሆኖም በደረሰው አስከፊ ድርቅ ምክንያት የአንድም ሰው ህይወት ሳይጠፋ መንግስት በአብዛኛው በውስጥ አቅም ህዝቡን አስተባብሮ በመምራት ድርቁ ሊያስከትል ይችል የነበረውን ሰብዓዊ ቀውስ ለመቋቋም ችሏል።

ጤናማ ህይወትና ደህንነትን ከማረጋገጥ አንፃር ባለፉት ዓመታት መንግስት የልማት ኃይሎችን በየደረጃው አስተባብሮ በመምራት የጤናውን ዘርፍ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ፕሮግራም ከሌሎች አግባብነት ካላቸው የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር በማመጋገብ በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ ተፈፃሚ ሲያደርግ ቆይቷል። በዚህም የጤና ተቋማትን በማስፋፋት፣ አስፈላጊውን የሰው ኃይል በማሠልጠንና ወደ ሥራ በማሰማራት፣ የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን ማስፋፋት እና የአገልግሎት ሽፋኑን 98 በመቶ ማድረስ ተችሏል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይ የእናቶችና የህፃናት ጤና ከፍተኛ ማሻሻል አሳይቷል። በአጠቃላይ የተላላፊ በሽታዎች ክስተት እና ስርጭትም በከፍተኛ ደረጃ ተገትቷል። ይህም ኢኮኖሚው የሚፈልገውን ጤናማ የሥራ ኃይል ምርታማነት

በማሻሻል የኢኮኖሚውን ፈጣን ዕድገት ለማስቀጠል እና እ.ኤ.አ. በ2030 ድህነትን ከነሁሉም መገለጫዎቹ ለማጥፋት የጎላ አስተዋፅኦ አለው።

የሥርዓተ-ፆታ ዕኩልነትን ከማረጋገጥ አንፃር መንግስት የሴቶችንና የወጣት ሴት ልጆችን ፍትሐዊ ተጠቃሚነትና እኩልነት ለማረጋገጥ የሴቶች ፖሊሲን፣ የሴቶች የልማት ፓኬጅ፣ የወጣቶች ፖሊሲና የወጣቶች የልማት ፓኬጅን ቀርፆ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። የወጣቶች ፖሊሲ ለሴቶች የተለየ ትኩረት በመስጠት ወጣቾች በዲሞክራሲና በመልካም አስተዳደር ጉዳዮች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣ እንዲደራጁና መብታቸውን እንዲያስከብሩ ማስቻልና በትምህርትና በተለያዩ ሙያዊ ስልጠናዎች አቅማቸውን መገንባት ዋነኛ በመሆኑ ፖሊሲውን ተፈፃሚ ለማድረግ ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ይገኛል። የሴቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ከማሳደግ አንጻር ባለፉት ዓመታት በርካታ የልማት ሥራዎች ተከናውነዋል። ከነዚህም መካከል በገጠር የሚገኙ ሴቶችን በተለያዩ የሥራ ዘርፎች እንዲሰማሩ መደገፍና የመሬት ባለቤት እንዲሆኑ ማድረግ ዋነኛው ነው። በገጠር መሬት ዋነኛ የኢኮኖሚ መሰረት እንደመሆኑ በ2008 በጀት አመት 276.1 ሺህ ሴቶች በጋራ ከባለቤቶቻቸው ጋር እና 61.7 ሺህ ሴቶች በግል እንዲሁም በ2009 ስድስት ወራት ደግሞ ለ432,011 ሴቶች በጋራ እና 71,169 ሴቶች በግል የሁለተኛ ደረጃ የመሬት ተጠቃሚነት ማረጋገጫ ደብተር እንዲያገኙ ተደርጓል።

የመሠረተ-ልማት ግንባታን እና የኢንዱስትሪ ፈጠራን ከማረጋገጥ አንፃር በመንገድ፣ በባቡር፣ በኢነርጂ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና በሌሎች መሠረተ-ልማቶች የተቀናጁ ሥራዎች በመካሄድ ላይ ናቸው። በዚህም መሠረት የመንገድ መሠረተ-ልማት ግንባታን በተመለከተ ሁሉንም የሀገሪቱ የገጠር ቀበሌዎች ክረምት ከበጋ ከሚያገለግሉ ዋና መንገዶች ጋር ለማገናኘት መንግስት ከፍተኛ የማስፈፀሚያ ሀብት በመመደብ የልማት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል። በዚህም መሠረት ክረምት ከበጋ የሚያስኬድ የመንገድ ርዝመት በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 110,414 ኪ.ሜ. በ2008 በጀት ዓመት ወደ 113,067 ኪ.ሜ. ማሳደግ የተቻለ ሲሆን በአማካይ ክረምት ከበጋ የሚያስኬዱ መንገዶች ላይ ለመድረስ የሚወስደው ጊዜ በ2008 የበጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 1.6 ሰዓት ዝቅ ብሏል።

የዕቃና የሰው ትራንስፖርት ወጪ ቆጣቢና የአየር ብክለትን የማያስከትል የትራንስፖርት አገልግሎት ለማስፋፈትና የቀጠና ትስስርን ለማጠናከር በተያዘው አቅጣጫ መሠረት ኢትዮጵያ የባቡር መሠረተ ልማት ግንባታን በማፋጠን ላይ ትገኛለች። በዚህም መሠረት የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ምዕራፍ አንድ ፕሮጀክት ሥራው ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ በ2008 የበጀት ዓመት አገልግሎት በመስጠት የጀመረ ሲሆን የሀገር አቀፍ የባቡር መሠረት ልማት ግንባታም በተያዘለት ዕቅድ መሠረት እየተከናወነ ይገኛል።

የኢነርጂ መሠረተ ልማትን በተመለከተ የታዳሽ ሀይል ማመንጫ (ከውሃ፣ ከጂኦተርማል፣ ከንፋስ እና ከፀሐይ ኃይል) ፕሮጀክቶች ግንባታ ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ተደርጓል። በአፍሪካ የመጀመሪያ የሆነውና በአዲስ አበባ ከተማ እየተገነባ ያለው ከደረቅ ቆሻሻ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ግንባታ ወደ መጠናቀቂያ ምዕራፍ ደርሷል። የኤሌክትሪክ ኃሐሓሃይልየይል ማመንጨት ሀገራዊ አቅም በ2008 በጀት ዓመት 4,269.5 ሜ.ዋ. ደርሷል። በመገንባት ላይ ካሉ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች መካከል በግዙፍነቱ በአፍሪካ የመጀመሪያውና በዓለም 8ኛ የሆነው በዓባይ ወንዝ ላይ እየተገነባ ያለው የታላቁ ህዳሴ የኃይል ማመንጫ ግድብ ፕሮጀክት አፈፃፀምም በ2009 ወደ 57 በመቶ የደረሰ ሲሆን የግድቡ ሥራ በ24 ሰዓት የማያቋርጥ የሥራ እንቅስቃሴ በሶስት ፈረቃዎች እየተከናወነ ይገኛል።

የዲጂታል መሰረተ ልማትን በተመለከተ በቴሌኮሙኒኬሽን ንዑስ ዘርፍ የሞባይል ስልክ፣ የብሮድባንድ ኢንተርኔትና ዳታ፣ የናሮው ባንድ ኢንተርኔትና ዳታ...ወዘተ አገልግሎቶችን ተደራሽ ለማድረግ የሚሠሩ ሥራዎች ተጠንክረው ቀጥለዋል። በዚህም መሠረት የስኩልኔት አገልግሎቶች በመስፋፋት ላይ ናቸው። የገጠሩን ህብረተሰብ የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለማድረግ በያዘው ሰፊ ዕቅድ መሠረት ከ1,600 በላይ የገጠር ሁለገብ የኮሙዩኒኬሽን ማዕከላት እንዲቋቋሙ ተደርጓል። ዓለም አቀፍ ትብብርን ከማሳደግ አኳያ ኢትዮጵያ አባል በሆነችባቸው ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ የዘርፉ ማህበራት የትብብርና የድጋፍ ሥራዎች ላይ ንቁ ተሳትፎ በመደረግ ላይ ነው። ዓለም አቀፍ የሳተላይት ግንኙነት

እየተስፋፋ ሲሆን ከሮሚንግ ፓርትነሮች፣ ከኢንተርኔት የድምጽ አጋሮች እና ከየኢነተርኔት የግንኙነት አጋሮች ጋር ሥራዎች በጋራ እየተሠሩ ይገኛሉ።

የአየር ትራንስፖርትን በተመለከተ የበረራ ደህንነትና ጸጥታ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማስቻል የአየር ትራንስፖርት አገልግሎትን ተቋማዊ አቅም የመገንባት፣ ብቃትናተወዳዳሪነትያለውየአየርትራንስፖርትአገልግሎትን የመስጠት እና የአየር ትራንስፖርት አገልግሎትን ተደራሽነት የማስፋት ሥራዎች በትኩረት ተይዘው በመከናወን ላይ ናቸው። በዚህም የገበያ ማስፋፊያና ማጠናከሪያ ሥራዎችን በመሥራት እና የአገልግሎት አድማሱን በማስፋት በዓለም አቀፍ የቀጥታ በረራ መዳረሻዎችን 98 እንዲሁም የሀገር ውስጥ መዳረሻዎችን 22 ማድረስ ተችሏል። በየ10 ሺህ በረራዎች የሚኖረውን የአደጋ አጋጣሚ ከዓለም አቀፍ የአቬዬሽን ድርጅት ኦዲት ስታንዳርድ አንጻር ተፈጻሚ በማድረግ የአደጋ መጠን በአዲስ አበባ ቦሌ ዓለማቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በቀን ካለው አማካይ 220 በረራዎች የአደጋ አጋጣሚ መጠን 0.505 ደርሷል። ይህም የዓለም አቀፍ የአቬዬሽን ድርጅት ኦዲት ስታንዳርድን ያሟላ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

የተቀናጀ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎትን በሚመለከት የዘርፉን አገልግሎት ለማሳደግ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ይገኛል። በዚህም መሠረት የሰው እና የዕቃ ማጓጓዣ የትራንስፖርት አገልግሎት እያደገ መጥቷል። ይሁን እንጂ በትራፊክ አደጋ ምክንያት በየ10,000 ተሽከርካሪዎች የሚደርሰውን የሞት አደጋን ትርጉም ባለው ሁኔታ መቀነስ አልተቻለም። በ2008 የበጀት ዓመት መጨረሻ በትራፊክ አደጋ የደረሰ የሞት አደጋ መጠን 63/10000 እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህም በኢትዮጵያ እየታየ ያለው የትራፊክ አደጋ በጣም የከፋ እና አደጋውን ለመቀልበስ ከፍተኛ ትኩረት እና ጥረት የሚጠይቅ መሆኑን ያመለክታል።

የመጠጥ ውሀና መስኖ መሠረተ ልማትን በተመለከተ አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን ለማሳደግና የተሻሻለ የፍሳሽ አወጋገድ ስርዓት ለመፍጠር፣ የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት አገልግሎትን ደረጃ በማሻሻል ተደራሽነቱን ለማስፋት፣ የውሃ ሀብታችን መጠንና ጥራት በማወቅ በኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተጽእኖ በመለየት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እንዲደግፍ ለማስቻል፣ በብሔራዊ ደረጃ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ መካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ እርሻዎችን ለማልማትና ለማስፋፋት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ይገኛል።

በኢንዱስትሪ ልማት መስክ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን በምርትና ምርታማነት፣ በኤክስፖርት ድርሻ፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር እና ለዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ቀዳሚና የመሪነት ሥፍራ እንዲይዝ ለማስቻል እየተሠራ ይገኛል። የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ዓላማን ለማሳካት ጠንካራ የሰው ኃብት በመገንባት ለልማታዊ ባለሀብቱ ምቹ ሁኔታ የመፍጠር፣ ከዘላቂ የአካባቢ ልማት ጋር የተጣጣመ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪን የመገንባት የማህበራዊ ልማትን የሚደግፍ፣ የአካባቢ ተጽዕኖ የማያስከትል አረንጓዴ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዕድገትን ለማረጋገጥ የተደራጁና የተቀናጁ ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው። ከዚህ አንፃር ከመሠረተ ልማቶች ጋር የተሳሰረ እና የአንድ መስኮት አገልግሎት ማስገኘት የሚያስችል የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት የፓርክ እና የክላስተር አደረጃጀቶችን በመከተል በስፋት እየተከናወነ ይገኛል።

የውሀ ሥነ-ምህዳርን ለዘላቂ ልማት ከመጠበቅ አንፃር አፈርንና ውሀን ከመሸርሸር አደጋ የሚጠብቁ በተለይ ከተፋሰስ ልማት ጋር የተያያዙ በርካታ የውሃና የአፈር ጥበቃ ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው። ለገፀ ምድር እና ለከርሰ ምድር ውሀ ዕጥረት ዋነኛው ምክንያት የመሬት መራቆትና የአፈር መሸርሸር ነው። ይህንንም ለመከላከል የተቀናጁና የተደራጁ የስነ-አካላዊና ስነ-ህይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው። በአጠቃላይ የከርሰ ምድር እና የገፀምድር ውሀን የሚያበለፅጉ፣ ብዝሀ ህይወትን የሚጠብቁ፣ አፈርንና ውሀን ከመሸርሸር አደጋ የሚታደጉ፣ እየተገነቡ ያሉ ትላልቅ የኢነርጂ መሠረተ-ልማት ግድቦችን እና ሀይቆችን ከደለል የሚከላከሉ፣ ለግድቦችና ለሀይቆች ዓመቱን ሙሉ አስተማማኝ የውሀ ፍሰት እንዲኖር የሚያስችሉ እና የወራጅ ወንዞች፣ የግድቦችና የሀይቆች የውሀ አካላትን ከግብርና የኬሚካል ግብዓት ቅሪቶች ብክለት የሚከላከሉ የተቀናጁና የተደራጁ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የተፋሰስ ልማት ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው።

በአጠቃላይ በአለፈው አንድ ዓመት ተኩል የዘላቂ ልማት

ግቦችን በማስተሳሰር የተዘጋጀውን የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተፈፃሚ በማድረግ ሂደት ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በሀገሪቱ የተከሰተ አስከፊ ድርቅ፣ ድንበር ዘለል የጤና ችግሮችን ከጎረቤት ሀገራት ጋር በጋራ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተቀናጀ ሥርዓት አለመኖር፣ የሴቶችን ዕኩልነት ከማረጋገጥ እና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ከማስወገድ አኳያ የአመለካከት ችግሮች ዕንቅፋት መሆናቸው፣ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም እንዲሁም የመረጃ ውስንነት ፈተናዎች እንደነበሩ በግምገማው መለየት ተችሏል።

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ መንግስት በሚከተለው የልማት አቅጣጫ ድህነት ተኮር ፖሊሲዎች ሥራ ላይ መዋላቸው፣ ያልተማከለ አስተዳደር በመከተል ለታችኛው የመንግስት አስተዳደር ዕርከን ከፍተኛ ሥልጣን በመስጠት የመንግስት አገልግሎቶች ለህዝቡ በቅርብ ተደራሽ እንዲሆኑ ማስቻሉ፣ በጋራ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ መግባባት በመፍጠር ለአንድ የጋራ የልማት ዓላማ ህዝቡን በተደራጀና በተቀናጀ ሁኔታ ማንቀሳቀስ መቻል፣ ግብርና መር ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ እና የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ድህነትን ከመቀነስና ረሀብን ከማጥፋት አኳያ ያስገኛቸው ውጤቶች፣ የተጠናከረ የግብርና እና የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም፣ የሴቶች የጤና ልማት ሠራዊት እና የጤና የልማት ቡድን መደራጀት፣ የሴቶች ፖሊሲና የልማት ፓኬጅ፣ ተቋማዊ አሠራሮችና አደረጃጀቶች፣ ሴቶችን በማህበር ማደራጀት፣ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮችን በሁሉም የልማት ዘርፎች ማካተት፣ በመሠረተ-ልማት ላይ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጡ የመንግስት ፖሊሲዎች (በተለይ ለኢነርጂ መሠረተ ልማት)፣ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እና የተፋሰስ ልማት በተቀናጀና በተደራጀ የህዝብ ንቅናቄ መሠረታዊ ለውጥ እያመጣ መሆኑን በግምገማው የተለዩ መልካም ተሞክሮዎች ናቸው።

# 13. የስታቲስቲክ አባሪዎች

በዚህ የግምገማ ሪፖርት ክፍል 10 ስለመረጃ፣ ስታቲስቲክስና አመልካቾች ተገልጿል። የዘላቂ ልማት ግቦች የ2017 የፈቃደኝነት ብሔራዊ ግምገማ የመረጃ ግብዓቶች ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የናሙና ጥናትና ቆጠራ እንዲሁም ከተለያዩ የመንግስት የዘርፍ አስፈፃሚ መ/ቤቶች አስተዳደራዊ መዛግብት መወሰዳቸውም ተብራርቷል።

ከዚህ አንፃር የስታቲስክስ ልማት ብሔራዊ ስትራቴጂውን መሠረት በማድረግ የዘላቂ ልማት ግቦችን በማስተሳሰር ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ የዋለውን የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የአፈፃፀም ሂደት ለመከታተል በዕቅዱ የፖሊሲ ማትሪክስ ተደራጅተው የተቀመጡ ቀጥተኛ እና ወካይ (Proxy) አመልካቾችን ተከትለው የመነጩ እና የግምገማው አካል የሆኑ እና ከማዕከላዊ ስታቲስክስ ኤጀንሲ እና ከተለያዩ የፌዴራል የክፍላተ ኢኮኖሚ አስፈፃሚ መ/ ቤቶች በተሰበሰቡ አፊሴላዊ መረጃዎች ላይ በመመስረት የተዘጋጁ አመልካቾች በአባሪ 13.1 እና 13.2 በተከታታይ ቀርበዋል።

## 13.1.የተመረጡ የዘላቂ ልማት ግቦች አፈፃፀም ማሳያዎች

| የዘላቂ ልማት ግብ | አመልካች | የአፈጻጸም መነሻ (2007 በጀት ዓመት) | የ2008 በጀት ዓመት አፈጻጸም |
|---|---|---|---|
| ግብ 4 ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም | | | |
| | የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቅበላ በመቶኛ | 39 | 49.6 |
| | የወንዶች ቅበላ በመቶኛ | 40 | 50.8 |
| | የሴቶች ቅበላ በመቶኛ | 38 | 48.3 |
| | የአንደኛ ደረጃ /1-8/ ንጥር ተሳትፎ በመቶኛ | 96.9 | 97.12 |
| | የወንዶች ንጥር ተሳትፎ በመቶኛ | 100 | 100 |
| | የሴቶች ንጥር ተሳትፎ በመቶኛ | 93.2 | 93.6 |
| | የ1ኛ ደረጃ ትምህርት (1-8) የሥርዓተ-ጾታ ተሳትፎ ልዩነት | 0.93 | 0.91 |
| | የሁለተኛ ደረጃ 1ኛ እርከን (9-10) ጥቅል ተሳትፎ በመቶኛ | 39.8 | 44.8 |
| | የወንዶች ጥቅል ተሳትፎ በመቶኛ | 41.3 | 46.2 |
| | የሴቶች ጥቅል ተሳትፎ በመቶኛ | 38.4 | 43.4 |
| | የሁለተኛ ደረጃ 2ኛ እርከን (11-12) ጥቅል ተሳትፎ በመቶኛ | 10.6 | 12.6 |
| | የወንዶች ጥቅል ተሳትፎ በመቶኛ | 11.3 | 13.4 |
| | የሴቶች ጥቅል ተሳትፎ በመቶኛ | 9.9 | 11.6 |
| | የጎልማሶች ትምህርት ተሳትፎ (በሚሊዮን ቁጥር) | 6.0 | 6.9 |
| | በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ጠቅላላ የሰልጣኞች ቅበላ በቁጥር | 352144 | 304139 |
| | በከፍተኛ ትምህርት የቅድመ ምረቃ መርሀ ግብር ጥቅል ተሳትፎ በቁጥር* | 729028 | 778766 |
| | በቅድመ ምረቃ ፕሮግራም የሴቶች ጥቅል ተሳትፎ ድርሻ በመቶኛ | 32 | 34 |
| | በከፍተኛ ትምህርት የቅድመ ምረቃ መርሀ ግብር ተመራቂዎች ብዛት | 107567 | 130714 |
| | በቅድመ ምረቃ ፕሮግራም የወንድ ተመራቂዎች ድርሻ በመቶኛ | 71 | 66 |
| | በቅድመ ምረቃ ፕሮግራም የሴት ተመራቂዎች ድርሻ በመቶኛ | 29 | 34 |
| | በድህረ ምረቃ ፕሮግራም ቅበላ /ሁለተኛ ዲግሪ/በቁጥር | 37152 | 52611 |
| | በድህረ ምረቃ ፕሮግራም የሴቶች ቅበላ በመቶኛ | 25 | 25 |
| | በድህረ ምረቃ ፕሮግራም የወንዶች ቅበላ በመቶኛ | 75 | 75 |
| | በድህረ ምረቃ ፕሮግራም ቅበላ /ሦስተኛ ዲግሪ/ በቁጥር | 3135 | 2725 |
| | በድህረ ምረቃ ፕሮግራም ቅበላ /ሁለተኛ ዲግሪ/ ተመራቂዎች ብዛት | 10203 | 8588 |
| | የሴት ተመራቂዎች ብዛት | 1608 | 1481 |
| | የወንድ ተመራቂዎች ብዛት | 8595 | 7107 |
| | በድህረ ምረቃ ፕሮግራም ቅበላ /ሦስተኛ ዲግሪ/ ተመራቂዎች ብዛት | 485 | 263 |
| | የወንድ ተመራቂዎች ብዛት | 424 | 239 |
| | የሴት ተመራቂዎች ብዛት | 61 | 24 |
| **ግብ 4 ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም** | | | |
| | የሰለጠኑ የመጀመሪያ ደረጃ /1-4/ መምህራን ድርሻ በመቶኛ | 71.37 | 73 |
| | የሰለጠኑ የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን /5-8/ መምህራን ድርሻ በመቶኛ | 71.37 | 94 |
| | የሰለጠኑ የሁለተኛ ደረጃ /9-12/ መምህራን ድርሻ በመቶኛ | 87.3 | 96 |

| የዘላቂ ልማት ግብ | አመልካች | የአፈጻጸም መነሻ (2007 በጀት ዓመት) | የ2008 በጀት ዓመት አፈጻጸም |
|---|---|---|---|
| ግብ 6. የንፅህ ውሃና የንፅህና አገልግሎት፣ | | | |
| | የገጠር መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን በዕትዕ-2 ስታንዳርድ አገልግሎት ደረጃ (በተሻሻሉ የውሀ ተቋማት በጥቅል) በመቶኛ | 59 | 63.1 |
| | የከተማ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን በዕትዕ-2 ስታንዳርድ አገልግሎት ደረጃ (በቧንቧ ውሃ) በመቶኛ | 51 | 52.5 |
| | አጠቃላይ (ከተማና ገጠር) መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን በዕትዕ-2 ስታንዳርድ አገልግሎት ደረጃ (በተሻሻሉ የውሀ ተቋማት በጥቅል) በመቶኛ | 58 | 61 |
| | የማይሰሩ የገጠር መጠጥ ውሃ ተቋማት ሽፋን በመቶኛ | 11.2 | 11 |

## 13.2.የተመረጡ የዘላቂ ልማት ግቦች አፈፃፀም ማሳያዎች…የቀጠለ

| የዘላቂ ልማት ግብ | አመልካች | የአፈጻጸም መነሻ (2007 በጀት ዓመት) | የ2008 በጀት ዓመት አፈጻጸም |
|---|---|---|---|
| ግብ 7 አቅምን ያገናዘበ ታዳሽ ኢነርጂ፣ | | | |
| | የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም በሜጋ ዋት | 2399.5 | 4269.5 |
| | ከውሃ የሚመነጭ የኤሌክትሪክ ኃይል በሜ.ዋ | 3734 | |
| | ከንፋስ የሚመነጭ የኤሌክትሪክ ኃይልበሜ.ዋ | 324 | |
| | ከጂኦተርማል የሚመነጭ የኤሌክትሪክ ኃይልሜ.ዋ | 7 | |
| | ከስኳር (ኢታኖል) የሚመነጭ የኤሌክትሪክ ኃይል በሜ.ዋ | 26 | |
| | መጠባበቂያ/ጋስ ተርባይን/ከነዳጅ/ በሜ.ዋ | 89 | |
| | ከኤሌክትሪክ ኃይል የተገኘ ገቢ በሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር | 131 | |
| | የደንበኞችን ብዛት በሚሊዮን ቁጥር | 2.31 | 2.49 |
| | የነፍስ ወከፍ ፍጆታ ዕድገት ኪሎ ዋት ሰዓት በሰው በዓመት | 86 | |
| | የኤሌክትሪክ አገልግሎት ሽፋንን በመቶኛ | 60 | 56 |
| | አጠቃላይ የኃይል ብክነት በመቶኛ | 23 | |
| | የኤሌክትሪክና ውሃ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ በመቶኛ | 0.7 | 0.6 |

## 13.3.ዝርዝር ግምገማ የተካሄደባቸው የዘላቂ ልማት ግቦች አፈፃፀም

| ግቦች | የዘላቂ ልማት ግቦችና አመልካቾች | የ2007 አፈጻጸም (መነሻ ዓመት) | የ2008 አፈጻጸም | ዕቅድ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
| ግብ 1 | ድህነትን ማጥፋት[1] | | | | | | |
| | ከአጠቃላይ ሀገራዊ የድህነት መስመር በታች የሚኖረው ሕዝብ ብዛት በመቶኛ | 23.40 | | | | | 16.70 |

| ግቦች | የዘላቂ ልማት ግቦችና አመልካቾች | የ2007 አፈጻጸም (መነሻ ዓመት) | የ2008 አፈጻጸም | ዕቅድ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
| | የድህነት ተኮር ዘርፍ ወጪ ከጠቅላላ የመንግስት ወጪ ያለው ድርሻ በመቶኛ | 66 | 67 | 72 | 72 | 71 | 68.0 |
| | የመንግስት የመሠረታዊ አገልግሎት ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በመቶኛ (ጤና፣ትምህርት፣መንግድ፣ ውሃ፣ ግብርና እና ተፈጥሮ ሀብት) | 12.30 | 12.90 | 13.50 | 14.10 | 14.80 | 15.40 |
| | ሴቶችን፣ድሆችን፣ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን ተጠቃሚ ለሚያደርጉ ተቋማት በመንግስት የተመደበ የመደበኛና የካፒታል መጠን( ከጠቅላላ የሀገር ውሰጥ ምርት ያለው ድርሻ በመቶኛ) | 17.3 | 18.4 | 19.30 | 20.20 | 21.40 | 22.60 |
| | በሴፍቲ ኔት የማህበራዊ ዋስትና ድጋፍ ተጠቃሚ ሕዝብ ብዛት በሚሊዮን (50 % ሴቶች) | 1.20 | 1.54 | 0.81 | 0.90 | 0.98 | 1.01 |
| | የቁስ ድጋፍ ተደረገላቸው አካል ጉዳተኞች ብዛት (የአካላዊ ተሃድሶ አገልግሎት ያገኙ አካል ጉዳተኞች ብዛት በቁጥር*) በሺህ | 236.19 | 78.74 | 70.00 | 75.00 | 80.00 | 85.00 |
| | የሁለተኛ ደረጃ የገጠር መሬት የይዞታ ማረጋረጫ ያገኙ ተጠቃሚዎች ብዛት በሚ/ን ቁጥር | 0.33 | 0.33 | 1.40 | 1.60 | 1.80 | 1.30 |
| | አባወራ በሚሊዮን ቁጥር | 0.26 | 0.27 | 1.12 | 1.28 | 1.44 | 1.04 |
| | እማወራ በሚሊዮን ቁጥር | 0.07 | 0.06 | 0.28 | 0.32 | 0.36 | 0.26 |
| | የተዘጋጀ የአደጋ መከላከል ስተራቴጂ | ተዘጋጅቷል | ተዘጋጅቷል | ተዘጋጅቷል | ተዘጋጅቷል | ተዘጋጅቷል | ተዘጋጅቷል |
| **ግብ 2** | **ረሀብን ማጥፋት 2** | | | | | | |
| | የዋና ዋና ምግብ ሰብሎች ምርት መጠን በሚ/ን ኩንታል | 270.08 | 267 | 319 | 346 | 375 | 406 |
| | የዋና ዋና ምግብ ሰብሎች ምርታማነት ኩንታል/ ሄክታር | 21.05 | 19 | 25 | 27 | 29 | 31 |

| ግቦች | የዘላቂ ልማት ግቦችና አመልካቾች | የ2007 አፈጻጸም (መነሻ ዓመት) | የ2008 አፈጻጸም | ዕቅድ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
| | አጠቃላይ የኤክስቴንሽን ምክር አገልግሎት ያገኙ አርሶ አደር ብዛት በሺ ቁጥር | 13950 | 15,735 | 16,406 | 17,038 | 17,692 | 18,237 |
| | የኤክስቴንሽን ምክር አገልግሎት ያገኙ አርሶ አደር ብዛት በሺ ቁጥር | 14,014 | 14,549 | 15,105 | 15,685 | 16,287 | 16,776 |
| | የኤክስቴንሽን ምክር አገልግሎት ያገኙ አባዎራ አርሶ አደሮች ብዛት በሺ ቁጥር | 8,343 | 8,594 | 8,852 | 9,118 | 9,392 | 9,674 |
| | የኤክስቴንሽን ምክር አገልግሎት ያገኙ እማወራ አርሶ አደሮች ብዛት በሺ ቁጥር | 4,253 | 4,466 | 4,689 | 4,924 | 5,170 | 5,325 |
| | የኤክስቴንሽን ምክር አገልግሎት ያገኙ ወጣት አርሶ አደሮች ብዛት በሺህ ቁጥር | 1,418 | 1,489 | 1,564 | 1,643 | 1,725 | 1,777 |
| | የኤክስቴንሽን ምክር አገልግሎት ያገኙ አርብቶ አደሮች ብዛት በሺ ቁጥር | 690 | 718 | 755 | 794 | 826 | 858 |
| | የኤክስቴንሽን ምክር አገልግሎት ያገኙ አባወራ አርብቶ አደሮች ብዛት በሺ ቁጥር | 414 | 427 | 449 | 472 | 487 | 502 |
| | የኤክስቴንሽን ምክር አገልግሎት ያገኙ እማወራ አርብቶ አደሮች ብዛት በሺ ቁጥር | 207 | 218 | 229 | 241 | 254 | 267 |
| | የኤክስቴንሽን ምክር አገልግሎት ያገኙ ወጣት አርብቶ አደሮች ብዛት በሺህ ቁጥር | 69 | 73 | 77 | 81 | 85 | 89 |
| | የኤክስቴንሽን ምክር አገልግሎት ያገኙ ከፊል አርብቶ አደሮች ብዛት በሺ ቁጥር | 450 | 420 | 487 | 507 | 527 | 547 |
| | ጥቅም ላይ የዋለ ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ በሜ/ቶን | 1,025,231 | 752,282 | 1,355,868 | 1,559,248 | 1,793,135 | 2,062,106 |
| | ጥቅም ላይ የዋለ ምርጥ ዘር በሺህ ኩንታል | 1,874 | 2,617 | 2,795 | 3,052 | 3,296 | 3,560 |
| | የተለያዩ የፊዚካል የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች የተካሄደባቸው የማህበረሰብ ተፋሰሶች በሺህ ሄክታር | 20170 | 1,062 | 1,168 | 1,284 | 1,412 | 2,134 |
| | በስነ ህይወታዊ ዘዴዎች የተሸፈኑ የማህበረሰብ ተፋሰሶች በዓመት ያገለሉት የሙቀት አማቂ ጋዝ መጠን ($CO_2e$) በሚሊዮን ሜትሪክ ቶን | - | 5 | 6 | 6 | 7 | 8 |

## 13.4.ዝርዝር ግምገማ የተካሄደባቸው የዘላቂ ልማት ግቦች አፈፃፀም...የቀጠለ

| ግቦች | የዘላቂ ልማት ግቦችና አመልካቾች | የ2007 አፈጻጸም (መነሻ ዓመት) | የ2008 አፈጻጸም | ዕቅድ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
| | በማህበረሰብ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ ፕሮግራም የለማ መሬት በሚሊዮን ሄክታር | 12.162 | | | | | 41 |
| | በመለስተኛ ዘመናዊ የመስኖ ልማት የለማ መሬት መጠን በሚሊዮን ሄክታር | 2.35 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 |
| | የተመረተ የስጋ ምርት መጠን (ከከብት፣ በግ፣ ፍየል፣ ግመል፣ ዶሮ) በሺህ ቶን | 1,321 | 1,990 | 1,652 | 1805 | 1966 | 2103 |
| | የተመረተ የወተት (ላም፤ ግመል፤ ፍየል) ምርት ብዛት በሚ/ን ሊትር 5 | 5,304 | 4,467 | 5,938 | 6610 | 7051 | 9418 |
| **ግብ 3** | **ጤናማ ህይወትና ደህንነት [3]** | | | | | | |
| | የእናቶች ሞት ምጣኔ ከ 100000 | 420 | 412 | | | | 199 |
| | በሰለጠነ የጤና ባለሙያ የወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ሽፋን በመቶኛ | 60 | 72.7 | 72 | 78 | 84 | 90 |
| | ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት ሞት መጣኔ ከ1000 | 64 | 67 | | | | 30 |
| | የጨቅላ ህፃናት ሞት መጣኔ ከ1000 | 28 | 29 | | | | 10 |
| | ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት መቀንጨር በመቶኛ | 40 | 38.4 | | | | 26 |
| | ከ5 ዓመት በታች የሆኑ የህፃናት መቀጨጭ በመቶኛ | 9 | 9.9 | | | | 4.9 |
| | በኤች አይ ቪ ቫይረስ አዲስ የሚያዙ ሰዎች መጠን በ1000 | 0.03 | 0.03 | | | | 0.01 |
| | የሁለም አይነት የቲቢ በሽታ ልየታ መጠንን በመቶኛ | 61 | 61.3 | 81 | 83 | 85 | 87 |
| | የቲቢ ህክምና የማጠናቀቅ መጠን በመቶኛ | 92 | 92 | | | | 95 |
| | የወባ በሽታ ክስተት በየ1000 ሰው | 21 | 22 | | | | 12 |
| | በሄፓታይትስ ቢ አዲስ የመያዝ ዕድል በ100000 | 21.63 | 23.2 | | | | |
| | ትኩረት ከሚሹ የቆላ በሽታዎች ህክምና የሚያስፈልጋቸው የሰዎች ብዛት በሚሊዮን ቁጥር | 75 | 66.6 | | | | 14.9 |
| | በልብ በሽታ፣በካንሰር፣ በስኳርና በመተንፈሻ አካላት በሽታዎች የሚከሰት የሞት መጣኔ በመቶኛ | 476 | 287 | | | | |
| | በራስ ማጥፋት የሚከሰት የሞት መጣኔ | | 7 | | | | |
| | በመንገድ ትራፊክ አደጋ ምክንያት የሚከሰት የሞት መጣኔ ከ10000 | 60 | 63 | | | | 27 |
| | የዘመናዊ የወሊድ መከላከያ ዘዴ ፍላጎታቸው የተሟላላቸው እናቶች በመቶኛ | 40.4 | 35.3 | | | | 50 |
| | አፍላ ወጣቶች የመውለድ መጠን በ1000 | | 12 | | | | |
| | የወሳኝ የሆኑ ጤና አገልግሎቶች ሽፋን በመቶኛ | 96 | 98 | | | | 100 |
| | የጤና መድን ሽፋን ያላቸው የህዝብ ብዛት በሽኛ | 72 | 125 | | | | |
| | በተበከለ ዉሃ፣ የአከባቢ ንፅህና መጓደልና የጤና አጠባበቅ እጠረት ምክንያት የሚከሰት የሞት ምጣኔ | | 80 | | | | |

| ግቦች | የዘላቂ ልማት ግቦችና አመልካቾች | የ2007 አፈጻጸም (መነሻ ዓመት) | የ2008 አፈጻጸም | ዕቅድ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
| | ባልተጠበቀ ወይም በድንገት መመረዝ ምክንያት የሚከሰት የሞት ምጣኔ | | 29 | | | | |
| | ለህክምና ጥናትና ለመሰረታዊ የጤና ዘርፍ የሚመደብ ጠቅላላ የተጣራ አፊሻል የልማት ድጋፍ(ODA) | | | | | | |
| | የጤና ባለሙያ በ1,000 ሕዝብ | | 0.84 | 1.2 | 1.3 | 1.5 | 1.6 |
| | የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ተግባራዊ ያደረጉ ቀበሌዎች በመቶኛ | 92 | 93 | | | | 100 |

## 13.5.ዝርዝር ግምገማ የተካሄደባቸው የዘላቂ ልማት ግቦች አፈፃፀም...የቀጠለ

| ግቦች | የዘላቂ ልማት ግቦችና አመልካቾች | የ2007 አፈጻጸም (መነሻ ዓመት) | የ2008 አፈጻጸም | ዕቅድ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
| **ግብ 5** | **የሥርዓተ-ፆታ ዕኩልነት 4** | | | | | | |
| | ሙሉ በሙሉ እየተተገበሩ ያሉ የሴቶች ፖሊሲና የሴቶች የዕድገት ፓኬጅ፣ የወጣቶች ፖሊሲ እና የወጣቶች ዕድገት ፓኬጅ | የሴቶች ፖሊሲና ፓኬጅ ተቀርጸው እየተተገበሩ ይገኛሉ | | | | | |
| | ሙሉ በሙሉ እየተተገበሩ ያሉ ብሄራዊና የዘርፍ የልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች፣ አዋጆች ለምሳሌ የትምህርት የመጤና ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና የቤተሰብ ህግ | ፖሊሲና ህጎች ወጥተው እየተተገበሩ ይገኛሉ | | | | | |
| | በተለያዩ ሙያዎች ሥልጠና ያገኙ ሴቶች ብዛት በሚሊዮን | 1.13 | 1.89 | 2.40 | 2.88 | 3.37 | 3.87 |
| | በተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶች ብዛት በሚሊዮን | 2.97 | 2.35 | 3.66 | 4.98 | 6.29 | 7.60 |
| | በልማት፣ በመልካም አስተዳደርና በዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ የተሳተፉ ሴቶች ብዛት በሚሊዮን | 4.47 | | | | | |
| | የሴቶች ጉዳይን ተቋማዊ ያደረጉ ተቋማት/ድርጅቶች ብዛት በቁጥር | 8 | 69 | 19 | 20 | 21 | 22 |
| | በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሴት ተማሪዎች የምክር አገልግሎት የሚሰጡ መዋቅሮች ብዛት በቁጥር | 31 | 111 | 119 | 127 | 135 | 143 |

| ግቦች | የዘላቂ ልማት ግቦችና አመልካቾች | የ2007 አፈጻጸም (መነሻ ዓመት) | የ2008 አፈጻጸም | ዕቅድ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
| | የተገነቡና የተጠናከሩ ሆስቴል /አዳሪ ት/ቤት/ ብዛት በቁጥር | 10 | 16 | 24 | 26 | 28 | 30 |
| | በተወከዮች ም/ቤት የሴቶች ድርሻ በመቶኛ | 38.8 | 38.8 | | | | 50 |
| | በፌዴራል አስፈፃሚ አካላት የፖለቲካ ተሿሚ ሴቶች ውሳኔ ሰጭነት ድርሻ በመቶኛ | 9.2 | | 34 | 36 | 38 | 40 |
| | የሴቶችን የስነ-ተዋልዶ ጤና መረጃና ትምህርት ተደራሽነት ለማረጋገጥ የወጡ ህጎችና ደንቦች | የአሠራር ሥልቶች ተዘርግተው እየተተገበሩ ይገኛሉ | | | | | |
| | የመሬት ተጠቃሚነት መብት ሰርተፊኬት ያገኙ ሴቶች ብዛት በቁጥር | 8,647,118 | 9,492,772 | 12,086,907 | 14,681,042 | 17,275,177 | 19,869,312 |
| | የሴቶችን ዕኩል የመሬት ባለቤትነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ስራ ላይ የዋለ ህግ | የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በሕገመንግስቱ ከመደንገጉም በተጨማሪ የሴቶች ፖሊሲና የልማት ፓኬጅ ወጥቶ በመተግበር ላይ ይገኛል | | | | | |
| | ለሴቶች እኩልነትና የማብቃት ተግባራት የተበጀተ በጀትን ስራ ላይ መዋሉን ለመከታተል የተዘረጋ አሰራር | የአሠራር ሥርዓቱ ተዘርግቷል | | | | | |
| **ግብ 9** | **መሠረተ-ልማት ግንባታና የኢንዱስትሪ ፈጠራ [5]** | | | | | | |
| | ክረምት ከበጋ ከሚያስኬዱ መንገዶች ከ5 ኪ.ሜ በላይ ርቀው የሚገኙ የገጠር ነዋሪዎች መጣኔ በመቶኛ | 36.6 | 35.8 | | | | 13.5 |
| | የመንገደኛ መቀመጫ አቅርቦት ቁጥር በበረራ ርቀት በቢሊዮን ኪ.ሜ | 32 | 39.9 | | | | 68 |
| | የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ተጨማሪ ዕሴት ዕድገት በመቶኛ | 3.8 | 2.5 | 21.3 | 22.60 | 23.00 | 23.50 |
| | የመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ምርት ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት ያላቸው የተጨማሪ ዕሴት ድርሻ በመቶኛ | 3.8 | 4.4 | 4.4 | 4.8 | 5.3 | 5.9 |

## 13.6.ዝርዝር ግምገማ የተካሄደባቸው የዘላቂ ልማት ግቦች አፈፃፀም...የቀጠለ

| ግቦች | የዘላቂ ልማት ግቦችነ አመልካቾች | የ2007 አፈጻጸም (መነሻ ዓመት) | የ2008 አፈጻጸም | ዕቅድ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
| | ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ከአጠቃላይ አገር ውስጥ ምርት ያላቸው የተጨማሪ ዕሴት ድርሻ በመቶኛ | 1.1 | 1 | 1.3 | 1.4 | 1.6 | 1.8 |
| | ከአጠቃላይ የሥራ ቅጥር ውስጥ በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የተቀጠሩ ሠራተኞች ደርሻ በመቶኛ | 13.6 | | | | | |
| | የማኑፋክቸሪንግ ተጨማሪ ዕሴት ዕድገት በመቶኛ | 15.8 | 18.4 | | | | 21.9 |
| | የመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ተጨማሪ ዕሴት ዕድገት በመቶኛ | 23.1 | 22.9 | 21.3 | 21.8 | 22.6 | 23.4 |
| | የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ አንቀሳቃሾች ቁጥር በሺህ | | | | | | |
| | ለልማት ምርምር የዋለ ወጪ ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ | | | | | | |
| | በአገሪቷ ውስጥ የሚገኙ የሙሉ ጊዜ ተመራማሪዎች ቁጥር በሚሊዮን | 0.11 | | | | | 0.22 |
| | ጠቅላላ ለመሰረተ ልማት ግንባታ የተገኘ አለም አቀፍ ድጋፍና ሌሎች የገንዘብ ፍሰቶች ከአጠቃላዩ የካፒታል ወጪዎች ያላቸው ድርሻ መጣኔ | | | | | | |
| | የሞባይል አገልግሎት ስርፀት/penetration/ | 43.9 | 49 | 68.2 | 79.4 | 90 | 100 |
| | የሞባይል ስልክ ደንበኞች ብዛት (በሺህ) | 40,000 | 45,963 | 65,465 | 78,197 | 90,930 | 103,662 |
| | የአዲስ አበባ ምዕራፍ አንድ ቀላል ባቡር ግንባታ የ34 ኪ.ሜ ግንባታ አፈጻጸም በመቶኛ | 80 | 100 | | | | |
| | አዲስ አበባ-ሰበታ- መኢሶ-ደወንሌ የባቡር መሠረተ ልማት ግንባታ አፈጻጸም በመቶኛ | 86.5 | 99.2 | | | | |
| **ግብ 14** | **የውሀ ሥነ ምህዳርን ለዘላቂ ልማት መጠበቅ** [6] | | | | | | |
| | የዓሳ ምርት ተጨማሪ ዕሴት ከአጠቃላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በመቶኛ | 0.1 | 0.1 | | | | |
| | የተሻሻሉ አነስተኛና መካከለኛ የወተት ማምረቻዎች በቁጥር | 57,629 | | | | | |
| | የተሻሻሉ አነስተኛና መካከለኛ የከብቶች መመገቢያ በቁጥር | 30,278 | | | | | |
| | የተመረተ የዓሳምርት ብዛት በቶን | | 48386 | 55158. | | | |
| | በዋናዋና ሀይቆች የጋራ ተጠቃሚነትን ያማከለ ተሳትፏዊ ዓሳ ሀብት የክትትልና የቁጥጥርስርዓት (Fishery Co-management) መዘርጋት በቁጥር | | | 8 | | | |
| **ግብ 17** | **ዓለም አቀፋዊ ትብብር ለዘላቂ ልማት** [7] | | | | | | |

| ግቦች | የዘላቂ ልማት ግቦችነ አመልካቾች | የ2007 አፈጻጸም (መነሻ ዓመት) | የ2008 አፈጻጸም | ዕቅድ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
| | ጠቅላላ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በመቶኛ | 15.4 | 16 | 16.4 | 17.4 | 18.4 | 19.7 |
| | የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ በመቶኛ | 12.7 | 12.5 | 14 | 15.2 | 15.9 | 17.2 |
| | የውጭ ርዳታ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ደርሻ በመቶኛ | 1 | 0.9 | 0.8 | 0.7 | 0.6 | 0.5 |
| | የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትት፣ እርርዳታና ሳውዝ - ሳውዝ ትብብር ከጠቅላላ የመንግስት በጀት ያለው ድርሻ በመቶኛ | 21 | 24 | | | | |
| | የበጀት ጉድለት ከጠቅላላ ምርት አንጻር በመቶኛ | 1.9 | 2.4 | 2.8 | 2.8 | 3 | 3 |
| | የውጭ ብድር ክፍያ ለጠቅላላ የወጭ ንግድ ያለው ደርሻ በመቶኛ | 16.13 | 16.70 | | | | |
| | ልማትን ለማሳለጥ ለአካባቢ ምቹና ተስማሚ የሆኑቴክኖሎጂ ሽግግር ለማድረግ የጸደቀ ጠቅላላ የገንዘብ መጠን | | | | | | |

## 13.7.ዝርዝር ግምገማ የተካሄደባቸው የዘላቂ ልማት ግቦች አፈፃፀም…የቀጠለ

| ግቦች | የዘላቂ ልማት ግቦችነ አመልካቾች | የ2007 አፈጻጸም (መነሻ ዓመት) | የ2008 አፈጻጸም | ዕቅድ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
| | በዶላር የተተመነ ለታዳጊ ሃገራት የዋለ የገንዘብና የሙያ ድጋፍ (ሳውዝ - ሳውዝ፣ ኖርዝ -ሳውዝ ና ተሪያንጉላር ትብብርንም ጨምሮ) | - | | | | | |
| | አማካይ የጉሙሩክ ታሪፍ መጣኔ | 17.5 | 17.5 | | | | |
| | በኢንዱስትሪ ዞኖች የተገነቡ ፋብሪቻዎች ጥቅል ብዛት | 19 | 52 | | | | |
| | ከሃገሮች ጋር የተደረገ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ስምምነቶች በስምምነት ዓይነት | | | | | | |
| | የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ብዛት በሚሊዮን | 9.6 | 13.6 | 25.3 | 37.9 | 47.0 | 56.0 |
| | የብሮድ ባንድ ኢንተርኔት ተጠቃማች ብዛት በሚሊዮን | 1.6 | 49 | 16.4 | 24.1 | 31.6 | 39.1 |
| | የሸቀጦችና አገልግሎት የውጭ ንግድ ከጠቅላላ ምረት ያለው ድርሻ በመቶኛ | 9.4 | 8 | 15.5 | 15.7 | 18.1 | 20.6 |
| | ለዘላቂ ልማትን ከልማት ፖሊሲ ጋር ለማጣጣም የተቀመጡ ስልቶች | የዘላቂ ልማት ከሀገራዊ የልማት ዕቅድ ጋር ተጣጥሞ ተዘጋጅቷል። | | | | | |
| | የዘላቂ ልማት ግቦችን አፈጻጸምን ለላማሰጥ በተቀመጡ የክትትልና ግምገማ ቅጽ መሠረት ሪፖርቱን አዘጋጅቶ የማቅረብ ብቃት | የክትትልና ግምገማ ሥርዓቱ ተዘርግቷል | | | | | |
| | መደበኛ የስታቲስቲክስ መርሆችን በጠበቀ መልኩ እና ከዘላቂ ለማት ግቦች በተጣጣመ መልኩ በብሄራዊ ደረጃ የተዘጋጁ የዘላቂ ልማት የግብ አመልካቾች | ከዘላዊ ልማት ግቦች ጋር የተጣጣመ ዕቅድና የዕቅድ ክትትልና ግምገማ ፖሊሲ ማትሪክስ ተዘጋጅቷል | | | | | |
| | ከብሄራዊ የስታስቲክሰር መርሆች ጋር የተጣጣሙ የስታቲስቲክስ ሕግ | የስታቲስቲክስ ሕግ አለ | | | | | |
| | በበጀት የተደገፈና እየተተገበረ ያለ የስታቲስቲክስ ዕቅድ | በሔራዊ የስታቲስቲክስ ልማት ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል። | | | | | |
| | በ10 ዓመት ቢያንስ አንዴ የተደረገ የህዝብ ቆጠራ | በ1976፣ በ1987 እና 2007 ዓ.ም ቆጥራ ተካሂዷል | | | | | |
| | የልደት ሰርተፊኬት ያገኙ ህጻናት በመቶኛ | ሥራው ተጀምሯል | | | | | |

# የግርጌ ማስታወሻ

1. የመረጃ ምንጮች፡-የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር፣ የግብርና እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር፣ የብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን
2. የግብርና እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር፣ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር፣ የብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን
3. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣
4. የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የግብርና እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር
5. የትራንስፖርት ሚኒስቴር፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የመገናኛና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ የብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን
6. የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር እና የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር
7. የብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር፣ የመገናኛና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣